አካባቢ ሳይንስ

አንደኛ ክፍል

የመምህር መምሪያ መጽሐፍ



አካባቢ ሳይንስ
፭ኛ ክፍል

የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

አዘጋጅ

ፍቅሩ ቸርነት
እርጎዬ ምስጋናው
አምደብርሃን አበበ
አማኑኤል ኃይሌ
ስሜነህ ደሳለው

አርታኢ እና ገምጋሚዎች

ሠለሞን ወንድሙ
በላይ በለጠ
ሙሉነህ ተክለብርሃን
ጌታሁን ጌታቸው
አሊ ከማል
ፍቅርተ ቶለሳ
ምህረቱ ዋሌ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ

ሥዕላዊ መግለጫ እና ገጽ ቅንብር

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (ሲሳይ ደጉ)

2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀምንባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ 1

የአካባቢያችን መገኛ 1

1.1 የመገኛ ምንነት 2

1.2 ዐራቱ አቅጣጫዎች (ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ) 4

1.3 ከትምህርት ቤታችንና ከወረዳችን አንጻንር የቤታችን መገኛ 7

1.4 በዙሪያችን የሚገኙ ጎረቤቶቻችን መገኛና ስም 9

ምዕራፍ ሁለት 12

ሳይንስን መገንዘብ 12

2.1 የሰውነታችን ክፍሎች 13

2.2 የግል ንፅሕናን መጠበቅ 22

2.3 የብርሃን ምንነት 24

ምዕራፍ ሦስት 27

ተፈጥሮአዊ አካባቢ 27

3.1 የአካባቢያችን የአየር ንብረት 28

3.2 ሕይወት ያላቸው ነገሮች 42

3.3 ንፅሕናና የግል ንፅሕና 52

ምዕራፍ አራት.....55

ማኅበራዊ አካባቢ.....55

4.1 ለመኖር ምን ያስፈልገናል?.....56

4.2 የቤተሰብ አባላትና ሚናቸው.....58

4.3 በአካባቢያችን ለመኖር የሚያስፈልጉ እጽዋት.....62

4.4 በትምህርት ቤታችን ምን ምን ነገሮችን እናገኛለን?.....65

4.5 በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንሥራ.....66

4.6 የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን መለየት.....70

ምዕራፍ አምስት.....73

ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች.....73

5.1 ተሸከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዴት እንጠቀማለን?.....74

5.2 ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?.....81

መግቢያ

የአንደኛ ክፍል መምህራን የተማሪዎች የወደፊት እጣፋንታ ላይ መሠረት ከሚጥሉ ወላጆቻቸው በማይተናነስ መልኩ ከፍተኛ ሚና በመጫወት የወደፊት ሀገር ተረካቢ ዜጎችን ለመቅረፅ አሻራ የሚያሳርፉበት የክፍል ደረጃ ነው።

የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ምንነት እና ለተማሪዎች ስላለው ጠቀሜታ ወደ መምህር መምሪያው አጠቃቀም ከመግባታችን በፊት እንደሚከተለው ተብራርቷል።

ሳይንስ የሚለው ቃል ሳይንቲያ (scientia) ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ዕውቀት" ማለት ነው።

አካባቢ ሳይንስ በአካባቢያችን ስለሚገኙ ሕይወት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮች መስተጋብር እና በተፈጥሮአዊ አካባቢያቸው ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ከሰው ልጆች ጋር በማስተሳሰር የሚያስረዳ የሳይንስ ትምህርት ክፍል ነው። ስለዚህ አካባቢ ሳይንስ ሕፃናት በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሕይወት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮችን ትስሥር በማድነቅ የሚማሩበት የሳይንስ ዘርፍ ነው።

ይህ የአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ለተማሪዎች ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞችን ይሰጣል፤ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ፡-

- ስለ አካባቢያቸው ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሰፉ ይረዳቸዋል።
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን በቀላሉ ለማወቅ ያስችላቸዋል።
- ስለ አካባቢያቸው ማወቅ ሌሎች ትምህርቶችን በቀላሉ ለመረዳት ያስችላቸዋል።
- ስለ ራሳቸው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች እና ጥቅሞቻቸው ግንዛቤ እንድኖራቸው ይረዳቸዋል::
- ልጆች ወደ ውስብስብ የሳይንስ ምስጢር ለመግባት አካባቢያቸውን እንደመነሻ ዕውቀት እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል።

በአጠቃላይ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ዋና ዓላማው ንቃትና ግንዛቤን እንዲሁም ሳይንሳዊ እውቀትን እንዲያዳብሩ ማስቻል ነው። ስለሆነም ይህ የአንደኛ ክፍል መጽሐፍ በዋናነት ተማሪዎች አካባቢያቸውን በሚገባ እንዲገነዘቡና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ የተቀናጀ ዕውቀትን አካቶ እንደሚከተለው በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ ቀርቧል።

ምዕራፍ አንድ፡ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እና የራሳቸውን መገኛ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ጋር በማነጻጸር እንዲገነዘቡ የሚያስችል ምዕራፍ ነው።

በምዕራፍ ሁለት፡ ተማሪዎች ስለ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸው፣የግል ንጽሕናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ እንዲሁም ስለ ብርሃንና ጨለማ ልዩነት እንዲገነዘቡ ሆኖ ቀርቧል።

ምዕራፍ ሦስት፡ ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን ከአየር ሁኔታ እና አየር ንብረት ጋር በማዋሀድ ሕይወት ስላላቸው እና ስለሌላቸው ነገሮች አጠቃላይ ትስሥር ያስገነዝባል።

ምዕራፍ አራት፡ ስለ ማህበራዊ አካባቢያችን ማለትም የቤተሰብ አባላት እና ሚናቸው፣ስለ መሠረታዊ ፍላጎቶች፣ ተማሪዎች በጋራ ሲጫወቱ እና ሲሠሩ ሊያደርጓቸው ስለሚገቡ ጥንቃቄዎችና ስለሚያዳብሯቸው መልካም ነገሮች እንዲሁም የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን እንዲዘረዝሩና እንዲተገብሩ የሚያስችል ሆኖ የቀረበ ነው።

በመጨረሻም ምዕራፍ አምስት ተዕዕኖ የሚፈጥሩ ድምበር ተሻጋሪ ጉደዮችን በተመለከተ ስለ ተሸከርካሪ የመንገድ ደንቦች፤ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት፣ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት እና በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሕፃናት እና ቤተሰቦቻቸው ንዘኔታና ፍቅር ማሳየት እንደሚገባቸው ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ሆኖ ተዘጋጅቷል።

በአጠቃላይ እነዚህ ምዕራፎች አጥጋቢ የመማር ብቃቶችን፣ ዋና ይዘቶች እና ንዑስ ይዘቶችን፣ የተለያዩ መልመጃዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን እና ተግባራትን እንዲሁም የየምዕራፉ ማጠቃለያ ነጥቦችን፣ የማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎችን እና በየምዕራፉ መጨረሻ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚፈትሹበት ወይንም ምን ያህል እንደተገነዘቡ የሚያረጋግጡበትን (ፍተሻን) በማካተት ተዘጋጅተዋል።

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው ለአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ መምህራን ነው። ስለዚህ መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት የመምህር መምሪያውን ትኩረት ሰጥተው ሊያነቡት ይገባል። ምክንያቱም እርስዎ ወደ ክፍል ሲገቡ መማር ማስተማሩን ስኬታማ ለማድረግ ሊተገብሯቸው የሚገቡ ነገሮችን በቅደም ተከተል ከዚህ የመምህር መምሪያ ስለሚያገኟቸው ነው። የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ የተማሪዎች መጽሐፍን ተማሪ ተኮር በሆነ ሥነ-ዘዴ ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል። በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱት የቡድን ውይይቶች፣ ተግባራዊ ክንዋኔዎች፣ የግል ሥራዎች እና የመሳሰሉት የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች ተማሪዎችን በትምህርቱ ላይ የበለጠ ተሳታፊ ለማድረግ ታስቦ ነው። በቡድን ውይይቱ ወይንም ተግባራዊ ክንዋኔው ወቅት ሁሉም የቡድን አባላት ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ምን ጊዜም ከውይይቱ በኋላ በጽብረቃ ወቅት ሁሉም አባላት እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ማበረታታት እና በመጨረሻም በእርስዎ በኩል የማጠቃለያ ገለጻ መስጠት ያስፈልጋል። በተጨማሪም መልመጃዎች እና የተግባር ሥራዎችን በራሳቸው ጥረት እንዲሰሩ በማበረታታት መልሶቻቸውን ያረጋግጡላቸው።

በተማሪዎች አማካኝነት በግል የተሠሩ ሥራዎች ለክፍሉ ቀርበው ላቅ ላሉ ሥራዎች እውቅናን በመስጠት እና በሚታይ ቦታ ላይ እንዲቀመጡ በማድረግ ለሚቀጥለው ሥራቸው ብርታትን ያጎናጽፏቸው። እንዲሁም ዝቅተኛ እና መሻሻል የሚገባቸው ሥራዎች ደግሞ የሞራል ድጋፍ እና የተለያዩ ማነቃቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም ወደ መካከለኛ እና ከፍተኛ የትምህርት አቀባበል ያላቸው ተማሪዎች ማቀራረብ ያስፈልጋል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ብቃት መለካት አስፈላጊ ነው። ተማሪዎችን በትምህርት አቀባበላቸው በሦስት በመለየት ከፍተኛ የትምህርት አቀባበል ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ይበልጥ ጠንክረው እንዲሰሩ በክፍል እና ከክፍል ውጪ የሚሠሩ ተጨማሪ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ መስጠት ያስፈልጋል። እንዲሁም ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል ብቃት ላላቸው ተማሪዎች በተለየ መልኩ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመስጠት፣ በቡድን ውይይት ወቅት ጠንከር ካሉ ተማሪዎች ጋር በመመደብ፣ ከትምህርት ጊዜ ውጪ ያለውን ጊዜም ቢሆን በመጠቀም ልዩ ድጋፍ በማድረግ ወደ መካከለኛ እና ከፍተኛ የመማር ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ጋር ማቀራረብ ተገቢ ነው።

በክፍል ውስጥ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችንም በመለየት የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም ለአካል ጉዳተኞች እንደየአስፈላጊነቱ ልዩ ድጋፍ መስጠት ይኖርብዎታል።

የመማሪያ መጽሐፉ ዝርዝር ይዘቶች የክፍለ ጊዜ ክፍፍልን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ምዕራፍ	ይዘቶች	የክፍለ ጊዜ ብዛት	ምርመራ
አንድ	<u>የአካባቢያችን መገኛ</u>	42	
	1.2 የመገኛ ምንነት	9	
	1.2 ዐራቱ አቅጣጫዎች (ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ)	15	
	1.3 ከትምህርት ቤታችንና ከወረዳችን አንጻር የቤታችን መገኛ	9	
	1.4 በዙሪያችን የሚገኙ ጎረቤቶቻችን መገኛና ስም	9	
ሁለት	ሳይንስን መገንዘብ	54	
	2.1 የሰውነታችን ክፍሎች	24	
	2.2 የግል ንጽሕናን መጠበቅ	15	
	2.3 የብርሃን ምንነት	15	
ሦስት	ተፈጥሮአዊ አካባቢ	54	
	3.1 የአካባቢያችን የአየር ንብረት	20	
	3.2 ሕይወት ያላቸው ነገሮች	24	
	3.3 ንጽሕናና የግል ንጽሕና	10	
አራት	ማኅበራዊ አካባቢ	54	
	4.1 የአካባቢያችን የሚገኙ ተፈላጊ እጽዋቶች	12	
	4.2 የቤተሰብ አባላትና ሚናቸው	9	
	4.3 ለመኖር ምን ያስፈልጋል?	8	
	4.4 በትምህርት ቤታችን ምን ምን ነገሮችን እናገኛለን?	8	
	4.5 በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንሥራ	8	
	4.6 የትምህርት ቤትን ሕግና ደንቦችን መለየት	9	
አምስት	ተዕዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች	34	
	5.1 ተሸከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዴት እንጠቀማለን?	17	
	5.2 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንድን ነው?	17	

ምዕራፍ አንድ

የአካባቢያችን መገኛ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 42

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የመገኛን ምንነት ፅንሰ ሐሳብ ይገልጻሉ፡፡
- ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ አቅጣጫዎችን ይለያሉ፡፡
- የአንድ ቦታ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር እንዴት እንደሚወሰን ያብራራሉ፡፡
- በዙሪያቸው የሚገኙ ነገሮችን አቅጣጫ ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ በማለት ይለያሉ፡፡
- በትምህርት ቤት የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ገጽታና መገኛ ይለያሉ፡፡
- የትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤትንና የጎረቤት መገኛን ይለያሉ፡፡
- የአካባቢን ንድፍ ካርታ መሥራትና የትምህርት ቤት አቅጣጫን ያሳያሉ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

1.1 የመገኛ ምንነት

1.2 ዐራት አቅጣጫዎች (ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ)

1.3 ከትምህርት ቤታችንና ከወረዳችን አንጻንር የቤታችን መገኛ

1.4 በዙሪያችን የሚገኙ ጎረቤቶቻችን መገኛና ስም

1.1 የመገኛ ምንነት

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 9

ከንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **የመገኛን ምንነት ፅንሰ ሐሳብ ይገልጻሉ፡፡**

መገኛ

የትምህርቱ ጭብጥ

ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ በዋናነት መረዳት የሚገባቸው የመገኛን ምንነት ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ በቤታቸው ውስጥ የተለያዩ ዕቃዎችን፣ በመኖሪያ ቤት ግቢ እንዲሁም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን መገኛ ቦታ ይገነዘባሉ፡፡ በተጨማሪም በአካባቢያቸው የሚገኙ እንደ ትምህርት ቤት፣ መኖሪያ ቤታቸውን፣ የጎረቤት ቤት እና የመሳሰሉትን ነገሮች መገኛ ቦታ ይለያሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ተማሪዎች ለአካባቢ ሳይንስ ለትምህርት ፍቅር እንዲኖራቸው ለማድረግ ለማስተማር ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ መገኛን በተመለከተ የተገለጹትን ማብራሪያዎች በማንበብ፣ ተያያዥ የሆኑ ሥዕሎችን እና ምሳሌዎችን በመጠቀም በደንብ ይርዷቸው፡፡ ለንዑስ ርዕሱ አስፈላጊ መርጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀትም ለተማሪዎች ግልፅ ሆኖ በሚታይ ቦታ መስቀል ይጠበቅበዎታል፡፡ በተጨማሪም ወደ ክፍል ሲገቡ ለተማሪዎች ስለመገኛ ምንነት እንዲረዱና በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች እንደ ምሳሌ በመጥቀስ መገኛቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ለተማሪዎች ስለመገኛ ምንነት ገለጻ ካደረጉ በኋላ አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴን ለመተግበር እንዲቻል መማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 1.1 የነገሮች መገኛ መሠረት በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች ሥዕሉ ላይ የሚገኙ ነገሮችን መገኛ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎችን ስለመገኛ ምንነት እንዲወያዩ በማድረግ እያንዳንዱ ተማሪ የመገኛን ምንነት እና በክፍል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን መገኛ ቦታ ተራ በተራ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- **የሰሌዳው መገኛ የት ነው?**
- ***መጽሐፉ የት ይገኛል?...የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን መገኛ በመለየት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡***

በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን መልመጃ ደብተራቸው ላይ ገልብጠው በሥዕሉ መሠረት እንዲሰሩና የበለጠ ስለመገኛ ምንነት እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ስለመገኛ ምንነት የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- የተለያዩ ነገሮችን መገኛ ቦታ የሚያሳዩ ሥዕሎች፡፡
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ፡፡

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄና መልስ
- የተግባር ሥራ (ስለ መገኛ ምንነት)
- የፅሁፍ ጥያቄዎች

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ የነገሮችን መገኛ ቦታ እንዲያሳዩ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን መገኛ መጠየቅ፡፡
- ✓ ሥዕሉን መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የነገሮችን መገኛ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የመልመጃ 1.1 መልሶች

<u>የግለጹ መልሶች</u>

1. ዛፉ ሥር
2. ዛፉ ላይ
3. ከልጆች ፊት ለፊት

<u>የተግባር አንድ መልሶች</u>

1. መምህር! የክፍሉን ገፅታ መሠረት በማድረግ የጥቁር ሰሌዳውን መገኛ ይንገሯቸው፡፡
2. መምህር! የክፍሉን ገፅታ መሠረት በማድረግ ከጥቁር ሰሌዳው አንፃር የክፍሉን በር መገኛ ይንገሯቸው፡፡
3. መምህር! የክፍሉን ገፅታ መሠረት በማድረግ የመስኮቶቹን መገኛ ይንገሯቸው፡፡

1.2 አራቱ አቅጣጫዎች (ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ)

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 15

የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ አቅጣጫዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ በዙሪያችን የሚገኙ ነገሮችን አቅጣጫ ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ በማለት ይለያሉ፡፡
- ✓ የአንድ ቦታ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር እንዴት እንደሚወሰን ያብራራሉ፡፡

የትምህርቱ ጭብጥ

አንድ ቦታ ወይንም አንድ ነገር በአካባቢው ካሉት ቋሚ ነገሮች አንጻር የሚገኝበትን ሥፍራ የምንገልጽበት መንገድ አቅጣጫ ይባላል፡፡

ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃቸው የራሳቸውን አራት አቅጣጫዎች ማለትም ቀኝ፣ ግራ፣ ፊት እና ኋላ አቅጣጫቸውን፣ የጓደኞቻቸውንና የተለያዩ ነገሮችን ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላን መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቀላሉ በአካባቢያቸዉ የሚገኙ ነገሮችን አቅጣጫ ይለያሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ተማሪዎች ቀኝና ግራ፤ ፊትና ኋላ አቅጣጫዎችን በደንብ መለየት ስለሚገባቸዉ በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ሥዕል 1.2 የትምህርት ቤት ግቢ በመጠቀም ተያያዥ የሆኑ መርጃ መሣሪያዎች ተዘጋጅተው ግልፅ ሆኖ በሚታይ ቦታ መሰቀል ይኖርባቸዋል፡፡

ስለ አራቱ አቅጣጫ ማለትም ቀኝ፣ ግራ፣ ፊት እና ኋላ የተገለጹ ማብራሪያዎችን፣ ምሳሌዎችን እና ሥዕሎችን እንዲሁም የተለያዩ የተግባር ሥራዎችን ከመማሪያ መጽሐፉ በደንብ በመረዳት ተማሪዎችን በአቅማቸው ብቁ ለማድረግ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበዎታል፡፡

ስለ አቅጣጫ ምንነት በቂ ዕውቀት ለማስጨበጥ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተጠየቁ ጥያቄዎችን በደንብ በመረዳት ምላሽ ያዘጋጁ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ይህንን የትምህርት ይዘት ማስተማር ሲጀምሩ በመጀመሪያ ስለ አቅጣጫ ምንነት እንዲገልጹ በመጋበዝ ይጀምሩ፡፡ በመቀጠልም ስለ አራቱ አቅጣጫዎች ማለትም ቀኝና ግራ ፊትና ኋላ መማሪያ መጽሐፉን መሠረት በማድረግና ምሳሌዎችን በመስጠት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ የተሰጠውን የተግባር ሥራ ተማሪዎችን ተራ በተራ በማሥነሳት ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠቀሙ፡-

- ወደ ሰሌዳዉ በመዞር አራቱን አቅጣጫዎች ቀኝና ግራ ፊትና ኋላቸውን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ፊታቸውን ወደ ተማሪዎች በማዞር አራቱን አቅጣጫዎች ቀኝና ግራ ፊትና ኋላቸውን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ፊታቸውን ወደ በሩ በማዞር አራቱን አቅጣጫዎች ቀኝና ግራ ፊትና ኋላቸውን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ጀርባቸውን ወደ በሩ በማዞር አራቱን አቅጣጫዎች ቀኝና ግራ ፊትና ኋላቸውን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

መምህር! ተማሪዎችን ከክፍል ወደ ሰንደቅ ዓላማው ስፍራ ይዘው ይሂዱ፡፡ ተማሪዎች እያንዳንዱን የአገልግሎት መስጫ ክፍል መገኛ ቦታ በትኩረት እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ስለ አቅጣጫ በክፍል ውስጥ የተማሩትን መሠረት በማድረግ እያንዳንዳቸውን አንዱን ከአንዱ አንጻር በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ብዙ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚገኙ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል፦

- የአስተዳደር ቢሮ
- የመማሪያ ክፍሎች
- የመጫዎቻ ሜዳ
- የመፀዳጃ ቤት
- የሰንደቅ ዓላማ ቦታ
- ቤተ መጻሕፍት
- ቤተ - ሙከራ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ግቢያቸው ከገቡ በኋላ ስለ እነዚህ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መገኛ ይለያሉ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች በየት በኩል እንደሚገኙ አቅጣጫቸውን በቀኝ፣ በግራ፣ በፊት እና ከኋላ እያሉ እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የተሰጠውን የተግባር ሥራ ሶስት በደብተራቸው ገልብጠው ሰንጠረዥ 1 የትምህርት ቤት የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መገኛ የሚሞሉበትን መንገድ ተረድተው በትክክል እንዲሞሉ ያድርጓቸው፡፡ እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፉ የተሰጠውን መልመጃ እንዲሰሩ ከሰጧቸው በኋላ በትክክል ስለመስራታቸው ያረጋግጡ፡፡ በመጨረሻም ስለ አራቱ አቅጣጫዎች (ቀኝ፣ ግራ፣ ፊት እና ኋላ) በቃል ጠይቀው በደንብ መገንዘባቸውን ካረጋገጡ በኃላ ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- የተለያዩ አራቱን አቅጣጫዎች የሚያሳዩ ሥዕሎች፡፡
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ፡፡
- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን፣ የመጫወቻ ቦታዎችን አንጻራዊ መገኛ የሚያመለክት ንድፍ ካርታ ይጠቀሙ፡፡

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የተግባር ሥራ (አቅጣጫን መለየት)
- ሠርቶ ማሳየት
- የፅሁፍ ጥያቄዎች
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ አቅጣጫዎችን ቀኝና ግራ፤ ፊትና ኋላ በማለት መለየታቸውን ማረጋገጥ።
- ✓ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ለማመልከት የሚያደርጉት ጥረት መሻሻሉን ይከታተሉ።
- ✓ ሥዕሎችን መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የነገሮችን አቅጣጫ እንዲያሳዩ ያድርጉ።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የተግባር 2 መልሶች

1. መምህር! ተማሪዎች በትክክል የቀኝ አቅጣጫቸውን ማሳየታቸውን ይገምግሙ።
2. መምህር! ተማሪዎች በትክክል የግራ አቅጣጫቸውን ማሳየታቸውን ይገምግሙ።
3. መምህር! ተማሪዎች በትክክል የፊት ለፊት አቅጣጫቸውን ማሳየታቸውን ይገምግሙ።
4. መምህር! ተማሪዎች በትክክል የኋላ አቅጣጫቸውን ማሳየታቸውን ይገምግሙ።

የመልመጃ 1.2 መልሶች

	ከሰንደቅ አላማው አንፃር	በስተቀኝ	በስተግራ	ፊት ለፊት	በስተኋላ
1	ቤተ-መጽሐፍት		✓		
2	የመማሪያ ክፍሎች	✓			
3	የመጫወቻ ሜዳ			✓	
4	የመፀዳጃ ቤት				✓

የግለጹ መልሶች

1. ቢጫና ቀይ
2. ጥቁር
3. በስተኋላ
4. ቢጫና አረንጓዴ

1.3 ከትምህርት ቤታችንና ከወረዳችን አንጻንር የቤታችን መገኛ

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 9

የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **ከትምህርት ቤታቸው አንጻር የቤታቸውን መገኛ ይናገራሉ፡፡**
- ✓ **ከወረዳቸው አንጻር የቤታቸውን መገኛ ይናገራሉ፡፡**

የትምህርቱ ጭብጥ

ተማሪዎች በዚህ የዕድሜ ደረጃቸው በአካባቢያቸው ስለሚገኙ እንደ መኖሪያ ቤት፣ ትምህርት ቤት እና የጎረቤት መገኛ አቅጣጫን መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመኖሪያ ቤታቸውን መገኛ አቅጣጫ ከትምህርት ቤታቸውና ከወረዳቸው አንጻር በየት በኩል እንደሚገኝ ይለያሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ተማሪዎች ከትምህርት ቤታቸውና ከወረዳቸው አንጻር የቤታቸውን መገኛ በቀላሉ እንዲለዩ ተያያዥ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፡፡ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የተማሪዎችን የመኖሪያ ቤት፣ የትምህርት ቤት እና የወረዳቸውን መገኛ አቅጣጫዎች አገናዝበው ለማስተማር ዝግጁ ሆነው መገኘት ይጠበቅበዎታል፡፡ እንደ መርጃ መሣሪያነት የመኖሪያ አካባቢን ሊያሳዩ የሚችሉ የተለያዩ ሥዕሎችን እና ንድፍ ካርታ መጠቀም ይቻላል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ወደ ዋናው ንዑስ ርዕስ ከመግባትዎ በፊት ስለአቅጣጫ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ስለ ንዑስ ርዕሱ እንደሚከተለው አጭር ገለጻ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በአዲስ አበባ የታችኛው የአስተዳደር እርከን ወረዳ ይባላል፡፡ በአንድ ወረዳ ውስጥ ብዙ ትምህርት ቤቶች ሊገኙ እንደሚችሉ ማብራሪያ መስጠት ይችላሉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎችን በመማሪያ መጽሐፉ የተሰጠውን የቡድን ውይይት ለመወያየት ዝግጁ ያድርጓቸው:: በሦስት በሦስት ቡድን በመክፈል በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ሥዕል 1.3 የአንድ አካባቢ ገፅታ በትኩረት ከተመለከቱ በኋላ የመኖሪያ ቤቱን መገኛ፡-

1. **ከትምህርት ቤቱ አንጻር**
2. **ከወረዳው ጽሕፈት ቤት አንጻር የሚገኝበትን አቅጣጫ በቡድናቸው መሰረት ተራ በተራ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡**

በመጨረሻም የተማሩትንና ከሥዕሉ የተረዱትን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የመኖሪያ ቤታቸውን መገኛ ከትምህርት ቤታቸው አንጻር በየት በኩል እንደሚገኝ እንዲናገሩ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤቶችንና የወረዳ ጽሕፈት ቤትን በአንድ ላይ የያዘ የመኖሪያ አካባቢ ሥዕል።
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ።
- የትምህርት ቤትንና የመኖሪያ ቤቶችን አንጻራዊ መገኛ የሚያመለክት ንድፍ ካሪታ።

የማስተማሪያ ሥነ - ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (የመኖሪያ ቤት መገኛ ከትምህርት ቤት እና ከወረዳ አንጻር)
- የዕሁፍ ጥያቄዎች
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ከትምህርት ቤታቸው አንጻር የመኖሪያ ቤታቸውን መገኛ አቅጣጫ መለየታቸውን ማረጋግጥ
- ንድፍ ካርታን በመጠቀም የትምህርት ቤታቸውን እና የወረዳቸውን መገኛ እንዲያሳዩ ማድረግ
- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የተለያዩ ቦታዎችን አቅጣጫ ለመጠቆም የሚያደርጉት ጥረት መሻሻሉን መከታተል።
- ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 1.3 መልሶች

የግለጹ መልሶች

1. ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን መልስ ይስጡ።
2. ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን መልስ ይስጡ።

የተግባር ሦስት መልሶች

ሰንጠረዥ 1 የትምህርት ቤት የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መገኛ

የውይይት አንድ መላሶች

- መምህር! ሥዕሉን መሠረት በማድረግ የመኖሪያ ቤት መገኛን ከትምህርት ቤቱ እና ከወረዳው አንፃር ይመልሱ።

1.4 በዙሪያችን የሚገኙ ጎረቤቶቻችን መገኛና ስም

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 9

ከንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **ከመኖሪያ ቤታቸው አንጻር የጎረቤቶቻቸውን መገኛ ያመለክታሉ፡፡**
- ✓ **የመኖሪያ አካባቢያቸውን ንድፍ ካርታ ያሳያሉ፡፡**

የትምህርቱ ጭብጥ

በቤታችን አቅራቢያ የሚገኙ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ጎረቤት ይባላሉ፡፡ ተማሪዎች በዚህ የዕድሜ ክልል ወይም የክፍል ደረጃቸው የጎረበትን መጠሪያ ስም ለይተው ከመኖሪያ ቤታቸው በየት በኩል እንደሚገኝ መናገር ይችላሉ፡፡

በቀላሉ እና በፍጥነት የሚሳል *ሥዕል* ንድፍ ካርታ ይባላል፡፡ ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ በአካባቢያቸው የሚገኙ የመኖሪያ ቤታቸውን፣ የጎረቤታቸውን፣ የትምህርት ቤታቸውንና የመሳሰሉትን በንድፍ ካረታ በመሣል መገኛ ቦታቸውን ማሳየት ይችላሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

***መምህር!* ትምህርቱን ከማስተማርዎ በፊት ስለጎረቤት እና ንድፍ ካርታ ምንነት ጽንሰ ሀሳብ በደንብ መረዳትና መዘጋጀት እንዲሁም በአንድ አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ጎረቤቶች መኖሪያ ቤት በአንድ ላይ የያዘ የመኖሪያ አካባቢ *ሥዕል* እና የትምህርት ቤት ንድፍ ካርታ የሚያሳዩ *መርጃ መሣሪያዎችን* አዘጋጅተው ግልፅና ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ መሰቀል ይኖርብዎታል፡፡**

የትምህርቱ አቀራረብ

***መምህር!* ወደ ዋናው ንዑስ ርዕስ ለመግባት *መጀመሪያ* ተማሪዎች የጎረበቶቻቸውን ስም እየጠቀሱ የጎረበት ምንነት እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ ስለ ጎረቤት አጭር ገለጻም ያድርጉላቸው፡፡ በዚህ ዕድሜ ያሉ ህፃናት ስለ ጉርብትና ያላቸው ግንዛቤ በጣም አነስተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በጉርብትና የሚኖሩ ልጆች ይጣላሉ፡፡ ስለዚህ ልጆችን ከእንደዚህ ዓይነት መልካም ያልሆነ ባህርይ እንዲታቀቡ ምክር መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በመቀጠልም በ*መማሪያ* መጽሐፉ ላይ ያለውን *ሥዕል* 1.4 ንድፍ ካርታ በአትኩሮት እንዲመለከቱና እርስ በእርስ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ *መጽሐፉ* ላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡**

በተጨማሪም በ*መማሪያ* መጽሐፉ ላይ ያሉትን *ሥዕሎችንና* *መርጃ መሣሪያዎችን* መሰረት በማድረግ ስለ ንድፍ ካርታ ምንነት የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን መልኩ ያስተምሯቸው፡፡ በመቀጠልም እያንዳንዳቸው በተግባር አራት ላይ የተሰጠውን መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤታቸውን ንድፍ ካርታ በወረቀት እንዲሠሩ ካደረጉ በኋላ በትክክል መስራታቸውን በማረጋገጥ ስለ ንድፍ ካርታ ምንነት መረዳታቸውን ያረጋግጡ፡፡

በመጨረሻም በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ በማድረግና በትክክል ስለመሥራታቸው በማረጋገጥ ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- በአንድ አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ጎረቤቶች መኖሪያ ቤት በአንድ ላይ የያዘ የመኖሪያ አካባቢ ሥዕል፡፡
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ፡፡
- የትምህርት ቤት ንድፍ ካርታ፡፡
- የመኖሪያ ቤት ንድፍ ካርታ፡፡

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- ጥያቄና መልስ
- የተግባር ሥራ (የትምህርት ቤታቸውን እና ቤታቸውን ንድፍ ካርታ መሳል)
- የፅሁፍ ጥያቄዎች

<u>የምዘናና የክትትል ስልቶች</u>

- ✓ የጎረቤታቸውን ስምና መገኛ እንዲገልጹ ማድረግ
- ✓ የትምህርት ቤትና የመኖርያ ቤት ንድፍ ካርታ መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ✓ በመጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ መልመጃ ማሠራት፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የተግባር አራት መልስ

- ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን የት/ቤት ንድፍ ካርታ ይሰራሉ

የመልመጃ 1.4 መልሶች

<u>የግለጹ መልሶች</u>

1. ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን መልስ ይስጡ፡፡
2. ንድፍ ካርታውን በደንብ ስለመሳላቸው ያረጋግጡላቸው፡፡

ሥዕል 1.4 የጎረቤታሞች መገኛ ጥያቄዎች መልስ

1. 4
2. እነፈትያ ፣ እነዮናስ ፣ እነፀሐይ እና እነአወል
3. በስተግራ
4. እነፀሐይ እና እነአወል

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ. እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

ለ. የምርጫ መልሶች

1. ሀ
2. ሐ

ሐ. የግለፅ መልሶች

1. አንድን ቦታ ወይንም ነገር በአካባቢው ካሉት ነገሮች አንጻር የሚገኝበትን ሥፍራ ለመግለጽ የምንጠቀምበት መንገድ አቅጣጫ ይባላል፡፡
2. የተወሰነ አካባቢን ለማሳየት ወይም የአንድን ቦታ መገኛና አቅጣጫ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ሳይንስን መገንዘብ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 54

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን ይጠራሉ
- የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን ይናገራሉ
- የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና ይለያሉ፡፡
- የግል ንፅሕና በመረዳት ይተገብራሉ
- የጨለማን ምንነት ይገነዘባሉ

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

2.1 የሰውነታችን ክፍሎች

2.2 የግል ንጽሕናን መጠበቅ

2.3 የብርሃን ምንነት

2.1 የሰውነታችን ክፍሎች

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 24

የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን ይጠራሉ፡፡
- ✓ የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን ይናገራሉ፡፡
- ✓ የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና ይለያሉ፡፡

ሀ. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምንነት

የትምህርቱ ጭብጥ

ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃቸው መረዳት የሚገባቸው ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ሲሆን ውጫዊ የሰውነት አካል ክፍሎች ራስ፣ ፀጉር፣ ፊት፣ ግንባር፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ ከንፈር፣ አንገት፣ ትከሻ፣ እጅ፣ ደረት፣ ሆድ፣ ወገብ፣ ጉልበት ፣ቅልጥም፣ እግር፣ ተረከዝ እና የመሳሰሉት መሆናቸውን ይገነዘባሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ አስቀድሞ ለትምህርቱ አስፈላጊ መርጃ መሣሪያዎች በቅድሚያ በማዘጋጀት ወደ ክፍል ሲገቡ ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ ያስቀምጡ፡፡ ስለ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች በደንብ ለተማሪዎች ለማስተማር በተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን ሥዕል እና ጥያቄዎች ተመልክተው ዝግጅት ያድርጉ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ይህን ንዑስ ርዕስ በቀላሉ ለማስተማር እንዲረዳዎና ትምህርቱን አሳታፊ ለማድረግ እንዲቻል በመማሪያ መጽሐፉ በተሰጠው የተግባር ሥራ አንድ መሠረት ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመጥራትና በማመልከት እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ለትምህርት መርጃ ያዘጋጁትንና በመጽሐፉ የሚገኘውን ሥዕል 2.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች በመጠቀም ስለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ለተማሪዎች በሚገባ ያስረዱ፡፡

በመቀጠልም ተማሪዎች ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን እያንዳንዳቸው ለይተው ማሳየታቸውን ያረጋግጡ፡፡ በመቀጠልም የቡድን ውይይት አንድን መሠረት በማድረግ ተማሪዎችን በቡድን አራት አራት በማድረግ ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸው ምን ምን ጥንቃቄዎች እንደሚያደርጉ ተወያይተው ከየቡድኑ አንድ አንድ ተማሪ እየተነሳ የተወያዩበትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

በመጨረሻም ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉትን ፀጉር፣ ራስ፣ ግንባር፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድ፣ ክንድ፣ እጅ፣ ጉልበት፣ እግር እና የመሳሰሉት መሆናቸውን እና ስለሚያስፈልጋቸው ጥንቃቄ በማስታውስ ስለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

ለምሳሌ፡-

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምን ምን ናቸው?
2. ለውጫው የሰውነት ክፍሎች ምን ምን ጥንቃቄዎች ይደረጋሉ? .... የመሳሰሉትን በመጠየቅ ተማሪዎች በትክክል መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኃላ ትምህርቱን ያጠቃልሉ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ሥዕል
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ሞዴል
- ስዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

<u>የማስተማሪያ ሥነ - ዘዴዎች</u>

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- እያሳዩ ማስተማር
- የቡድን ውይይት (ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን)
- ጥያቄና መልስ
- የፅሁፍ ጥያቄዎች

<u>የምዘናና የክትትል ስልቶች</u>

- ✓ ተማሪዎች የራሳቸውን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች እንዲያመለክቱ የቃል ጥያቄ ይጠይቁ፡፡
- ✓ በስዕሉ አማካኝነት ተማሪዎች ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ስም እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚደረጉ ጥንቃቄዎች እንዲዘረዝሩ ይጠይቁ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የመልመጃ 2.1ሀ መልስ

<u>የግለጹ መልሶች</u>

1. ፀጉር፣ ራስ፣ ግንባር፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ ሆድ፣ ክንድ፣ እጅ፣ ጉልበት፣ እግርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የተግባር አንድ መልስ

- መምህር! ተማሪዎች ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን በትክክል ማመልከታቸውን ይመዝኑ፡፡

የቡድን የውይይት አንድ መልስ

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን የሚደረጉ ጥንቃቄዎች ለመጠበቅ፡-

- ዘወትር እጆቻችን፣ እግሮቻችን እና ፊታችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
- በየጊዜው ፀጉራችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብና ማበጠር
- ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀን ገላችንን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
- ዘወትር የአፍንጫችን እና የጆሯችን ዕዳት መጠበቅ እና
- ጥፍራችን መቁረጥ ይኖርብናል።

ለ. የስሜት አካላትና ጥቅሞቻቸው

ዓይን

የትምህርቱ ጭብጥ

በዚህ የክፍል ደረጃቸው ተማሪዎች ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ምንነት ከመገንዘባቸውም በተጨማሪ አምስቱ የስሜት አካላት የሚባሉትን ዓይን፣ አፍንጫ፣ ጆሮ፣ ምላስና ቆዳን ከነተግባራቸው ለይተው ይናገራሉ።

ዓይን ከአምስቱ የስሜት አካላት መካከል አንዱ ሲሆን ነገሮችን ለማየት የምንጠቀምበት ውጫዊ የሰውነት ክፍል ነው።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ስለዓይን ጥቅም የሚያመለክት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል። ስለዚህ የተለያዩ የዓይን ሞዴሎች፣ ሥዕሎች እና ስለዓይን ጥቅም በተግባር ለማሳየት የተለያየ ቀለም ያላቸው ኪሶችንም ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎችን ስለዓይን ጥቅም በመጠየቅ የዕለቱን ትምህርት ያስተዋውቋቸው። ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎችን አምስት አምስት አባል ያለው ቡድን እዲመሰርቱ ያድርጓቸው። ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በማቅረብ፡-

- ከአምስቱ የቡድን አባላት አንድ አንድ ተማር በማሥነሳት በዓይኖቻቸው ሥስቱን ኪሶች ከተመለከቱ በኋላ ምን ዓይነት ቀለም ያላቸውን ኪሶች እንደተመለከቱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ በማድረግ በትክክል ስለማብራራታቸው ይከታተሉ።

በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 2.3 የስሜት አካላት ጥቅም እንዲመለከቱ እና ሥዕሉ ምንን እንደሚገልፅ በመጠየቅ በገለጻ ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- አምስቱን የስሜት አካላትን የሚያሳይ ሥዕል
- የዓይን ሞዴል
- የዓይን ሥዕል

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (የዓይን ጥቅም)
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- እያሳዩ ማስተማር (Demonstration)

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ዓይን የሚገኝበትን የአካል ክፍል እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው
- ✓ ዓይን ምን ጥቅም እንዳለው መጠየቅ
- ✓ በዓይናቸው በመመልከት የኳስትን ቀለም እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ ዓይናቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

አፍንጫ

የትምህርቱ ጭብጥ

አፍንጫ ጠረን ወይንም ሽታ ያላቸውን ነገሮች ለማሽተት የምንጠቀምበት የስሜት አካል ነው። ተማሪዎች ነገሮችን በዓይን ሳያዩ በሽታቸው መለየት እንደሚችሉ ይረዳሉ። በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው መልካም መዓዛ ያላቸውንና መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች ለይተው ይመድባሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ስለአፍንጫ ጥቅም የሚያመለክት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል። ስለዚህ የተለያዩ የአፍንጫ ሞዴሎች፣ ሥዕሎች እና ስለአፍንጫ ጥቅም በተግባር ለማስተማር የተለያየ ጠረን ያለቸውን ነገሮች ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! የዕለቱን ትምህርት አፍንጫ ምን ጥቅም አለው ብለው በመጠየቅ ይጀምሩ።

ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በማቅረብ፡-

- ከአምስቱ የቡድን አባላት ሌላ አንድ አንድ ተማሪ በማሥነሳት በአፍንጫቸው ሰንደሉን ወይንም እጣኑንና ብርቱካኑን እንዲያሸቱ ካደረጉ በኋላ ምን ምን ነሮችን እንዳሸተቱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ በማድረግ በትክክል ስለማብራራታቸው ይከታተሉ፡፡

በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል እንዲመለከቱ እና ሥዕሉ ምንን እንደሚገልፅ በመጠየቅ በገለጻ ያጠቃልሉ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- አምስቱን የስሜት አካላትን የሚያሳይ ሥዕል
- የአፍንጫ ሞዴል
- የአፍንጫ ሥዕል

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (የአፍንጫ ጥቅም)
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- እያሳዩ ማስተማር

<u>የምዘናና የክትትል ስልቶች</u>

- ✓ አፍንጫ የሚገኝበትን የአካል ክፍል እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው
- ✓ አፍንጫ ምን ጥቅም እንዳለው መጠየቅ
- ✓ በአፍንጫቸው በማሽተት የፍራፍሬዎችን እና የሰንደልን ጠረን እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ አፍንጫቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

<u>ምላስ</u>

<u>የትምህርቱ ጭብጥ</u>

ምላስ የተለያዩ ነገሮችን ጣዕም የምንለይበት የስሜት አካል ነው፡፡ ነገሮችን በመቅመስ ጣፋጭ፣ መራራ፣ ጨዋማ፣ ኮምጣጣ እና የመሳሰሉት በማለት ጣዕማቸውን ይለያሉ፡፡ ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ህፃናት ስለሆኑ ያገኙትን ነገር በሙሉ መቅመስ እንደሌለባቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል::

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ስለምላስ ጥቅም የሚያመለክት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል። ስለዚህ የተለያዩ የምላስ ሞዴሎች፣ ሥዕሎች እና ስለምላስ ጥቅም በተግባር ለማስተማር የተለያየ ጠረን ያለቸውን ነገሮች ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! የዕለቱን ትምህርት ምላስ ምን ጥቅም አለው ብለው በመጠየቅ ይጀምሩ። ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በማቅረብ፡-

- ከአምስቱ የቡድን አባላት ሌላ አንድ አንድ በማሥነሳት ጨውን፣ ስኳሩን እና ሎሚውን በምላሳቸው ከቀመሱ በኋላ ጣዕማቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ በማድረግ በትክክል ስለማብራራታቸው ይከታተሉ።

በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል እንዲመለከቱ እና ሥዕሉ ምንን እንደሚገልፅ በመጠየቅ በገለጻ ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- አምስቱን የስሜት አካላትን የሚያሳይ ሥዕል
- የምላስ ሞዴል
- የምላስ ሥዕል

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- እያሳዩ ማስተማር
- የቡድን ውይይት (የምላስ ጥቅም)
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ምላስ የሚገኝበትን የአካል ክፍል እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው
- ✓ ምላስ ምን ጥቅም እንዳለው መጠየቅ
- ✓ በምላሳቸው በመቅመስ የሎሚን፣ የስኳርን እና የጨውን ጣዕም እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ ምላሳቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

ጆሮ

የትምህርቱ ጭብጥ

ጆሮ የተለያዩ ድምፆችን የምንለይበት የስሜት አካል ነው። ተማሪዎች ድምጽን በመስማት በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ምንነት ለምሳሌ፦ የእንስሳት፣ የሞተር፣ የሙዚቃ መሣርያ እና የመሳስሉትን ድምጻቸውን በመስማት መለየት ይችላሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ስለጆሮ ጥቅም የሚያመለክት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል። ስለዚህ የተለያዩ የጆሮ ሞዴሎች፣ ሥዕሎች እና ስለጆሮ ጥቅም በተግባር ለማስተማር የተለያየ ጠረን ያለቸውን ነገሮች ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! የዕለቱን ትምህርት ጆሮ ምን ጥቅም አለው ብለው በመጠየቅ ይጀምሩ። ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በማቅረብ፦

- ከአምስቱ የቡድን አባላት ሌላ አንድ አንድ የመጨረሻዎችን በማሥነሳት የውሻ፣ የድመት፣ የመኪና እና የመሳሰሉ ድምጾችን እንዲያሰሙ በማድረግ የክፍል ጓደኞቻቸው በጆሮዎቻቸው የምን የምን ድምጾች እንደተሰማቸው እንድናገሩ ያድርጓቸው።

በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል እንዲመለከቱ እና ሥዕሉ ምንን እንደሚገልፅ በመጠየቅ በገለጻ ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- አምስቱን የስሜት አካላትን የሚያሳይ ሥዕል
- የጆሮ ሞዴል
- የጆሮ ሥዕል

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- እያሳዩ ማስተማር
- የቡድን ውይይት (የጆሮ ጥቅም)
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ጆሮ የሚገኝበትን የአካል ክፍል እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው
- ✓ ጆሮ ምን ጥቅም እንዳለው መጠየቅ
- ✓ በጆሯቸው የውሻን፣ የድመትን እና የሙዚቃ መሣሪያን ድምፅ እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ ጆሯቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

ቆዳ

የትምህርቱ ጭብጥ

ከአምስቱ የስሜት አካላት መካከል ቆዳ አንዱ ሲሆን ነገሮችን በመዳሰስ የምንለይበት ውጫዊ የሰውነት ክፍል ነው። ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ቆዳቸውን በመጠቀም በተለይ በእጅ ጣቶች በመዳሰስ ነገሮችን ለስላሳ ወይም ሻካራ ብለው እንዲሁም በቆዳቸው አማካኝነት ቀዝቃዛና ሞቃት፣ ግፊትን፣ ንዝረትን ይለያሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ስለጆሮ ጥቅም የሚያመለክት መርጃ መሣሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅቦታል። ስለዚህ እንጨት፣ መስታወት፣ አፈር፣ አሸዋና ድንጋይ ለትምህርቱ ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! የዕለቱን ትምህርት ቆዳ ምን ጥቅም አለው ብለው በመጠየቅ ይጀምሩ። ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በማቅረብ፡-

- ከአምስቱ የቡድን አባላት ሌላ አንድ አንድ በማሥነሳት መስታወቱንና ድንጋዩን እንዲሁም አፈር እና አሸዋ በጣታቸው እንዲዳብሱ ካደረጉ በኋላ የቱ ሻካራ የትኛው ደግሞ ለስላሳ እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ በማድረግ በትክክል ስለማብራራታቸው ይከታተሉ።

በመጨረሻም በመጽሐፉ የተሰጡትን ጥያቄዎች በደብተሮቻቸው ሠርተው እንዲያመጡ ያድርጓቸው። በትክክል ስለመስራታቸው ካረጋገጡ በኋላ ስለ አምስቱ የስሜት አካላትና ተግባሮቻቸው የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን ጠይቀው በደንብ መገንዘባቸውን ካረጋገጡ በኋላ የትምህርቱን ይደምድሙ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ➢ አምስቱን የስሜት አካላት የሚያሳይ ሥዕል
- ➢ የዓይን፣ ምላስ፣ አፍንጫ እና ጆሮ ሞዴል
- ➢ የአምስቱን የስሜት አካላት ጥቅም የሚገልጽ ቻርት

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- እያሳዩ ማስተማር
- የቡድን ውይይት (የቆዳ ጥቅም)
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ቆዳ የሚገኝበትን የአካል ክፍል እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው
- ✓ ቆዳ ምን ጥቅም እንዳለው መጠየቅ
- ✓ በቆዳቸው የመስታወትን፣ የአፈርን እና የአሸዋ ልዩነት በዳስሳው እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ የስሜት አካላትን እንዴት እንደሚንከባከቡ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የውይይት ሁለት መልሶች

መምህር! ተማሪዎቹ ሥዕል 3 ተመልክተው መወያየታቸውን ለማረጋገጥ፡-

- ሥዕል ሀ እና ለ ዓይን ለማየት እንደሚጠቅም
- ሥዕል ሐ ጆሮ ለመስማት እንደሚጠቅም
- ሥዕል መ እና ሠ አፍንጫ ለማሽተት እንደሚጠቅም
- ሥዕል ረ እና ሰ ምላስ ለመቅመስ እንደጠጥቅም
- ሥዕል ሸ ደግሞ ቆዳ ለመዳሰስ እንደሚጠቅም የሚገልጹ ናቸው፡፡

የመልመጃ 2.1ለ መልሶች

እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት

2.2 የግል ንፅሕናን መጠበቅ

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 15

የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ የግል ንፅሕና በመረዳት ይተገብራሉ፡፡

የግል ንጽሕና

የትምህርቱ ጭብጥ

የግል ንፅሕና ማለት ዘወትር የሰውነታችንን እና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንፅሕና መጠበቅ ነው፡፡ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንን ንጽህና ለመጠበቅ፡-

- ዘወትር እጆቻችን፣ እግሮቻችን እና ፊታችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
- በየጊዜው ፀጉራችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብና ማበጠር
- ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀን ገላችንን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ
- ዘወትር የአፍንጫችን እና የጆሯችን ፅዳት መጠበቅ እና
- ጥፍሮቻችንን መቁረጥ ይኖርብናል፡፡

የግል ንጽህናን በአግባቡ አለመጠበቅ ለተለያዩ በሽታዎች ይዳርገናል፡፡ ከእኛ አልፎ አብረውን የሚውሉ፣ የሚጫወቱና የሚማሩ ጓደኞቻችንን ጤና ያውካል፡፡

ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃቸው የግል ንጽሕናቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው፣ የግል ንጽሕናን መጠበቅ ለምን እንደሚጠቅም፣ አለመጠበቅ ደግሞ በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ተረድተው የራሳቸውን ጤንነት ይጠብቃሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ይህን የትምህርት ንዑስ ርዕስ ለማስተማር መጀመሪያ የተለያዩ ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ዘዴን የሚያሳዩ ሥዕሎችን እንዲሁም ውሃ፣ ሳሙና እና የእጅ ማስታጠቢያ ያዘጋጁ፡፡ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁ ገለጻዎችን፣ ሥዕሎችንና የተግባር ሥራዎችን በደንብ በመመልከት ራስዎን ያዘጋጁ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ይህን የትምህርት ይዘት ከመጀርዎ አስቀድሞ ተማሪዎች ስለ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ቀድመው የተማሩትን እንድያብራሩ በማድረግ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም የግል ንጽህናን በተመለከተ ሥዕል 2.4 የግል ንጽሕና አጠባበቅ በአትኩሮት እንዲመለከቱና ከሥዕሉ የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እየተነሱ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

በመቀጠልም በመጽሐፉ ስለሚገኙት ሥዕሎች እና ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ንጽህና ለመጠበቅ ምን ምን ጥንቃቄዎችን ማድረግ እንደሚገባ ገለጻ ያድርጉላቸው።

ተማሪዎችን በተግባር ሁለት ላይ ያለውን በትምህርት ቤታቸው የሰልፍ ሥነ-ሥርዓት መርሃ-ግብር ላይ የእጅ ንፅሕና አጠባበቅን በተግባር እንዲያሳዩ ፕሮግራም በማዘጋጀት ውሃ፣ ሳሙናና የእጅ ማስታጠቢያ በመጠቀም ለሌሎች ጓደኞቻቸው ንጽሕና አጠባበቅን በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጓቸው።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ዘዴን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ
- ውሃ፣ ሳሙናና የእጅ ማስታጠቢያ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- ጥያቄና መልስ
- የተግባር ሥራ (የግል ንጽሕናን መጠበቅ)
- የቡድን ሥራ (የግል ንጽሕናን መጠበቅ ጠቀሜታ)

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ተማሪዎች ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ በተግባር ሲያሳዩ መከታተል።
- ✓ ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ የተለያዩ ሥዕሎችን እየተመለከቱ የተረዱትን እንዲናገሩ ይገምግሟቸው።
- ✓ የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ከራሳቸው አልፎ በጓደኞቻቸው ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መጠየቅ።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የተግባር ሁለት መልስ

- መምህር! ተማሪዎች በተያዘላቸው ፕሮግራም መሠረት በሰልፍ ሥነ-ሥርዓት ላይ የእጅ ንፅሕና አጠባበቅን መተግበራቸውን ይከታተሉ።

የመልመጃ 2.2 መልሶች

ሀ. የግለጹ መልሶች

1. ዘወትር እጆቻችን፣ እግሮቻችን እና ፊታችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ

   ቢያንስ በሳምንት ሁለት ቀን ገላችንን በውሃ እና በሳሙና መታጠብ

   በየጊዜው ፀጉራችን በውሃ እና በሳሙና መታጠብና ማበጠር

   ዘወትር የአፍንጫችን እና የጆሯችን ፅዳት መጠበቅ እና

   ጥፍራችን መቁረጥ ናቸው።

2. ለተለያዩ በሽታዎች እንጋለጣለን።

   ለሌሎች ሰዎች በሽታን እናስተላልፋለን።

   ሌሎች ሰዎች ደስተኛ ሆነው አይቀርቡንም።

2.3 የብርሃን ምንነት

ንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 15

የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- ✓ የጨለማን ምንነት ይገልፃሉ።

የትምህርቱ ጭብጥ

ብርሃን ነገሮችን ለማየት የሚረዳ የጉልበት ዓይነት ነው። ብርሃን ከሌለ ነገሮችን ማየት አንችልም። ስለዚህ አንድን ነገር በግልፅ ማየት የሚቻለው ብርሃን ሲኖር ብቻ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ጨለማ የብርሃን ጉልበት ሲያንስ ነገሮችን እንዳንመለከት የሚያደርግ ክስተት ነው።

ተማሪዎች ስለ ብርሃንና ጨለማ ክስተት ሁል ጊዜ ስለሚመለከቱ በዚህ የክፍል ደረጃቸው ብርሃን ምን እንደሆነና ከጨለማ ጋር ያለውን ልዩነት ለይተው ያስተውላሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የብርሃንና የጨለማን ምንነት እና ልዩነት ሊያሳዩ የሚችሉ ሥዕሎችን ለመርጃ መሣሪያ ያዘጋጁ።

ስለ ብርሃንና ጨለማ ልዩነት የሚያሳዩ ሥዕሎችንና ገለጻዎችን በደንብ አንብበው በመረዳት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ ጥያቄዎችን ቀድመው በመስራት እራስዎን ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! በመጀመሪያ ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በተገቢው ቦታ ካስቀመጡ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሥዕሎችን ለተማሪዎች በደንብ እንዲመለከቱ ይዘሏቸው። ተማሪዎችን ከሥዕል 2.5 የብርሃን እና ጨለማ ልዩነት ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው።

ተማሪዎችን አምስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ በማድረግ በመጽሐፉ ላይ የሚገኘውን የቡድን ውይይት ሦስት ስለ ብርሃንና ጨለማ ልዩነት የተጠየቁ ጥያቄዎችን ተወያይተው ተራ በተራ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እናዲናገሩ ያድርጓቸው።

በመቀጠልም ስለ ብርሃን ምንነት እና ጨለማ ምንነት እንዲሁም በመካከላቸው ስላለው ልዩነት በበቂ ሁኔታ ያስረዷቸው። ስለብርሃን እና ጨለማ ልዩነት የበለጠ ለተማሪዎቹ ግልፅ ለማድረግ በተግባር ሦስት ላይ የተሰጠውን ተግባራዊ ክንዋኔ ይዘሏቸው።

በመጨረሻም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን መልመጃ በደብተራቸው ጽፈው መልሶቻቸውን እንዲሰሩ ካደረጉ በኋላ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን ስለ ብርሃን እና ጨለማ ጠይቀው በደንብ መገንዘባቸውን ካረጋገጡ በኋላ ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የብርሃን እና የጨለማን ምንነት እና ልዩነት ሊያሳዩ የሚችሉ ሥዕሎች
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (የብርሃን እና የጨለማ ምንነት)
- የፅሁፍ ጥያቄ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ስለጨለማ ምንነት መጠየቅ።
- ✓ በብርሃንና ጨለማ ልዩነት ላይ ሲወያዩ ያላቸውን ግንዛቤ መገምገም።
- ✓ ለጥያቄዎች ከሚሰጡት መልስ በመነሣት ተገቢውን ግብረመልስ መስጠት።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የቡድን ውይይት ሦስት መልሶች

1. ብርሃን ነገሮችን ለማየት የሚያስችለን የጉልበት ዓይነት ነው።
2. ጨለማ የብርሃን ጉልበት ሲያንስ ነገሮችን እንዳናይ የሚያደርግ ክስተት ነው።
3. በብርሃን ነው።

የመልመጃ 2.3 መልሶች

እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ. እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

ለ. የአዛምድ መልሶች

1. ለ
2. መ
3. ሀ
4. ሠ
5. ሐ

ሐ. የምርጫ መልሶች

1. ሐ
2. ሐ
3. ለ
4. ሐ
5. ሀ

ምዕራፍ ሦስት

ተፈጥሮአዊ አካባቢ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 54

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የወቅቶችን፣ የቀንና የማታን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ቀስተ ደመናና ጎርፍ ተፈጥሮዊ ክስተቶች መሆናቸውን በማጥናት ይገነዘባሉ፡፡
- ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕርያት ይገልጻሉ፡፡
- ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ይዘረዝራሉ፡፡
- የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት ይጠቅሳሉ፡፡
- እንስሳትን በአካል ሽፋናቸው፣ በእንቅስቃሴያቸውና በእግራቸው ብዛት ይመድባሉ፡፡
- የቤት ውስጥ የንጽሕና ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመጸዳጃ ቤት ንጽሕና ይጠብቃሉ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

3.1 የአካባቢያችን የአየር ንብረት

3.2 ሕይወት ያላቸው ነገሮች

3.3 ንጽሕናና የግል ንጽሕና

3.1 የአካባቢያችን የአየር ንብረት

ለንዑስ ርዕሱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 20

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ የወቅቶችን፣ የቀንና የማታን ምንነት ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ቀስተ ደመናና ጎርፍ ተፈጥሮዊ ክስተቶች መሆናቸውን በማጥናት ይገነዘባሉ፡፡

ሀ. የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት

የትምህርቱ ጭብጥ

በምንኖርበት አካባቢ የተለያዩ የተፈጥሮ ክስተቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የፀሐይ ብርሃን፣ የሙቀት፣ የቅዝቃዜ፣ የነፋስ እና የዝናብ ክስተቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃቸው የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት የተለያዩ መሆናቸውን ተረድተው የአካባቢያቸውን የአየር ሁኔታ ፀሐያማ፣ ዝናባማ፣ ነፋሻማ፣ ደረቃማ፣ ሞቃታማ፣ ቀዝቃዛማ፣ ጭጋጋማ በማለት በየዕለቱ የገጠማቸውን የአየር ሁኔታ ይናገራሉ፡፡ የአየር ሁኔታ በየሰዓቱ፣ በየቀኑ፣ በየሳምንቱ በአጠቃላይ በአጭር ጊዜ የሚቀያየር የአየር ጠባይ ነው፡፡ ነገር ግን የአየር ንብረት ማለት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ በረዛማ ፣ደጋማ እና ቆላማ የአየር ንብረት መገለጫዎች ናቸው::

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱና በንቃት እንዲከታተሉ ለማድረግ የአየር ሁኔታን ፀሐያማ፣ ዝናባማ፣ ደረቃማ፣ ሞቃታማ እና ጭጋጋማ እንዲሁም የአየር ንብረትን በረዛማ ፣ደጋማ እና ቆላማ የሚያሳዩ ሥዕሎችን እንደመርጃ መሣሪያነት ያዘጋጁ፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስለ አየር ሁኔታ እና አየር ንብረት የሚገልጹ ሥዕሎችን፣ ገለጻዎችን እና የተሰጡ ጥያቄዎችን በሚገባ ተመልክተውና ተረድተው ራስዎን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ስለ አየር ሁኔታ እና አየር ንብረት በቀላሉ ለማስተማር እንዲረዳዎ በትምህርት ቤት እና በአካባቢው ያለውን አየር ንብረት እና ወቅታዊ የአየር ሁኔታ በመገንዘብ ለተማሪዎች ለማስረዳት ዝግጁ መሆን ይጠበቅቦዎታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ ይስቀሉት፤ ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፉን ገልጠው በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሥዕሎችን እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ስለ እያንዳንዱም ሥዕል 3.1 የአየር ሁኔታ እና ሥዕል 3.2 የአየር ንብረት በሚገባ ለተማሪዎች ገለጻ ካደረጉ በኋላ ተማሪዎችም ተራ በተራ እየተነሱ ከሥዕሉ የተረዱትን እንዲያሳዩና እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎችን ከክፍል ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት ምን ዓይነት የአየር ሁኔታ እንዳለ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

በተጨማሪም ያዘጋጁትን መርጃ መሣሪያ በመጠቀም ስለ አየር ንብረት ምንነት እና መገለጫዎች አጠር ያለ ገለጻ ያድርጉላቸው። በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ስለ አየር ንብረት መገለጫዎች የሚያሳየውን ሥዕል 3.2 የአየር ንብረት እንዲመለከቱ እና ከሥዕሉ ምን እንደተረዱ እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸውቸው።

ተማሪዎች አምስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ በማድረግ በመማሪያ መጽሐፋቸው የሚገኘውን ሥዕል 3.1 የአየር ሁኔታ እና ሥዕል 3.2 የአየር ንብረት በመመልከት የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ልዩነትን ተወያይተው ለክፍል ጓደኞቻቸው አጭር ገለጻ እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው። ተማሪዎች ያቀረቡት ገለጻ መነሻ በማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያ ያድርጉላቸው።

ተማሪዎች የግል ሥራ አንድን ማታ ቤታቸው ስለ አየር ሁኔታ የሚቀርበውን ዜና ተከታትለው በቤተሰቦቻቸው ድጋፍ የቀጣዩን ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ ጽፈው በመምጣት ለክፍል ጓዳኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። የአየር ሁኔታ ትንበያው ትክክል ስለ መሆኑ የቀኑን የአየር ሁኔታ ተከታትለው ለተማሪዎች በሚገባ ገለጻ ያድርጉላቸው። ተማሪዎች ይህን የግል ሥራ ሲያጠናቅቁ የአየር ሁኔታ ምንነት ይገነዘባሉ።

በመጨረሻም ስለ አየር ሁኔታ እና አየር ንብረት መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤ ለምሳሌ፦

- የአየር ሁኔታ ምንድ ነው? የአየር ንብረትስ?
- የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት መገለጫዎች ምንድን ናቸው? ብለው በመጠየቅ በደንብ መረዳታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ፀሐያማ፣ ዝናባማ እና ጭጋጋማ የአየር ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- በረሃማ፣ ደጋማ እና ቆላማ የአየር ንብረቶችን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የግል ሥራ (የአየር ሁኔታን መገንዘብ)
- የቡድን ውይይት (የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነትን መገንዘብ)
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ልዩነትን ይጠይቁ፡፡
- ✓ ስለ ቀጣይ ቀን የአየር ሁኔታ ጽፈው ካመጡ በኋላ ገለጻ ሲያደርጉ ያላቸውን ግንዛቤ መገምገም፡፡
- ✓ ከቡድን ውይይቱ ምን እንደጨበጡ በገለጻ መልክ እንዲናገሩ ይዘሏቸው፡፡
- ✓ ከሥዕሉ የተረዱትን እንዲናገሩ ይጠይቁ፡፡
- ✓ ለጥያቄዎች ከሚሰጡት መልስ በመነሣት ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት መማራቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ ያመላክቱ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የግል ሥራ አንድ መልስ

- መምህር! ተማሪዎች የቀጣዩን ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ ፅፈው መምጣታቸውን በማረጋገጥ ለክፍል ጓዳኞቻቸው ሲያቀርቡ ይገምግሙ፡፡

የቡድን ውይይት አንድ መልሶች

1. ፀሐያማ፣ ዝናባማ፣ ጭጋጋማ እና ነፋሻማ
2. በረሃማ፣ ደጋማ እና ቆላማ

የመልመጃ 3.1ሀ መልሶች

የምርጫ መልሶች

1. ሀ
2. ለ

ለ. የአየር ንብረት ይዘቶች

የትምህርቱ ጭብጥ

የአየር ግፊት፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የአየር እርጥበት እና የነፋስ ሁኔታ የመሳሰሉት ዋና ዋና የአየር ንብረት ይዘቶች ተብለው ይጠራሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የአየር ንብረት ይዘቶችን በደንብ ለይተው ይዘረዝራሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

የመማር ማስተማሩን ለማቀላጠፍና ተጨባጭ ለማድረግ እንዲሁም ተማሪዎች በቀላሉ ትምህርቱን እንዲረዱ ለማድረግ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያገለግል የሙቀት መጠን ካርታን በመጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሙቀት መጠን ልዩነት የሚያሳይ ሥዕል በማዘጋጀት ለተማሪዎች ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ ላይ መሰቀል ይኖርበታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች ስለ አየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ልዩነት የተማሩትን እንዲያስታውሱ የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ምንነትን እንዲሁም የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት መገለጫዎችን እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ የዕለቱን ክፍለ ጊዜ ትምህርት የአየር ንብረት ይዘቶች በማለት ያስተዋውቁ።

ተማሪዎች ስለ አየር ንብረት ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል ስለ አየር ንብረት ይዘት በደንብ ገለጻ በማድረግ ዋና ዋና የአየር ንብረት ይዘት የሚባሉትን ከዘረዘሩ በኋላ ተማሪዎች ስለ መረዳታቸው ለማወቅ እያንዳንዳቸው ተራ በተራ እየተነሱ የአየር ንብረት ይዘቶችን እንዲዘረዝሩና እንዲገልጹ ያድርጓቸው።

በመቀጠልም ተማርዎችን አምስት አባላት ያለው ቡድን እንዲመሰርቱ በማድረግ በተግባር አንድ ላይ ሥዕል 3.3 የኢትዮጵያ ሙቀት መጠን ካርታን በመመልከት ከካርታው ላይ የሙቀት መጠን ልዩነቱን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው።

በመጨረሻም ስለ የአየር ንብረት ይዘቶች ምን እንደተረዱ ለማወቅ ዋና ዋን የአየር ንብረት ይዘቶችን እንዲናገሩ የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሙቀት መጠን ልዩነት የሚያሳይ ሥዕል ወይንም ካርታ
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የተግባር ሥራ (ከሙቀት መጠን ካርታ ላይ የአየር ሙቀት መጠንን መግለፅ)
- ሰርቶ ማሳየት
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የአየር ንብረት ይዘቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ✓ እያንዳንዱን የአየር ንበረት ይዘቶች እንዲገልጹ መጠየቅ
- ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሙቀት መጠን ልዩነት የሚያሳይ ሥዕል ወይንም ካርታ እንዲመለከቱ እና ግብረ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

ሐ. የአየር ንብረት ክልሎች

የትምህርቱ ጭብጥ

ኢትዮጵያ አምስት ዋና ዋና የአየር ንብረት ክልሎች አሏት፡፡ እነዚህም፡- ውርጫማ፣ ደጋማ ፣ ወይናደጋ፣ ቆላማ እና በረሃማ የአየር ንብረት ክልሎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

- ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ3300 ሜትርና ከዚያ በላይ የሆኑ ስፍራዎች እና አማካይ የሙቀት መጠን ከ10 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታችና በጣም ቀዝቃዛ ሲሆን ውርጫማ የአየር ንብረት ክልል ይባላል፡፡
- ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ2300 - 3300 ሜትር የሆኑ እና መጠነኛ ቅዝቃዜ ያላቸው ስፍራዎች ደጋማ የአየር ንብረት ክልል ይባላል፡፡
- ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ1500 - 2300 ሜትር የሆኑና ብዙም ቀዝቃዛ ብዙም ሞቃት ያልሆኑ ስፍራዎች ወይናደጋ የአየር ንብረት ክልል ይባላል፡፡
- ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ500 - 1500 ሜትር እና አማካይ የሙቀት መጠን ከ20 - 30 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሆኑ እንዲሁም የዝናብ መጠኑ አነስተኛ ሆኖ ሞቃታማ የሆኑ ስፍራዎች ቆላማ የአየር ንብረት ክልል ይባላል፡፡
- ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ0 - 500 ሜትር እና አማካይ የሙቀት መጠን ከ30 - 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሆኑ እንዲሁም በጣም ደረቅ እና በጣም ሞቃታማ የሆኑ ስፍራዎች በረሃማ የአየር ንብረት ክልል በመባል ይታወቃሉ፡፡

በመሆኑም ከላይ የተገለፁትን የአየር ንብረት ክልሎች መነሻ በማድረግ ተማሪዎች የአካባቢቸውን የአየር ንብረት ክልል በየትኛው ምድብ ውስጥ እንደሚገኝ ማወቅ ይችላሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር ከመግባትዎ በፊት የአየር ንብረት ክልሎችን የሚያሳይ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ካርታ ማዘጋጀት ይጠበቅብዎታል፡፡ በመቀጠልም በመማሪያ መጽሐፉ የተጻፉትን ገለጻዎች እና የተሰጡትን ጥያቄዎች እንዲሁም የተግባር ሥራዎችን በሚገባ ተመልክተው ለማስተማር ይዘጋጁ፡፡

በተጨማሪም በሚያስተምሩበት አካባቢ ከባህር ጠለል በላይ ከፍታው እና አማካይ የሙቀት መጠኑን ለይተው በማወቅ የአየር ንብረት ክልሉ ከአምስቱ የኢትዮጵያ ዋና ዋና የአየር ንብረት ክልሎች በየትኛው እንደሚመደብ በማረጋገጥ ይዘጋጁ፡፡ እንዲሁም ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን በመጠቀም የዕለቱን አማካይ የሙቀት መጠን ማወቅ ይችላሉ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎች በዚህ የዕድሜ ክልላቸው ስለ አየር ንብረት ክልሎች ዕውቀት ላይኖራቸው ስለሚችል ትምህርቱን ሲጀምሩ ስለ አየር ንብረት ክልሎች የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን መልኩ በደንብ ገለጻ ያድርጉ፡፡ አምስቱን የኢትዮጵያ አየር ንብረት ክልሎችን ሥዕላዊ መግለጫን በመጠቀም ዘርዝረው ካስተማሩ በኋላ ትምህርቱን አሳታፊ ለማድረግ እና ተማሪዎች መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎችን በአምስት ቡድን በመመደብ አምስቱን የኢትዮጵያ አየር ንብረት ክልሎችን ዘርዝረው

እንዲናገሩ ያድርጓቸው። ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ እና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 3.3 የኢትዮጵያ አየር ንብረት ክልሎች በመጠቀም ስለ አምስቱ የኢትዮጵያ አየር ንብረት ክልሎች ተጨማሪ ገለጻ አድርገው ካርታውን እንዴት ማንበብ እና ከካርታው መረጃን እንዴት መመዝገብ እንዳለባቸው ያስተምሯቸው።

ተማሪዎችን በቡድን አምስት አምስት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ በተሰጠው የተግባር ሥራ ሁለት መሠረት እርጥበታማ እና ደረቃማ ክልሎችን ከካርታው አንብበውና መዝግበው እንዲሁም የአየር ንብረት ክልሎችን አወዳድረው እንዲያሳዩና ተራ በተራ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አድርገው በትክክል አንብበው ስለ መመዝገባቸው እና ማወዳደራቸው በደንብ ተከታትለው ያርሟቸው።

በተጨማሪም መጽሐፉ ላይ የተቀመጠውን የዝናብ ሥርጭት ካርታን በመጠቀም የዝናብ ሥር ጭት መጠን እንዲመዘግቡ ይዘሏቸው። የመዘገቡትንም መረጃ በመመልከት በትክክል ሰለመመዝገባቸው አረጋግጠው መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው።

በመጨረሻም ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው በመጠየቅ አካባቢያቸው ከአምስቱ የአየር ንብረት ክልሎች በየትኛው እንደሚመደብ ለክፍል ጓደኞቻቸው በትክክል መዝግበው እንዲያመጡ ይዘሏቸው። ያመጧቸውንም መልሶች ትክክል ስለመሆናቸው የአካባቢያቸው የአየር ንብረት ክልል ከአምስቱ በአንዱ መመደባቸውን አረጋግጠው ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- የኢትዮጵያን አየር ንብረት ክልሎችን የሚያሳይ የአየር ንብረት ካርታ
- የዝናብ ሥር ጭት መጠንን የሚያሳይ ካርታ
- ካርታውን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ
- የአየር ንብረት የሚገልጽ መተግበሪያ ያለው ዘመናዊ ስልክ

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የግል ሥራ (የአየር ንብረት ክልሎችን መለየት)
- የተግባር ሥራ (የአየር ንብረት ክልሎችን የዝናብ ሥር ጭት መጠኑን ከካርተው ላይ መመዝገብ)
- ሰርቶ ማሳየት
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የኢትዮጵያ አምስት ዋና ዋና የአየር ንብረት ክልሎች የሚባሉትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ
- ✓ እርጥበታማ እና ደረቃማ ክልሎችን ከካርታው አንብበውና መዝግበው ሲያሳዩ መከታተል
- ✓ የአየር ንብረት ክልሎችን ከካርታ አንብበው ሲያወዳድሩ መከታተል
- ✓ የዝናብ ሥር ጭት መጠንን ከካርታው ላይ አንብበውና መዝግበው ሲያሳዩ መከታተል
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የግል ሥራ ሁለት

- ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው በመጠየቅ የአካባቢያቸውን አየር ንብረት ክልሎች ከአምስቱ በየትኛው እንደሚመደብ ሲገልፁ በመከታተል መደምደም፡፡

ተግባር አንድ

- ተማሪዎች የአየር ንብረት ክልሎችን ከካርታው ላይ በትክክል መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር ሁለት

- ተማሪዎች የዝናብ ወቅቶችን በትክክል መመዝገባቸውን ያረጋግጡ፡፡

መ. አየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች

የትምህርቱ ጭብጥ

ከፍታ የአየር ንብረት እንዲለዋወጥ ተፅእኖ ከሚፈጥሩ ነገሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም ማለት ከፍታ ሲቀንስ አየሩ ይሞቃል ከፍታ ሲጨምር ደግሞ አየሩ ይቀዘቅዛል፡፡ ስለዚህ ከፍተኛ ሥፍራዎች ከፍተኛ የዝናብ መጠን እና ዝቅተኛ ሙቀት ሲኖራቸው ዝቅተኛ ሥፍራዎች ደግሞ አነስተኛ የዝናብ መጠን እና ከፍተኛ ሙቀት አላቸው፡፡

የዝናብ ሥር ጭት በአየር ንብረት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ሲሆን ይህም የዝናብ መጠን ከቦታ ቦታ እና ከወቅት ወቅት መለዋወጡ በአየር ንብረት ላይ ተፅእኖ እንዲያሳድር ያደርገዋል፡፡

ነፋስ እንደ ከፍታ እና የዝናብ ሥር ጭት የአየር ንብረት እንዲለዋወጥ ተፅእኖ የሚፈጠር ነው:: በክረምት ወቅት እርጥበት አዘል ንፋስ በደቡብ ምዕራብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ሲሆን ይህ ነፋስ ከፍተኛ ቦታ ላይ ሲደርስ ወደ ላይ ይነሳና ቀዝቅዞ እርጥበቱን በዝናብ መልክ ይዘንባል::

በመሆኑም ከፍታ፣ ነፋስ፣ እርጥበት፣ የፀሐይ ጨረር፣ የዝናብ ሥር ጭት፣ የደመና ሽፋን እና የመሳሰሉት የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ናቸው፡፡ የአየር ንብረት ይዘት መለኪያ መሣሪያዎች ዊንድ ቬን፣ ቴርሞሜትር፣ ሬንጌጅ እና አኒሞሜትር ናቸው፡፡

- ዊንድ ቬን የነፋስ አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ ነው፡፡
- ቴርሞሜትር የሙቀት መጠን መለኪያ መሣሪያ ነው፡፡

- ሬንጌጅ የዝናብ መጠን መለኪያ መሣሪያ ነው።
- አኒሞሜትር የነፋስ ፍጥነት መለኪያ መሣሪያ ነው።

በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ለይተው በመረዳት ይዘረዝሯቸዋል። የአየር ንብረት ይዘት መለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሙቀት እና የዝናብ መጠንን አንብበው መመዝገብ ይችላሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች እና የአየር ንብረት መለኪያ መሣሪያዎችን በማስመልከት በመጽሐፉ በተዘጋጀው መሠረት አንብበው ከተዘጋጁ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ የተግባር ሥራ ውጤቶቻቸውን በመመዝገብ ይዘጋጁ።

ትምህርቱን ተግባር ተኮር ለማድረግ የአየር ንብረት መለኪያ መሣርያዎችን የሚያሳይ ሥዕል በመርጃ መሣሪያነት እንዲሁም ቴርሞሜትርና ሬንጌጅ በማዘጋጀት ለማስተማር ይዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

ወደ ዋናው ትምህርት ከመግባትዎ በፊት የአየር ንብረት ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑ ተማሪዎቹን በመጠየቅ ስለ አየር ንብረት ይዘቶች ቀድመው የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው።

በመቀጠልም የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ምን ምን እንደሆኑ እያንዳንዳቸውን ዘርዝረው ያስተምሯቸው። ተማሪዎች ስለ የአየር ንብረት ተቆጣጣርዎች በሚገባ ለይተው እንዲረዱ ለማስቻል ቡድን መሥር ተው እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ የአየር ንብረት ተቆጣጣርዎችን ተራ በተራ እየተነሱ እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸው።

ስለ አየር ንብረት መለኪያ መሣሪያዎች ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያ በተገቢው ቦታ በመስቀልና ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘጋጀውን ሥዕል 3.4 የአየር ንብረት ይዘት መለኪያ መሣሪያዎች እንዲገልጡ በማድረግ እያንዳንዳቸውን መሣሪያዎች ምን ምን እንደሚባሉና ምን ለመለካት እንደሚያገለግሉ የመርጃ መሣሪያ እና ሥዕሉ ላይ እያመላከቱ ለተማሪዎች በደንብ ያስተምሯቸው። በመቀጠልም ተማሪዎች እያንዳንዳቸው ተራ በተራ እየተነሱ በመርጃ መሣሪያው ላይ የሚታዩትን መለኪያዎች እያንዳንዳቸውን እየጠቆሙ የመለኪያውን ስም እና ምን ለመለካት እንደሚጠቅም እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

በመቀጠልም ያዘጋጇቸውን ቴርሞሜትር እና ሬንጌጅ በክፍል ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲመለከተው በማድረግ እንዴት ከመለኪያዎቹ መረጃን እንደሚያነቡና እንደሚመዘግቡ ያሳዩዋቸው። ከዚያ ቀጥለው እንደ አየር ሁኔታው በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተሰጠው የተግባር ሥራ ሦስት ላይ አምስት አምስት በመሆን እንዲሰሩ ካደረጉ በኋላ በትክክል ስለ መስራታቸው ተከታትለው ያርሟቸው።

በመጨረሻም ትምህርቱን በደንብ ስለ መገንዘባቸው ለማወቅ የአየር ንብረት ተቆጣጣርዎችን እንዲዘረዝሩ እንዲሁም የአየር ንብረት መለኪያ መሣሪያዎችን እንዲዘረዝሩና ምን ምን ለመለካት እንደሚያገለግሉ የቃል ጥያቄዎችን ከጠየቁ በኋላ ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የአየር ንብረት መለኪያ መሣርያዎችን የሚያሳይ ሥዕል
- ሥዕሉን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ
- ቴርሞሜትር
- ሬንጌጅ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የተግባር ሥራ (የአየር ንብረት ይዘት መለኪያ መሣሪያዎችን መጠቀም)
- ሰርቶ ማሳየት
- የፅሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ከቴርሞሜትር እና ከሬንጌጅ መረጃን ሲያነቡና ሲመዘግቡ መከታተል
- ✓ በመርጃ መሣሪያው ላይ የሚታዩትን መለኪያዎች እየጠቆሙ የመለኪያውን ስም እና ምን ለመለካት እንደሚጠቅም ሲናገሩ መከታተል
- ✓ ስለአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ተወያይተው ሲዘርዝሩ መከታተል
- ✓ ለጥያቄዎች ከሚሰጡት መልስ በመነሣት ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት መማራቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ ማመላከት
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የተግባር ሶስት መልሶች

- መምህር! ተማሪዎቹ ከሬንጌጅ እና ቴርሞሜትር መሣሪያዎች ላይ የዝናብ እና የሙቀት መጠኑን በትክክል መለካታቸውን አረጋግጠው ውጤታቸውን ይገምግሙ።

የመልመጃ 3.1ለ መልሶች

የምርጫ መልሶች

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. ሀ

ቀንና ማታ

የትምህርቱ ጭብጥ

ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ የሆነና በተፈጥሮ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠር ክስተት የተፈጥሮ ክስተት ይባላል። ቀንና ማታ ተፈጥሯዊ ዑደትን የሚያሳይ የተፈጥሮ ክስተት ነው። አንድ ዕለት 24 ሰዓታት ሲኖሩት የፀሐይ ብርሃን ያለበት 12 ሰዓታት ቀን በመባል የሚታወቁ ሲሆን ቀሪው የፀሐይ ብርሃን የሌለበት 12 ሰዓታት ደግሞ ማታ እንደሚባል ተማሪዎች ለይተው ይገነዘባሉ። ተማሪዎች ዕለት ዕለት የሚገጥማቸውን በማስተዋል ለይተው በቀን ብርሃን፣ ሙቀት፣ ጫጫታና የመሳሰሉት በማታ ደግሞ ጨለማ፣ ቅዝቃዜ፣ ጸጥታና የመሳሰሉት ክስተቶች የሚስተዋሉ መሆኑን ይናገራሉ።

በተጨማሪም ፀሐይ በቀን የምትታይ ሲሆን ጨረቃና ከዋክብት ደግሞ በማታ የሚታዩ መሆናቸውን ይገነዘባሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ቀንና ማታን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ሊዘጋጁ ይገባል። በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ ገለጻዎችንና የተግባር ስራዎችን በመመልከት ተማሪዎችን ለማስተማር ይዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ስለ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ለተማሪዎች በደንብ አብራርተው ገለጻ ያድርጉላቸው። ቀንና ማታ ከተፈጥሮ ክስተቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ጠቅሰው በቀንና በማታ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገልጹ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ያዘጋጁትን መርጃ መሣሪያና በመጽሐፋቸው የቀንንና ማታን ልዩነት የሚያሳየውን ሥዕል 3.5 ፣ 3.6 በመጠቀም የቀንንና ማታን ልዩነት በደንብ ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው። ተማሪዎችን የቀንና ማታ ልዩነቶችን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን የግል ሥራ አንድ እና በግል ሥራው የሚገኘውን ሰንጠረዥ 1 የቀንና ማታ ልዩነት

እንዲሞሉ እያገዟቸው በትክክል መሙላታቸውን ተከታትለው ያርሟቸው።

በመጨረሻም ስለ ቀንና ማታ ልዩነት አጠር ያለ ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ቀንና ማታን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ - ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ

- የግል ሥራ
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የቀንና ማታ ምንነትን መጠየቅ
- ✓ ቀንንና ማታን ከሥዕሉ ተመልክተው እንዲለዩ ማድረግ
- ✓ የቀንና ማታ ልዩነት እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ✓ ሰጠረገፑን ሲሞሉ ያላቸውን መረዳት መገምገም
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የግል ሥራ አንድ መልሶች

ተ.ቁ	የቀንና ማታ ልዩነቶች	ቀን	ማታ
1	የፀሐይ ብርሃን አለ	✓	
2	የጨረቃ ብርሃን አለ		✓
3	ከዋክብት ይታያሉ		✓
4	ጫጫታ የበዛበት ነው	✓	
5	እንቅስቃሴ የበዛበት ነው	✓	
6	ጨለማ ነው		✓

ወቅቶች

የትምህርቱ ጭብጥ

በሀገራችን ኢትዮጵያ አራት የተለያዩ ወቅቶች አሉ፡፡ እነርሱም በጋ፣ ፀደይ፣ ክረምትና መኸር ናቸው፡ ፡ እነዚህ ወቅቶች አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሳይሆን ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚከሰቱ ናቸው፡፡ ከአራቱ ወቅቶች በጋና ክረምት ጎልተው የሚታዩ ሲሆን በበጋ ወቅት ደረቅና ሞቃታማ የአየር ጠባይ ዝቅተኛ የዝናብ መጠን የሚኖር ሲሆን በክረምት ወቅት ደግሞ ቀዝቃዛ የአየር ጠባይና ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚታይበት ወቅት መሆኑን ለይተው ይገነዘባሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ወቅቶችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ ገለጻዎችንና የተግባር ስራዎችን በመመልከት ተማሪዎችን ለማስተማር ይዘጋጁ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት ስለ ቀንና ማታ በቃል ጥያቄ ክለሳ ካደረጉ በኋላ የዕለቱን ትምህርት ወቅቶች በማለት ያስተዋውቁ፡፡ በመቀጠልም ስለ ወቅት ምንነት እና በሀገራችን ስለሚከሰቱ አራቱ

ወቅቶች ዘርዝረው ለተማሪዎች ገለጻ ያድርጉላቸው። ተማሪዎች ስለ ወቅቶች በደንብ እንዲረዱ ለማድረግ ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በማዘጋጀት አራቱን የኢትዮጵያ ወቅቶች ዘርዝረው እንዲወያዩባቸውና ተራ በተራ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። በመማሪያ መጽሐፉ ስለሚገኙት ሥዕሎች ለተማሪዎች በደንብ ገለጻ ካደረጉ በኋላ የግል ሥራ ሁለትን መሠረት በማድረግ በቡድናቸው ከአራቱ ወቅቶች ውስጥ የበጋን እና የክረምትን ልዩነቶች ጽፈው ከተወያዩባቸው በኋላ በየግላቸው ሰንጠረዥ 2 የወቅቶች ልዩነት እንዲሞሉ ያድርጓቸው። በትክክል ተወያይተው ሰነጠረዡን መሙላታቸውን ተመልክተው እርማት ይስጧቸውቸው። ተማሪዎች ከአራቱ ወቅቶች ውስጥ አሁን የሚገኙበትን ወቅት ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው በመምጣት ተራ በተራ ክፍል ዉስጥ እንዲናገሩ በማድረግ ትክክለኛውን የሚገኙበትን ወቅትና መገለጫ ባህሪያቱን ያብራሩላቸው።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ወቅቶችን የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ወቅቶችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (አራቱ ወቅቶች)
- አራቱን ወቅቶች የሚገልጽ ቻርት
- የፅሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የወቅት ምንነትን መጠየቅ
- ✓ አራቱን የኢትዮጵያ ወቅቶች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ
- ✓ የክረምትና በጋ ወቅቶች ልዩነቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የግል ሥራ ሁለት መልሶች

ተ.ቁ	ወቅቶች	
	ክረምት	በጋ
1	ዘር ይዘራል	እህል ይሰበሰባል
2	ወንዞች ይሞላሉ	ወንዞች ይጎድላሉ
3	ዝናብ በብዛት ይዘንባል	ዝናብ ብዙም አይዘንብም
4	አየሩ ይቀዘቅዛል	አየሩ ይሞቃል
5	በአብዛኛው ጎርፍ ይከሰታል	ጎርፍ የመከሰት እድሉ ዝቅተኛ ነው

ቀስተ ደመና

የትምህርቱ ጭብጥ

ቀስተ ደመና አልፎ አልፎ የሚከሰት የተፈጥሮ ክስተት ነው። ቀስተ ደመና የሚከሰተው የፀሐይ ብርሃን በዝናብ ጠብታዎች ውስጥ ሲያልፍ ነው። ተማሪዎች ቀስተ ደመና ሰባት የተለያዩ ቀለማት እንዳሉት ይገነዘባሉ። እነርሱም በቅደም ተከተል፦ ቀይ፣ ብርቱካንማ፣ ቢጫ፣ አርንጓደ፣ ሰማያዊ፣ ሃምራዊና ወይን ጠጅ ናቸው።

ቅድመ ዝግጅት

ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ቀስተ ደመናን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ሊዘጋጁ ይገባል። በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ የተሰጡ ገለጻዎችንና የግል ሥራዎችን በመመልከት ተማሪዎችን ለማስተማር ዝግጅት ያድርጉ።

የትምህርቱ አቀራረብ

የቀስተ ደመናን ምንነትና ስንት ቀለማት እንዳሉት እንዲናገሩ በመጠየቅ ስለ ቀስተ ደመና ምንነትና ስለሚታዩት ቀለማት ያዘጋጁትን የመርጃ መሣሪያና መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 3.9 ቀስተ ደመና በመጠቀም በቅደም ተከተላቸው መሠረት የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን ሁኔታ ገለጻ ያድርጉላቸው። ትምህርቱን አሳታፊ ለማድረግ ጥንድ ጥንድ በማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተሰጠውን የቡድን ውይይት አንድ በቡድን በማደራጀት እንዲሠሩ ያድርጓቸው። በቡድን የሠሯቸውን ጥያቄዎች መልሶቻቸው ትክክል መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ እርማት ይስጧቸው።

በመጨረሻም ተማሪዎችን የተለያዩ እርሳሶችን በመጠቀም የቀስተ ደመና ሥዕል ሥለው እንዲያመጡ በማዘዝ፤ ሥለው ያመጡትን የቀስተ ደመና ሥዕሎች ተመልክተው ይገምግሙላቸው።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ቀስተ ደመና የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ቀስተ ደመና የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (የቀስተ ደመና ምንነት)
- የቀስተ ደመናን ክስተት የሚገልጽ ቻርት
- የፅሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የቀስተ ደመና ምንነትን መጠየቅ
- ✓ ቀስተ ደመና እንዴት እንደመከሰት ይጠይቋቸው
- ✓ የቀስተ ደመናን ቀለማት እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

ጎርፍ

የትምህርቱ ጭብጥ

ጎርፍ አልፎ አልፎ የሚከሰት የተፈጥሮ ክስተት ሲሆን የሚከሰተውም ከመጠን በላይ የሆነ ዝናብ በተከታታይ በአንድ አካባቢ ሲዘንብ ነው፡፡ ጎርፍ በሰዎች፣ በእንስሳትና እፅዋት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ክስተት ነው፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ጎርፍ ያስከተላቸውን ጉዳቶች የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ፖስተሮችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎችን ጎርፍ መቼ እንደሚከሰት በመጠየቅ እና ምን ምን ጉዳት እንደሚያስከትል እንዲያብራሩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ስለጎርፍ ምንነትና ስለሚያስከትለው ጉዳት ያሉበትን የክፍል ደረጃ መሠረት በማድረግ በሚገባ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም ያዘጋጁትን መርጃ መሣሪያና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን ሥዕል 3.10 ጎርፍ ተማሪዎች እንዲወያዩባቸውና ስለጎርፍ ምንነትና ሚያስከትለውን ጉዳት እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተሰጡትን የመልመጃ ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ከሠሩ በኋላ ስለ ትምህርቱ ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ የቃል ጥያቄዎችን ጠይቀው ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ጎርፍ ያስከተላቸውን ጉዳቶች የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ፎቶ ግራፎችና ሥዕሎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ የጎርፍን ምንነት መጠየቅ
- ✓ ጎርፍ መቼ እንደሚከሰት እንዲገልጹ መጠየቅ
- ✓ ጎርፍ ምን ጉዳት እንዳለው እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የመልመጃ 3.1ሐ መልሶች

የአዛምድ መልሶች

1. ሀ
2. መ
3. ለ
4. ሐ

3.2 ሕይወት ያላቸው ነገሮች

ለንዑስ ርዕስ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት - 24

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕሪያት ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ይለያሉ፡፡
- ✓ እንስሳትን በአካል ሽፋናቸው፣ በእንቅስቃሴያቸውና በእግራቸው ብዛት ይመድባሉ፡፡
- ✓ የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት ይለያሉ፡፡

ሀ. ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባህሪያት

የትምህርቱ ጭብጥ

ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነርሱም እንስሳት እና እፅዋት ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 1 የእንስሳት እና የእፅዋት ልዩነት

ተ.ቁ	እንስሳት	እፅዋት
1	ምግባቸውን አያዘጋጁም	ምግባቸውን ያዘጋጃሉ
2	ይንቀሳቀሳሉ	አይንቀሳቀሱም
3	ድምፅ አላቸው	ድምፅ የላቸውም

ስለዚህ እንስሳት እና እፅዋት የጋራ የሆነ ተመሳሳይ ባህሪያት እንዳላቸው ሁሉ ከላይ በተጠቀሱት ባህሪያት ደግሞ ይለያያሉ፡፡

ሕይወት ያለቸው ነገሮች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡፡

1. አየር ያስፈልጋቸዋል (ይተነፍሳሉ)፡- እንስሳት ንፁህ አየር ወደ ውስጥ በመሳብ የተቃጠለ አየር ያስወጣሉ፤ እንደዚሁም እፅዋት ምግባቸውን ለማዘጋጀት አየር ያስፈልጋቸዋል፡፡

2. ምግብ/ ጉልበት ያስፈልጋቸዋል፡- እንስሳት የተለየዩ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ጉልበት ከምግብ ያገኛሉ፤ እፅዋት ግን የራሳቸውን ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡

3. ስሜት አላቸው፡- እንስሳት በቁጣ፣ በጩኸት፣ በደንጋጤ ስሜታቸውን ይገልጻሉ፡፡ እፅዋትም ለፀሐይ ብርሃን ምላሽ በመስጥት ይኮማተራሉ፣ ውሃ ሲያጡ ይጠወልጋሉ፡፡

4. ይንቀሳቀሳሉ፡- እንሰሳት ከቦታ ቦታ ምግባቸውን ፍለጋ ይንቀሳቀሳሉ፤ ነገር ግን እፅዋት ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀሱም፡፡

5. ያድጋሉ፡- ሕይወት ያላቸው ነገሮች በመጠን የሚያሳዩት ለውጥ ዕድገት ይባላል፡፡

6. ይራባሉ፡-ሕይወት ያላቸው ነገሮች መሰሎቻቸውን በመተካት ቁጥራቸውን የሚጨምሩበት ሂድት መራባት ይባላል፡፡

7. ይጸዳዳሉ፡-ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከአካላቸው ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን የሚያስወግዱበት ሂደት መጸዳዳት ይባላል፡፡

ሕይወት የሌላቸው እና ያላቸው ነገሮች ተመሳሳይ ባህሪይ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አያድጉም፣ አይተነፍሱም፣ አይራቡም፣ አይንቃሳቀሱም እና ምግብ አያስፈልጋቸውም፡፡

ቅድመ ዝግጅት

የተለያዩ ሕይውት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮች ለማስገንዘብ ለመርጃ መሣሪያ ሞዴሎች፣ ፎቶዎችንና ሥዕሎችን ማዘጋጀት ይጠበቅበዎታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች በዚህ ክፍል ደረጃቸው ሕይወት ስላላቸውና ሕይወት ስሌላቸው ነገሮች ባህርያት እውቀት ስለማይኖራቸው ቀድመው ህይወት ስላላቸውና ህይወት ስሌለላቸው ነገሮች ባህርያት ግልጽ አድርገው ያብራሩላቸው። በመቀጠልም ተማሪዎችን ጥንድ ጥንድ እንዲሆኑ በማዘዝ ሕይወት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮችን ሥዕሉን በመመልከት እንዲዘረዝሩ አድርገው በመከታተል ስተቶቻቸውን ያርሟቸው።

በመቀጠል ያዘጋጁትን የእንስሳት እና እጽዋት ፎቶዎችና ሥዕሎች እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን ሥዕል 3.11 ሕይወት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮች በመጠቀም ልዩነታቸው ላይ በቂ የሆነ ማብራሪያ ይስጧቸው። በማያያዝም ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ባህሪያትን በመጥቀስ እና ምሳሌዎችን በመስጠት ሕይወት ካሏቸው ነገሮች የሚለያዩባቸውን ነገሮች በመዘርዘር ይግለጹላቸው፡ ፡ ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እንዲሆኑ በማድረግ የቡድን ሥራ አንድ ላይ የሚገኙትን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሠርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው። በትክክል ማቅረባቸውን ተከታትለው ያርሟቸው።

1) ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።

2) ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።

መምህር! በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን የቡድን ሥራ እያንዳንዱ ተማሪ መልሱን ጽፎ ካመጣ በኋላ አምስት አምስት ቡድን በማዘጋጀት በመልሶቻቸው ከተወያዩ በኋላ ከቡድኑ አንድ አንድ ተማሪ እየተነሳ እንዲያቀርብ ያድርጉ።

በመጨረሻም ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ሕይወት ስላላቸው ነገሮች ባህሪያት፣ ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ምሳሌ እንዲሰጡ እንዲሁም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ምን ምን በመባል ለሁለት እንደሚመደቡ የቃል ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ቻርቶች፣ ፎቶ ግራፎችና ሥዕሎች
- የእንስሳትና እጽዋት ሞዴሎች፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ፎቶ ግራፎችና ሥዕሎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ሥራ (ሕይወት ያላቸው እና የሌላቸውን መለየት)
- የዕሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ምን ዓይነት ባህሪያት እንዳላቸው ሲወያዩ ያላቸውን ግንዛቤ መገምገም
- ✓ ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ለይተው እንዲዘረዝሩ መጠየቅ
- ✓ ሥዕሉን በመመልከት ሕይወት ያላቸው ነገሮችን እንስሳት እና እጽዋት በማለት ሲመድቡ መከታተል
- ✓ የእንስሳትን እና እፅዋትን ልዩነት መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የቡድን ሥራ አንድ መልሶች

1. እንስሳት እና እፅዋት
2. አለት፣ ውሃ፣ አፈር፣ አሸዋ፣ ማዕድናት (ብረት፣ ወርቅ፣ ብር...) ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

የቡድን ሥራ ሁለት መልሶች

1. እንስሳት፡- አንባሳ፣ ቀጭኔ፣ ዝሆን፣ በሬ፣ ፍየል፣ ድብ፣ ጅብ ወ.ዘ.ተ. ናቸው።
2. እፅዋት፡- ዋንዛ፣ ዝግባ፣ ሳር፣ ብሳና፣ ቀርከሃ፣ ጥቁር እንጨት ወ.ዘ.ተ. ናቸው።
3. የእንስሳት እና የእፅዋት መሠረታዊ ልዩነት እንስሳት ምግባቸውን ማዘጋጀት የማይችሉ ሲሆን እፅዋት ግን የራሳቸውን ምግብ ማዘጋጀት መቻላቸው ነው። በተጨመሪም እንስሳት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችሉ ሲሆን እፅዋት ግን ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አይችሉም።

የመልመጃ 3.2ሀ መልሶች

የምርጫ መልሶች

1. ሀ
2. ሀ
3. ሐ

ለ. የእንስሳት ምድብ

የትምህርቱ ጭብጥ

እንስሳት ሕይወት ካላቸው ነገሮች የሚመደቡ ሲሆን በአረባባቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካላቸው ሽፋን እና በእንቅስቃሴያቸው ይመደባሉ። በአጠቃላይ እንስሳት፡-

1. በአረባባቸው፡- መሰሎቻቸውን በመውለድ እና እንቁላል በመጣል የሚራቡ ተብለው ይመደባሉ።
2. በእግራቸው ብዛት፡- አራት እግር ያላቸው፣ ሁለት እግር ያላቸው እና እግር የሌላቸው እንስሳት ተብለው ይመደባሉ።

3. <u>በመኖሪያ ስፍራቸው፡-</u> በመሬት ላይ የሚኖሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እና በመሬትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ተብለው ይመደባሉ።

4. <u>በአካላቸው ሽፋን፡-</u> በፀጉር የተሸፈኑ፣ በላባ የተሸፈኑ እና በቅርፊት የተሸፈኑ እንስሳት ተባለው ይመደባሉ።

5. <u>በእንቅስቃሴያቸው፡-</u> በእግራቸው የሚራመዱ፣ በመሬት ላይ የሚሳቡ፣ በሰማይ ላይ የሚበሩ እና በውሃ ውስጥ የሚዋኙ እንስሳት በመባል ይመደባሉ።

በመሆኑም ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሳትን በአረባባቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካላቸው ሽፋን እና በእንቅስቃሴያቸው ዘርዝረው ይመድቧቸዋል።

<u>ቅድመ ዝግጅት</u>

መምህር! የእንስሳትን ምድብ ለማስገንዘብ ይረዳዎት ዘንድ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተዘረዘረው መሠረት ምድባቸውን በመመልከት ይዘጋጁ። ትምህርቱን ለተማሪዎች ግልጽ አድርገው ለማስረዳትና በቀላሉ እንዲረዱት ለመድረግ የእንስሳትን የአረባብ መንገድ፣ የእግር ብዛት፣ የአካል ሽፋን፣ የመኖሪያ ስፍራ እና እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳዩ ቻርቶችን፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን፣ ፎቶዎችን እና ሥዕሎችን እንደመርጃ መሣሪያነት ያዘጋጁ።

<u>የትምህርቱ አቀራረብ</u>

መምህር! ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሳት እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ እና በየትኛው ሊመደቡ እንደሚችሉ ይንገሯቸው። በመቀጠልም ያዘጋጁትን መርጃ መሣሪያ በተገቢው ቦታ በመስቀል ተማሪዎችም መማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ የሚገኘውን ሥዕል 3.12 የእንስሳት አረባብ እንዲመለከቱ በማድረግ በአረባባቸው መሰሎቻቸውን በመውለድ የሚራቡ እና እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት የትኞች እንደሆኑ ከሥዕሉ በመዘርዘር ያስረዷቸው። በመቀጠልም ተማሪዎች ተራበተራ እየተነሱ ከተሰቀለው የመርጃ መሣሪያ ላይ መሰሎቻቸውን በመውለድና እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳትን ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጓቸው። በአካባቢቸው ከሚገኙ መሰሎቻቸውን በመውለድና እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳትን ለይተው በጽሑፍ እንዲያመጡ ካደረጉ በኋላ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። ትክክል ስለመሆናቸውም በሚከተለው መንገድ ያረጋግጡላቸው።

1. መሰሎቻቸውን በመውለድ የሚራቡ እንስሳት ለምሳሌ፡- ዝሆን፣ የሌሊት ወፍ፣ ቀጭኔ፣ ድመት፣ አህያ፣ ፈረስ፣ ግመል እና የመሳሰሉት ናቸው።

2. እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት ለምሳሌ፡- ኤሊ፣ እባብ፣ ዓሳ፣ ዶሮ፣ አዞ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ተማሪዎችን ሁለት እግር ያላቸው እንስሳት፣ አራት እግር ያላቸው እንስሳት እና እግር የሌላቸውን እንስሳት ተራ በተራ እንዲዘረዝሩ በመጠየቅ እንስሳቱ ባላቸው የእግር ብዛት በምን በምን እንደሚመደቡ ዘርዝረው ይግለጹላቸው። የተዘጋጀውን መርጃ መሣሪያና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን ሥዕል እንዲመለከቱ በማድረግ ተማሪዎችን ሥዕል 3.13 የተለያየ የእግር ብዛት ያላቸው እንስሳት ላይ የተመለከቷቸውን እንስሳት በእግራቸው ብዛት ሁለት እግር ያላቸው፣ አራት እግር ያላቸው እና እግር የሌላቸው በማለት እንዲመድቡ ያድርጓቸው።

ትክክል ስለመሆናቸውም በሚከተለው መንገድ ያረጋግጡላቸው፡፡

1. አራት እግር ያላቸው እንስሳት ለምሳሌ፡- ነብር፣ ከርከሮ፣ አሳማ፣ ጉማሬ፣ በግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. ሁለት እግር ያላቸው እንስሳት ለምሳሌ፡- ዳክዬ፣ ሰጎን፣ ዶሮ፣ እርግብ፣ ጨሉሌ፣ በቀቀን እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. እግር የሌላቸው እንስሳት ለምሳሌ፡- እባብን እና ዘንዶን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ተማሪዎችን እንስሳት የት የት ሊኖሩ እንደሚችሉ በመጠየቅ እንስሳትን በመኖሪያ ስፍራቸው በመሬት ላይ የሚኖሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት እና በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውን ሥዕል 3.14 የእንስሳት አኗኗር ላይ የሚገኙትንና ተጨማሪ ምሳሌዎችን ዘርዝረው ለተማሪዎች ግልፅ አድርገው ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም ትምህርቱን በደንብ እንዲረዱት ተጨማሪ በአካባቢያቸው የሚገኙ ሌሎች እንስሳትን ፅፈው እንዲያመጡ በማድረግ ሦስት ሦስት በመሆን የፃፏቸውን እንስሳት በመኖሪያ ስፍራቸው ከላይ በተማሩት መሠረት በመሬት ላይ የሚኖሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት እና በመሬትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ በማለት እንዲመድቡ በማድረግ እንዲያቀረቡ ያድርጓቸው፡፡ ትክክል ስለመሆናቸውም በሚከተለው መንገድ ያረጋግጡላቸው፡፡

1. በመሬት ላይ የሚኖሩ እንስሳት ለምሳሌ፡- አንበሳ፣ አቦሸማኔ፣ በቅሎ፣ ጅብ፣ ፍየል እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ለምሳሌ፡- የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎች (ዶልፊን፣ ሻርክ፣ ዓሳ እና ዓሳ ነባሪ) መጥቀስ ይቻላል፡፡

3. በመሬት ላይና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ለምሳሌ፡- አዞ፣ ጉማሬ፣ እንቁራሪት፣ ጉርጥ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የተዘጋጀውን መርጃ መሣሪያ ለሁሉም በሚታይ ቦታ በመስቀልና ሥዕሎችን ከመጽሐፋቸው እንዲመለከቱ በማድረግ ሥዕል 3.15 የተለያየ የአካል ሽፋን ያላቸው እንስሳት የሚመለከቷቸውን እንስሳት በፀጉር የተሸፈኑ፣ በላባ የተሸፈኑ እና በቅርፊት የተሸፈኑ እንስሳትን ደብተራቸው ላይ ለያይተው እንዲፅፉ ይዘሏቸው፡፡ ትክክል ስለመሆናቸውም በሚከተለው መንገድ ያረጋግጡላቸው፡፡

1. አካላቸው በፀጉር የተሸፈኑ እንስሳት ለምሳሌ፡- የሜዳ አህያ፣ ሽኮኮ፣ በሬ፣ በግ፣ ውሻ፣ አንበሳ፣ ድብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2. አካላቸው በላባ የተሸፈኑ እንስሳት ለምሳሌ፡- ጥንብ አንሳ፣ ጭልፋት፣ ንሥር ፣ ቁራ፣ ሰጎን እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. አካላቸው በቅርፊት የተሸፈኑ እንስሳት ለምሳሌ፡- የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎች፣ አዞ፣ እንሽላሊት፣ ዘንዶ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ተማሪዎችን በእግራቸው የሚራመዱ ፣በመሬት ላይ የሚሳቡ፣ በሰማይ ላይ የሚበሩ እና በውሃ ውስጥ የሚዋኙ እንስሳትን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው፡፡ ተራ በተራ እንዲዘረዘሩ ዕድል ከሰጧቸው በኋላ እንስሳት በእግራቸው የሚራመዱ፤ በመሬት ላይ የሚሳቡ፤ በሰማይ ላይ የሚበሩ እና በውሃ ውስጥ የሚዋኙ ተብለው በእንቅስቃሴያቸው በአራት እንደሚመደቡ ሥዕል 3.16 የእንስሳት እንቅስቃሴ

እና ምሳሌዎችን በመጥቀስ ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም ተማሪዎች በደንብ እንዲለዩአቸው ጥንድ ጥንድ በመሆን በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እንስሳት በመዘርዘር በእንቅስቃሴያቸው በአራት ምድቦች መድበው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። ትክክል መሆናቸውንም በሚከተለው መንገድ ያረጋግጡላቸው።

1. በእግራቸው የሚራመዱ እንስሳት ለምሳሌ፡- ጥንቸል፣ ሰጎን፣ ሽኮኮ፣ ሚዳቋ፣ ቀርኬ፣ ድኩላ እና የመሳሰሉት ናቸው።
2. በመሬት ላይ የሚሳቡ እንስሳት ለምሰሌ፡- አዞ፣ ኤሊ፣ እባብ እና የመሳሰሉት ናቸው።
3. በሰማይ ላይ የሚበሩ እንስሳት ለምሳሌ፡- ቁራ፣ ጭልፊት፣ የሌሊት ወፍ፣ ድንቢጥ፣ እርግብ፣ ጥንብ አንሳ እና የመሳሰሉት ናቸው።
4. በውሃ ውስጥ የሚዋኙ እንስሳት ለምሳሌ፡- የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎች (ዶልፊን፣ ሻርክ፣ ዓሳ እና ዓሳ ነባሪ) መጥቀስ ይቻላል።

በመጨረሻም ትምህርቱን በደንብ መረዳታቸውን ለማወቅ ስለእንስሳት ምድብ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን ለምሳሌ፡-

- እንስሳት በአረባባቸው ምን ምን ተብለው ይመደባሉ?
- እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት እነማን ናቸው?
- እንስሳት በአካል ሽፋናቸው በምን በምን ይመደባሉ?
- በቅርፊት የተሸፈኑ እንስሳት እነማን ናቸው? እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- መሰሎቻቸውን በመውለድ እና እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳትን የሚያሳዩ ፎቶዎችና ሥዕሎች
- አራት እግር ያላቸው፣ ሁለት እግር ያላቸው እና እግር የሌላቸውን እንስሳትን የሚያሳዩ ፎቶዎችና ሥዕሎች
- በመሬት ላይ፣ በውሃ ውስጥ እና በመሬትና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትን የሚያሳዩ ፎቶዎችና ሥዕሎች፤
- አካላቸው በፀጉር የተሸፈኑ፣ በላባ የተሸፈኑ እና በቅርፊት የተሸፈኑ እንስሳትን የሚያሳዩ ፎቶዎችና ሥዕሎች
- በእግራቸው የሚራመዱ፣ በመሬት ላይ የሚሳቡ፣ በሰማይ ላይ የሚበሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚዋኙ እንስሳትን የሚያሳዩ ፎቶዎችና ሥዕሎች
- ሥዕሎችን ለማሳየት የሚያስችል መጠቆሚያ ዘንግ
- ተንቀሳቃሽ ምስሎች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- ሰርቶ ማሳየት
- የፅሁፍ ጥያቄ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ እንስሳት በአረባባቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካላቸው ሽፋን እና በእንቅስቃሴያቸው ሲመድቧቸው ያላቸውን ግንዛቤ መገምገም
- ✓ ሥዕሎችን ወይንም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመመልከት በአረባባቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካላቸው ሽፋን እና በእንቅስቃሴያቸው እንስሳትን ለይተው ማሳየታቸውን መከታተል
- ✓ በአረባባቸው፣ በእግራቸው ብዛት፣ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካላቸው ሽፋን እና በእንቅስቃሴያቸው የተመደቡ እንስሳት እነማን እንደሆኑ እንዲጠቅሱ መጠየቅ
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 3.2ለ መልሶች

ሀ. እውነት/ሐሰት መልሶች

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

ለ. የምርጫ መልሶች

1. ሀ
2. ለ
3. ለ
4. ሀ
5. ሐ

የለማዳ እንስሳት አገልግሎት

የይዘቱ ጭብጥ

ለማዳ እንስሳት ከሰው ልጆች ጋር ተላምደው የሚኖሩ እንስሳት ናቸው። ለማዳ እንስሳት ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣሉ። ከእነዚህም መካከል ለምግብነት፣ ለወተት፣ ለልብስ መሥሪያነት፣ ለመጓጓዣነት፣ ለመዝናኛነት እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ይውላሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ስለ ለማዳ እንስሳት አገልግሎት ለማስተማር የመርጃ መሣሪያነት ከሚጠቀሟቸው ነገሮች መካከል የተለያዩ የለማዳ እንስሳት ሥዕል፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች እና ቻርቶች ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች ከዚህ በፊት የተማሩትን መሠረት አድርገው ለማዳ እንስሳትን እንዲዘረዝሩ ለመንደርደሪያነት ይጠይቋቸው። በመቀጠልም እነዚህን እንስሳት ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በመጠየቅ እንዲሳተፉ ያድርጉ። በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን የለማዳ እንስሳት ሥዕል 3.17 የለማዳ እንስሳት አገልግሎት አስተውለው እንዲመለከቱ ይዘሏቸው። ተማሪዎች ሥዕሉን በደንብ ከተመለከቱ በኋላ የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያብራሩ ያድርጉ። በመጨረሻም የተማሪዎችን ትክክለኛ መልስ በመያዝ ስለ ለማዳ እንስሳት አገልግሎት አጠር ያለ ገለጻ በመስጠት ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ ለማዳ እንስሳት ሥዕሎች
- ስለ ለማዳ እንስሳት አገልግሎት የሚገልጽ ቻርት
- የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል

የማስተማርያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄዎች
- በጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ለማዳ እንስሳትን እንዲዘረዝሩ ዕድል ይስጧቸው።
- ✓ የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት እንዲዘረዝሩ ያድርጉ።
- ✓ ድመት፣ ውሻ፣ አህያ፣ ፈረስና የመሳሰሉት ለማዳ እንስሳት ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ይጠይቋቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳትና የሚራቡበት ወቅት

የይዘቱ ጭብጥ

እንደሚታወቀው በአካባቢያችን የተለያዩ እንስሳት ይኖራሉ። እነዚህ እንስሳት የሚራቡበት ወቅት የተለያየ ነው። አብዛኞቹ እንስሳት በቂ ምግብ እና ምቹ የአየር ሁኔታ ሲኖር ይራባሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ይህን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር ያመች ዘንድ የተለያዩ እንስሳት የሚራቡበትን ወቅት የሚገልጽ ቻርት ይጠቀሙ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎችን በአካባቢያቸው ስለሚገኙ እንስሳት የመራቢያ ወቅት ያላቸውን ግንዛቤ ይጠይቋቸው። ከመልሶቻቸው በመነሣት እንስሳት ለመራባት በቂ ምግብ እና ምቹ የአየር ሁኔታ እንደሚያስፈልጋቸው ገለጻ በማድረግ ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ እንስሳት የሚራቡበትን ወቅት የሚገልጽ ቻርት

የማስተማርያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- ገለጻ
- በጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሳት የሚራቡበትን ወቅት ከወላጆቻቸው ጠይቀው ለክፍል ጓደኞቻቸው ፅብረቃ እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው።
- ✓ እንስሳት ለመራባት የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎችን ይጠይቁ።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 3.2ሐ መልሶች

የአዛምድ መልሶች

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. ሐ

3.3 ንፅሕናና የግል ንፅሕና

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-10

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **የቤት ውስጥ የንፅሕና ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመፀዳጃ ቤት ንፅሕና ይጠብቃሉ፡፡**

የግል ንጽሕና

የይዘቱ ጭብጥ

የግል ንፅሕና ሲባል ዘወትር የሰውነታችንን እና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንፅሕና መጠበቅ ማለት ነው፡፡ ንፅሕናው በተጠበቀ ቤትና አካባቢ የሚኖር ቤተሰብ ራሱን ከብዙ በሽታ መከላከል ይችላል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት የግል ንጽህና አጠባበቅን የሚገልጹ የተለያዩ ሥዕሎች፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ መዝሙሮች፣ ፎቶ ግራፎች እና በራሪ ወረቀቶች ያዘጋጁ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! በምዕራፍ ሁለት ስለ ግል ንጽህና የተማሩትን እንዲያስታውሱ አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል ስለ ግል ንጽህና ምንነት ከነገሯቸው በኋላ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 3.18 የግል ንጽሕና አጠባበቅ ተመልክተው እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎችን ምላሽ ተከትሎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡

1. **ጥርሳችሁን በቀን ምን ያህል ጊዜ ትቦርሻላችሁ?**
2. **ገላችሁ እና ልብሶቻችሁ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ይታጠብላችኋል?**

ከተማሪዎች ምላሽ በመነሣት የግል ንጽህናቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለበቸው እና የግል ንጽህናን መጠበቅ ስለሚያስገኘው ጥቅም በመዘርዘር ማጠቃለያ ይስጧቸው፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ➢ **የግል ንጽህና አጠባበቅን የሚገልጹ የተለያዩ ሥዕሎች፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ መዝሙሮች፣ ፎቶ ግራፎች እና በራሪ ወረቀቶች**

የማስተማርያ ሥነ-ዘዴዎች

- **የቃል ጥያቄ**
- **ዕብረቃ**
- **ገለጻ**

- በጥያቄና መልስ

<u>የምዘናና የክትትል ስልቶች</u>

- ✓ ጥርሳችውን በቀን ምን ያህል ጊዜ እንደሚያጸዱ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ ገላቸው እና ልብሶቻቸው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ቤተሰቦቻቸው እንደሚያጥቡላቸው በወረቀት ጽፈው እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው፡፡
- ✓ የግል ንጽህናን መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ክፍል ውስጥ ተወያይተው ዕብረቃ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

ቆሻሻን ማስወገድና መልሶ መጠቀም

<u>የይዘቱ ጭብጥ</u>

ቤታችን እና በአካባቢያችን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ ብዙ ተረፈ-ምርቶች እንዲሁም ከተጠቀምን በኋላ በየጊዜው የሚጣል ቆሻሻ ይኖራሉ፡፡ ይህ የሚወገደው ቆሻሻ ከመጣላችን በፊት በየፈርጁ ለይቶ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ቆሻሻን በተለያየ መንገድ በማስወገድ መልሶ መጠቀም ይቻላል፡፡

<u>ቅድመ ዝግጅት</u>

መምህር! ወደ ክፍል ሲገቡ በቅድሚያ ስለ ቆሻሻ አወጋገድ እና መልሶ መጠቀም የሚያስገነዝብ ሥዕል፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ፖስተር እና ቻርት ያዘጋጁ፡፡

<u>የትምህርቱ አቀራረብ</u>

መምህር! ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ ያለውን ቆሻሻ እንዴት እንደሚያስወግዱ ጠይቀው መልሶቻቸውን በየተራ ይቀበሏቸው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን ሥዕል አስተውለው እንዲመለከቱ በማድረግ በቡድን ተወያይተው የተገነዘቡትን ዕብረቃ እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው፡፡ ከዕብረቃው በኋላ በሚከተለው መንገድ ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

ከቤታችን እና ከአካባቢያችን በተለያየ መንገድ የሚጣሉትን ቆሻሻዎች በአግባቡ ማስወገድ ያስፈልጋል:: እንደዚሁም በተገቢው ሁኔታ በማስወገድ መልሶ መጠቀም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡-

በቀላሉ የሚበሰብሱትን እና የማይበሰብሱትን ለይቶ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ በስብሰው ወደ አፈርነት የሚቀየሩትን ለእፅዋት ማዳበሪያነት፤ የማይበሰብሱትን ደግሞ በፋብሪካ በማቀነባበር መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ➢ የቆሻሻ አወጋገድ እና መልሶ መጠቀምን የሚያስገነዝብ ሥዕል እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- ➢ ቆሻሻ እንዴት እንደሚወገድ የሚገልጽ ፎቶ ግራፍ እና ቻርት

የማስተማርያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- ፅብረቃ
- ገለጻ
- በጥያቄና መልስ

የምዘናና የክትትል ስልቶች

- ✓ ቆሻሻን በጥንቃቄ እንዴት ማስወገድ እንዳለባቸው ይጠይቋቸው።
- ✓ የትምህርት ቤታቸውን ንጽሕና እንዲጠብቁ የቡድን ሥራ ይስጧቸው።
- ✓ ቆሻሻን እንዴት መልሶ መጠቀም እንደሚቻል በቡድን ሆነው ፅብረቃ እንዲያደርጉ ይዘሏቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 3.3 መልሶች

እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ. እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

ለ. የአዛምድ መልሶች

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. ሐ

ሐ. የምርጫ መልሶች

1. ሐ
2. ሀ
3. ለ
4. ሐ
5. ለ
6. ሐ

ምዕራፍ አራት

ማኅበራዊ አካባቢ

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 54

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ፡-

- የቤተሰብ አባላትን ይዘረዝራሉ፡፡
- የቤተሰብ አባላት መብትና ኃላፊነትን ይገልጻሉ፡፡
- የቤተሰብን መሰረታዊ ፍላጎት ይረዳሉ፡፡
- እጽዋትን በባህሪያቸው ይመድባሉ፡፡
- የትምህርት ቤት ግቢን ይለያሉ፡፡
- በትምህርት ቤት ከአቻዎቻችሁ ጋር የእርስ በእርስ ግንኙነትን አዳብራችሁ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡
- በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ ቦታዎችን የሚያመለክቱ ሥዕሎችን በመስራት ደኅንነታችሁን የምትጠብቁበትን መንገድ ያሳያሉ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

4.1 የቤተሰብ አባላትና ሚናቸው

4.2 ለመኖር ምን ያስፈልገናል?

4.3 በአካባቢያችን ለመኖር የሚያስፈልጉ እጽዋቶች

4.4 በትምህርት ቤታችን ምን ምን ነገሮችን እናገኛለን?

4.5 በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንሥራ

4.6 የትምህርት ቤትን ሕግና ደንቦችን መለየት

4.1 የቤተሰብ አባላትና ሚናቸው

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-9

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **የቤተሰብ አባላትን ይዘረዝራሉ፡፡**
- ✓ **የቤተሰብ አባላትን መብትና ኃላፊነት ይገልጻሉ፡፡**

የቤተሰብ አባላት

የይዘቱ ጭብጥ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ስለ ቤተሰብ ምንነት እንዲሁም የቤተሰብ አባላትን መብትና ኃላፊነት በደንብ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡ የቤተሰብ አባለት የሚባሉት አባት ፣ እናት፣ ልጆች ሲሆኑ በተጨማሪም አያት፣ አጎት፣ አክስት፣ የቤት ሠራተኞች እና የመሳሰሉት አብረው የሚኖሩት ሰዎችንም ያጠቃልላል:: እነዚህ የቤተሰብ አባላት የየራሳቸው መብትና ኃላፊነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ወላጆች ልጆቻቸውን ይንከባከባሉ፣ ልጆች ለወላጆቻቸው በአቅማቸው ይታዘዛሉ፣ ልጆች የመማር መብት አላቸው፣ የቤት ሠራተኞች ደግሞ በዋናነት በቤት ውስጥ እና በውጪ ሥራዎች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለርዕሱ ተስማሚ የሚሆኑ የመርጃ መሣሪያዎችን አሰናድተው ወደ ክፍል በመግባት ለተማሪዎች በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ አመቻችተው ያስቀመጧቸው፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች በዚህ ንዑስ ይዘት ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ስንት የቤተሰብ አባላት እንደሏቸው በመጠየቅ ያነቃቋቸው፡፡ በመቀጠልም ስለቤተሰብ ምንነት ገለጻ ካደረጉ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 4.1 የቤተሰብ አባላት በማዘጋጀት ይዘው ከገቡት መርጃ መሣሪያ ጋር በማቀናጀት እንዲመለከቱ ያድርጉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡

ተማሪዎች ስለ ቤተሰብ ሚና ማለትም የወላጆችን ኃላፊነት እና የልጆችን የሥራ ድርሻ እንዲገነዘቡ ለማድረግ በቅድሚያ በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን የወላጆችን ኃላፊነት የሚያሳይ ሥዕል 4.2 የቤተሰብ ኃላፊነት ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ያድርጓቸው፡፡ እንዲሁም የልጆችን የሥራ ድርሻ የሚያሳየውን ሥዕል ተመልክተው በቤት ውስጥ ያላቸውን የሥራ ድርሻ ለይተው እንዲናገሩ እድሉን ይስጧቸው፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች የልጆችን መብት በተመለከተ የመማር፣ ያልገባቸውን የመጠየቅ፣ የመጫወት፣ የወላጅ ፍቅርና እንክብካቤ እና የመሳሰሉትን መብቶች የማግኘት መብት እንዳላቸው እና መብቶቻቸውን መጠቀም እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በሥዕል 4.1 እና 4.2 ላይ የሚታዩት ስለ ቤተሰብ ምንነት፣ ስለ ወላጆች ኃላፊነት እና ስለ ልጆች ሥራ ድርሻ የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ለሌሎች ቤተሰብ አርአያ የሚሆኑ ቤተሰቦችን የሕይወት ተሞክሮ የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች (ቪዲዮዎች)
- ስለ ቤተሰብ ኃላፊነት እና የልጆች መብት የሚገልጽ ቻርት
- የሚና ጨዋታዎች (ተማሪዎች ከሚጫወቱት ጨዋታዎች መካከል አንዱን በመምረጥ የቤተሰብን ሚና እና ኃላፊነት የሚገልጽ ጨዋታ)
- መዝሙሮች [ከልጆች ዝግጅት (መርሃግብር) ላይ የተወሰደ]

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄዎች
- የተንቀሳቃሽ ምስሎች (ቪዲዮዎች) ምልከታ
- ገለጻ
- ስለቤተሰብ የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ማሳየት

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የቤተሰባቸውን አባላት ብዛት ስንት እንደሆኑ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያድርጉ።
- ✓ በሥዕል 4.1 እና 4.2 ላይ ያሉትን ስለ ቤተሰብ ምንነት፣ ስለ ወላጆች ኃላፊነት እና ስለ ልጆች የሥራ ድርሻ የተረዱትን እንዲገልጹ ያድርጓቸው።
- ✓ ከሥዕላዊ መግለጫው ላይ የተገነዘቡትን እንዲናገሩ ይጋብዟቸው።
- ✓ እርስዎ ካዘጋጇቸው ሞዴል ቤተሰብን የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች (ቪዲዮዎች) መካከል የተወሰነውን ካሳዩዋቸው በኋላ የተገነዘቡትን ይጠይቋቸው።
- ✓ በግል ሥራዎቻቸው ላይ የተጠየቁቸውን ጥያቄዎች እንዲያስረዱ ዕድል ይስጧቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 4.1ሀ መልሶች

የምርጫ መልሶች

1. ለ
2. ሀ

የመልመጃ 4.1ለ መልሶች

የእውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

4.2 ለመኖር ምን ያስፈልገናል?

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-8

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ✓ የቤተሰብን መሰረታዊ ፍላጎት ይገልጻሉ፡፡

ምግብ

የይዘቱ ጭብጥ

የሰው ልጆች ለመኖር በዋናነት ሦስት መሠረታዊ ፍላጎቶች ሊሟሉ ይገባል፡፡ እነርሱም ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ ናቸው፡፡ ምግብ ሰውነታችን ለመገንባትና ለመጠገን፣ ኃይልና ሙቀት ለመስጠት እና በሽታን ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

ምግብን ከሁለት መሠረታዊ ምንጮች ማለትም ከእንስሳት እና እፅዋት እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም እንስሳት እና እፅዋት ለምግብነት ይውላሉ ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ እንደ ዶሮ፣ በግ፣ ሚዳቋ፣ ድኩላ፣ ዓሳ፣ ጅግራ እና የመሳሰሉት ሥጋቸው የሚበሉ እንስሳት ሲሆኑ በተቃራኒው ደግሞ እንደ ውሻ፣ ድመት፣ ቀበሮ፣ ጅብ፣ አህያ እና ሌሎች እንስሳት በሀገራችን ማኅበረሰብ ሊበሉ የማይችሉ ናቸው፡፡ ከእፅዋት እንደ ጎደሬ፣ ሞሪንጋ (ሽፈራው)፣ ሀባብ፣ ጎመን፣ እንሰት፣ በቆሎ፣ አደንጓሬ እና የመሰሰሉት የሚበሉ ሲሆኑ ከማይበሉት ደግሞ እንደ አሪቲ፣ ጠጅ ሳር፣ ብሳና፣ ግራር እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ይህንን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር የሚያስፈልገዎትን የመርጃ መሣሪያዎች አሰናድተው ክፍል ውስጥ ይዘው በመግባት ሊታዩ በሚችሉበት ቦታ ያስቀምጧቸው፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች ይህንን ይዘት በአግባቡ እንዲረዱት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል 4.4 መሠረታዊ ፍላጎቶች እና የተዘጋጀውን የመርጃ መሣሪያ በማሳየት የተገነዘቡትን ይጠይቋቸው፡፡

በተጨማሪም ከእንስሳት እና እፅዋት መካከል የሚበሉትን እና የማይበሉትን በቡድን በቡድን ሆነው በመወያየት እንዲለዩአቸው ክፍሉን ያመቻቹላቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች የውይይታቸውን ፍሬ ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡ በመጨረሻም ስለ ዕለቱ ትምህርት አጠር ያለ ክለሳ በማድረግ ያጠናቅቁ፡፡

<u>አስፈላጊ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ የእፅዋት እና እንስሳት ሥዕሎች
- አጫጭር ቻርቶች
- በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የእፅዋት እና እንስሳት ተዋጽኦ ምግቦች
- እፅዋትን እና እንስሳትን ወካይ የሆኑ ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶች (ሞዴሎች)

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- የቃል ጥያቄዎች
- የተለያዩ ልብሶችን የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ማሳየት
- ገለጻ

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ የምግብን ጥቅም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩዋቸውን የእፅዋት እና የእንስሳት ተዋጽኦ ምግቦች እንዲለዩ ይጋብዟቸው፡፡
- ✓ በመስክ ምልከታ ጊዜ ያዩአቸውን ሊበሉ የሚችሉ እና ሊበሉ የማይችሉ እፅዋት እና እንሳስትን እንዲዘረዝሩ ይርዷቸው፡፡
- ✓ በቡድን ውይይት ጊዜ የተጠየቋቸውን የመወያያ ጥያቄዎች እንዲያስረዱ ዕድል ይስጧቸው::
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

ልብስ

<u>የይዘቱ ጭብጥ</u>

ልብስ ከመሠረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ውጤቶች ሊሰራ ይችላል፡፡ ከተፈጥሮ ሲባል ከእፅዋት እና እንስሳት ውጤቶች ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ጥጥ፣ የተልባ እግር፣ ቃጫ፣ ዘንባባ እና የመሳሰሉት ለልብስ መሥሪያነት የሚያገለግሉ እፅዋት ሲሆኑ ከእንስሳት ደግሞ የሃር ትል የሃር ልብስ ለመስራት፣ የተለያዩ እንስሳት ፀጉራቸው ብርድ ልብስ እና ሌሎችንም ለመስራት ፣ ቆዳቸው ለጫማ፣ ለቀበቶ ቦርሳ እና ሌሎችንም የልብስ ዓይነቶች ለመሥራት ያገለግላሉ:: የፕላስቲክ ጫማዎች፣ የተለዩ ልብሶች፣ ኮፍያዎች እና የመሳሰሉት ደግሞ ከሰው ሰራሽ ውጤቶች የሚሰሩ ልብሶች ናቸው፡፡

ቅድመ ዝግጅት

ለልብስ መሥሪያነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲሁም ለማስተማር የሚያስፈልገዎትን መርጃ መሣሪያዎች በሥዕል አሰናድተው ክፍል ውስጥ በመግባት ሊታዩ በሚችሉ ቦታ በማስቀመጥ ተማሪዎች እንዲመለከቷቸው ያድርጉ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር!ተማሪዎች ይህንን ይዘት በአግባቡ እዲረዱት ለማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተቀመጠውን ሥዕል 4.4 መሠረታዊ ፍላጎቶች በትኩረት እንዲመለከቱ በማድረግ የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ያዘጋጇቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንም በመጠቀም ዋና ዋና ነጥቦችን በመዘርዘር ያጠቃልሉ፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ የእፅዋት እና እንስሳት ሥዕሎች
- ከተለያዩ እንስሳት እና እፅዋት የተሠሩ ልብሶችን የሚገልጽ ቻርት
- በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ከእፅዋት እና ከእንስሳት የሚሠሩ ልብሶች
- ከሰው ሠራሽ ጥሬ እቃ የተሰሩ (የፕላስቲክ) ልብሶች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ጥያቄና መልስ
- ገለጻ
- የተለያዩ ልብሶችን የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ማሳየት
- የቡድን ውይይት

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የልብስን ጥቅም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩዋቸውን የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ልብሶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡
- ✓ በቡድን ውይይት ጊዜ የተጠየቁትን የመወያያ ጥያቄዎች እንዲያስረዱ ዕድል ይስጧቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

መጠለያ

የይዘቱ ጭብጥ

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ሲማሩ የመጠለያ ዓይነቶች እና ከምን ከምን እንደሚሰሩ ይረዳሉ:: ለምሳሌ፦ ከብሎኬት፣ ከሲሚንቶ፣ ከሸክላ ጡብ፣ ከድንጋይ እና ከመሳሰሉት ቁሳቁሶች መጠለያ መሥራት እንደሚቻል ይገነዘባሉ፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለተማሪዎች ስለ መጠለያ በጥሩ ሁኔታ ለማስገንዘብ የሚረዳዎትን የመርጃ መሣሪያዎች አዘጋጅተው ክፍለ ጊዜውን በተገቢው መንገድ ይጠቀሙ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ሥዕል 4.4 መሠረታዊ ፍላጎቶች በመመልከት እና ለመጠለያ መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ስማቸውን በመጥራት እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው። እንደ አስፈላጊነቱ ከክፍል ውጪ በትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን ቤቶች ተዘዋውረው እንዲመለከቱና የተረዱትን እንዲናገሩ ማድረግ ተማሪዎች ስለ መጠለያ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ እንዲል ስለሚያደርግ ይህን ተግባር እንዲያከናውኑ ይርዷቸው። በመጨረሻም ከተማሪዎች ምላሽ በመነሣት ማጠቃለያ መስጠት ተገቢ ነው።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሲሚንቶ፣ ብሎኬት፣ እንጨትና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች
- ባህላዊና ዘመናዊ ቤቶችን የሚገልጽ ቻርት
- የቤት ሞዴሎች(ከካርቶን ከእንጨት እና ከመሳሰሉት ቁሳቁሶች የተሰሩ)
- የተለያዩ ቤትን ሊያሳዩ የሚችሉ ሥዕሎች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ጥያቄና መልስ
- ገለጻ
- የመስክ ምልከታ (የትምህርት ቤት ግቢ ከምን ከምን እንደተሰራ መመልከት)

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የመጠለያን ጥቅም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያድርጉ።
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩዋቸውን የመጠለያ ዓይነቶች እንዲዘረዝሩ ይጋብዟቸው።
- ✓ መጠለያ ከምን ከምን ሊሠራ እንደሚችል ይጠይቋቸው።
- ✓ በመስክ ምልከታ ጊዜ ያዩአቸውን ቤቶች ከምን ከምን እንደተሠሩ እንዲዘረዝሩ ዕድል ይስጧቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የመልመጃ 4.2 መልሶች

የአዛምድ መልሶች

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ

4.3 በአካባቢያችን ለመኖር የሚያስፈልጉ እጽዋት

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-12

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **እጽዋትን በባህሪያቸው ይመድባሉ፡፡**

የእፅዋት አስተዳደግ

የይዘቱ ጭብጥ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች በቅድሚያ ስለ እፅዋት ምንነት ማለትም እፅዋት በብርሃን አስተዋምሮ ሂደት የራሳቸውን ምግብ ማዘጋጀት የሚችሉ በአብዛኛው አረንጓዴ ሆነው የሚታዩ ሕይወት ያላቸው ነገሮች መሆናቸውን ማስገንዘብ ነው፡፡ እፅዋት በብዙ ነገሮች ስለሚለያዩ በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው መመደብ ይቻላል፡፡

በአስተዳደጋቸው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነርሱም ትናንሽ፣ መካከለኛ እና ትላልቅ እፅዋት በመባል ነው፡፡ እንደ ሳር፣ ሙጃ፣ሰርዶ፣ ድንች እና የመሳሰሉት ትናንሽ እፅዋት ናቸው፡፡ ጤናዳም፣ ዳማከሴ፣ ፅጌረዳ አበባና የመሳሰሉት መካከለኛ እፅዋት ሲሆኑ እንደ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ባህር ዛፍ፣ ጥቁር እንጨትና የመሳሰሉት ደግሞ ከትላልቅ እፅዋት ውስጥ ይመደባሉ፡፡

ከሚገኙበት ስፍራ አንፃር ደግሞ የከፍተኛ ስፍራ፣ የመካከለኛ እና የዝቅተኛ ስፍራ እፅዋት በመባል በሦስት ይመደባሉ፡፡ ጥድ፣ ኮሶ፣ ቀርከሃ፣ ጥቁር እንጨትና የመሳሰሉት የከፍተኛ ስፍራ እፅዋት ሲሆኑ እንደ ወይራ፣ ብሳና፣ ግራዋ፣ ዝግባ እና ሌሎች ደግሞ የመካከለኛ ስፍራ እፅዋት ናቸው:: በዝቅተኛ ስፍራ ከሚገኙ እፅዋት መካከል ደግሞ እንደ ግራር፣ ዋንዛ፣ ዋርካ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም እፅዋት በቅጠላቸው፣ በአበባቸው እና በግንዳቸው ዓይነት የተለያዩ መሆናቸውን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የጥድ፣ የዋንዛ እና የሳር ቅጠሎች የተለያዩ ናቸው፡፡ የአደይ አበባ እና የፅጌረዳ አበባ በአበባ ደግሞ በዓይነታቸው፣ በመጠናቸው፣ በመልካ አበባ ቀለማቸውና በመሳሰሉት ነገሮች ይለያያሉ፡፡ እፅዋት በቅጠላቸው እና በአበባቸው እንደሚለያዩ ሁሉ በግንዳቸው መጠን፣ ጥንካሬ፣ ቀለም እና በሌሎች ነገሮችም ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ የቃሪያ፣ የጥድ፣ የዋርካ፣ የጥቁር እንጨት፣ የግራር፣ የኮሶ እና የመሳሰሉት እፅዋት ግንዳቸው የተለያየ ነው፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! በቅድሚያ ለተማሪዎች ማስተማሪያ ይረዳዎት ዘንድ ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት የተለያዩ የእፅዋት ዝርያዎችን በማዘጋጀት በትምህርት ቤት ግቢ ካሉ በመስክ ምልከታ ከሌሉ ደግሞ ከተለያዩ አካባቢዎች በማስመጣት ወይንም በማምጣት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በተጨማሪም ክፍል ውስጥ ለማምጣት የማያመቹትን በሥዕል፣ በፎቶ ግራፍ እና ወካይ የሆኑ ሰው ሠራሽ እፅዋትን ለመጠቀም ወደ ክፍል ይዘው መግባት ይጠበቅብዎታል።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ወደ ትምህርት ንዑስ ርዕስ ከመግባትዎ አስቀድመው ተማሪዎችን ከዚህ በፊት ምዕራፍ ሁለት ላይ ተምረው እንደነበር በማስታወስ ስለ እፅዋት ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ከጠየቁ በኋላ ወደ ዕለቱ ንዑስ ርዕስ መንደርደር ይችላሉ።

እጽዋት ለማደግ የፀሐይ ብርሃን፣ አየር፣ አፈር እና ውሃ እንደሚያስፈልጋቸው ገለጻ በማድረግ በአስተዳደጋቸው ደግሞ በሦስት እንደሚመደቡ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ መስጠት ይኖርብዎታል።

በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ለተማሪዎች የተቀመጡትን ሥዕሎች ሥዕል 4.5 ትናንሽ እፅዋት፣ሥዕል 4.6 መካከለኛ እፅዋት ስዕል 4.7 ትልልቅ እፅዋት በመመልከት እፅዋትን በአስተዳደጋቸው በሦስት እንዲመድቧቸው ያድርጉ። ከዚያም በመቀጠል ሥዕል 4.8 የተክል ውጫዊ ገፅታ በመመልከት እፅዋት በግንዳቸው፣ በቅጠላቸው እና በአበባቸው የተለያዩ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ካደረጉ በኋላ በአካባቢያቸው የሚገኙትን እፅዋት አበባቸውን፣ ቅጠላቸውን እና ግንዳቸውን በመመልከት በተግባር አንድ መለየታቸውን ያረገግጡ። ተማሪዎች ተግባር አንድን ካጠናቀቁ በኋላ እፅዋት በቅጠላቸው፣ በግንዳቸው እና በአበባቸው የተለያዩ መሆናቸውን ለይተው መናገር አለባቸው።

እፅዋትን ከሚገኙበት ስፍራ አንጻር በሦስት መድበው በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኙትን ሥዕሎች (ሥዕል 4.9 የዝቅተኛ፣ 4.10 የመካከለኛ እና 4.11 የከፍተኛ ስፍራ እፅዋት) ወይንም አጠር ያለ ቻርት በማዘጋጀት ከቻርቱ ላይ በከፍተኛ ስፍራ የሚገኙ፣ በመካከለኛ ስፍራ የሚገኙ እና በዝቅተኛ ስፍራ የሚገኙ እፅዋት በማለት መድበው ማስገንዘብ ተገቢ ነው። በመጨረሻም ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት ለማጠናከር ያመች ዘንድ መከለስና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያለውን መልመጃ ደብተራቸው ላይ እንዲሠሩ አድርገው ትምህርቱን ያጠናቅቁ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በአካባቢ የሚገኙ እፅዋቶች
- የእፅዋት ፖስተሮች
- ስለእፅዋት ምድቦች የሚገልጹ አጫጭር ቻርቶች
- የእፅዋት ፎቶዎች
- ወካይ የሆኑ ሰው ሠራሽ እፅዋት (ሞዴሎች)

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የእፅዋት የአካል ክፍሎችን በተመለከተ የቃል ጥያቄዎች
- የመስክ ምልከታ (በትምህርት ቤታቸው የሚገኙ እፅዋትን መመልከት)
- የግል ሥራ (የእፅዋት ውጫዊ የአካል ክፍሎችን በተመለከተ)
- ገለጻ

የምዘናና ክትትል ስልቶች

የእፅዋትን ምንነት ክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩዋቸውን እፅዋት እንዲለዩ ይጋብዟቸው፡፡

በመስክ ምልከታ ጊዜ የተመለከቷቸውን እፅዋት እንዲዘረዝሩ ይርዷቸው፡፡

በግል ሥራ ላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች እንዲያስረዱ ዕድል ይስጧቸው፡፡

ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የተግባር አንድ መልስ

- መምህር! ተማሪዎቹ በትምህርት ቤታቸው የሚገኙትን እፅዋት አበባቸውን፣ ቅጠላቸውን እና ግንዳን ተመልክተው መለየታቸውን ያረጋግጡላቸው፡፡

የመልመጃ 4.3 መልሶች

የምርጫ መልሶች

1. ሀ
2. ለ

4.4 በትምህርት ቤታችን ምን ምን ነገሮችን እናገኛለን?

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-8

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ የትምህርት ቤት ግቢን ይለያሉ፡፡
- ✓ በትምህርት ቤታቸው የሚገኙ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርት ቤት ግቢ

የይዘቱ ጭብጥ

በትምህርት ቤት ውስጥ ልዩ ልዩ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡- ሰንደቅ ዓላማ፣ የመጫወቻ ሜዳ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቢሮዎች፣ የመምህራን ማረፊያ፣ ቤተ-ሙከራ፣ ቤተ-መጽሐፍት እና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን ከመለየትም በላይ በውስጡ የሚገኙትን ነገሮች ዝርዝር ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን በግልፅ ለማስረዳት የሚያስችል የመርጃ መሣሪያ ቀደም ብለው በማዘጋጀት በክፍል ዉስጥ ግልፅ በሆነ ስፍራ ላይ ያስቀምጡላቸው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተቀመጠውን የትምህርት ቤት ሥዕል ከነባራዊው ትምህርት ቤታቸው ጋር ለማነፃፀር ይጠቀሙበት፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ ላይ ስለ ነገሮች መገኛ የተማሩትን እንዲያስታውሱ በማድረግ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡ ከዚያም በመቀጠል በቡድን በቡድን በማደራጀት በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የሚገኙት ነገሮችን እንዲመለከቱ በማድረግ ከምልከታው መልስ በክፍል ውስጥ ፅብረቃ እንዲያቀርቡ በማድረግና ካቀረቡት ፅብረቃ በመነሣት በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ስለሚገኙ ዋና ዋና ነገሮች እንዲገነዘቡ ገለጻ ያድርጉላቸው:: በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተሰጠው ተግባር አንድ የትምህርት ቤት ግቢን ሥለው በማምጣት በውስጡ የሚገኙ ነገሮችን አንድ በአንድ በመጠቆም እንዲለዩ እና እንዲናገሩ ያበረታቷቸው::

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የትምህርት ቤት ግቢን የሚያሳይ ሥዕል
- የትምህርት ቤት ግቢን የሚያሳዩ ፎቶዎች
- የትምህርት ቤት ሞዴሎች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የመስክ ምልከታ (የትምህርት ቤት ግቢን መመልከት)
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ሥራ (የትምህርት ቤት ግቢን መለየት)
- ገለጻ

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የትምህርት ቤት ግቢን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡
- ✓ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ምን ምን ነገሮች እንደሚገኙ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ስላዩት የትምህርት ቤት ግቢ እንዲገልጹ ይጋብዟቸው፡፡
- ✓ በመስክ ምልከታው ጊዜ በትምህርት ቤት ግቢያቸው ውስጥ የተመለከቷቸውን ነገሮች እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ከመስክ ምልከታ በኋላ በክፍል ውስጥ ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የተግባር ሁለት መልስ

- መምህር! ተማሪዎቹ የትምህርት ቤት ግቢያቸውን በትክክል መሳላቸውና ቦታዎችን መጠቆማቸውን ያረጋግጡላቸው፡፡

የመልመጃ 4.4 መልሶች

የግለጹ መልሶች

1. የትምህርት ቤት ግቢን ያሳያል
2. የመጫወቻ ሜዳ፣ የቤተ-መጽሐፍት ክፍል፣ ቢሮዎች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ መፀዳጃ ቤት፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ የመምህራን ማረፊያ፣ የክበባት ክፍል እና የጥበቃ ቤት ናቸው፡፡

4.5 በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንሥራ

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-8

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ በትምህርት ቤት ከአቻዎቻቸው ጋር የእርስ በእርስ ግኑኝነትን አዳብረው የተለያዩ ተግባራትን በጋራ ያከናውናሉ፡፡

በጋራ መጫወት

የይዘቱ ጭብጥ

ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥም ሆነ በቤታቸው አካባቢ እነርሱን በሚመጥን ሁኔታ ጨዋታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በጋራ በሚጫወቱበት ጊዜ ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ ችሎታን፣ መልካም የሆነ የእርስ በእርስ ግኑኝነትን፣ መተሳሰብንና የመሳሰሉትን በጎ ተግባራት እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በጋራ ሲጫወቱ ሊያዳብሯቸው የሚችሉ ነገሮች ጥሩ ነገሮች

እንዳሉ ሁሉ በጥንቃቄ ካላከናወኗቸው ደግሞ ሊደርስባቸው የሚችል ጉዳትም ጭምር እንዳለ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ክፍል ከመግባትዎ በፊት ተማሪዎች ሊጫወቷቸው የሚችሉ ጨዋታዎችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መሰብሰብ ይኖርብዎታል። ማለትም የልጆችን ጨዋታ የሚያሳይ አስተማሪ ተንቀሳቃሽ ምስል ወይንም ድራማ፣ የሚና ጨዋታና ሌሎችንም በቅድሚያ ያዘጋጁ። የተክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምም ተማሪዎችን ለማሳየት ይዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች ምን ምን ዓይነት ጨዋታዎችን በትምህርት ቤት እና በአካባቢያቸው ሊጫወቱ እንደሚችሉ ይጠይቋቸው። ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀትም በተግባር ሦስት ላይ በተሰጠው መሠረት የሚያዉቁትን እና የሚችሉትን ጨዋታ እንዲጫወቱ ያመቻቹላቸው። በመምህሩ የተዘጋጀውን የጨዋታ ዓይነቶች እና ከተማሪዎች የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶችን በመሰብሰብ መልሰው ለተማሪዎች ማዋል ይችላሉ። ልጆች በባህሪያቸው አንድ ነገር ላይ ለረዥም ጊዜ መቆየት ስለማይችሉ የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶችን እየቀያየሩ እንዲጫወቱ ማድረግም ያስፈልጋል። ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ ጨዋታው ተማሪዎችን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። ከዚህም ባሻገር የሚያዝናና እና ቁም ነገር የሚያስጨብጥ እንዲሁም ለወደፊት እጣፋንታቸው መልካም የሆነ መሠረት የሚጥሉበት ወይንም ተሰጥዖአቸውን የሚያዳብሩበት መሆን አለበት። በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 4.13 ተማሪዎች በጋራ ሲጫወቱ፤ በጋራ ሲሠሩ የሚያሳየውን እንዲመለከቱ ያድርጉ።

በመጨረሻም ልጆች በትምህርት ቤት ዉስጥ በጋራ በሚጫወቱበት ጊዜ፡-

- በትምህርታቸው ንቁ ተሳታፊ ለመሆን
- ሃሳባቸውን በነፃነት ለመግልፅ
- መልካም የሆነ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማዳበር
- መተሳሰብንና መረዳዳትን ለማዳበር እንደሚያስችላቸው በመጠቆም ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ተማሪዎች በጋራ ስጫወቱ የሚያሳይ ፎቶዎች
- ስለጨዋታ የሚያሳዩ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄ
- የሚና ጨዋታ (ተማሪዎች በጋራ በሚጫወቷቸው ጨዋታዎች እና በጋራ የሚሰሯቸው ሥራዎች ላይ)
- የቡድን ጨዋታ (በመምህሩ የተዘጋጀ እና ከተማሪዎች የተሰበሰቡ የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶች)

- በገለጻ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ በትምህርት ቤታቸው እና በአካባቢያቸው ምን ዓይነት ጨዋታዎችን በጋራ እንደሚጫወቱ ይጠይቋቸው።
- ✓ በትምህርት ቤት እና በአካባቢያቸው በጋራ የሚጫወቷቸውን ጨዋታዎች እንዲለዩ ያድርጉ።
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩአቸውን የጋራ ጨዋታዎች እንዲዘረዝሩ ይጋብዟቸው።
- ✓ በትምህርት ቤት መጫወቻ ሜዳ ላይ በጋራ የተጫወቷቸውን ጨዋታዎች እንዲዘረዝሩ ያድርጓቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የተግባር ሦስት መልሶች

1. መምህር! ተማሪዎቹ የሚጫወቷቸውን ጨዋታ በትክክል ይመልከቱ
2. መምህር! ተማሪዎች ከተጫወቷቸው ጨዋታዎች እርስ በራሳቸው የተማማሩትን ሲገልፁ ይገምግሙላቸው።

በጋራ እንሥራ

የይዘቱ ጭብጥ

መምህር! ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸውም ሆነ በአካባቢያቸው በጋራ ሊሠሯቸው የሚችሉትን ሥራዎች ሊያሳዩዋቸው ይገባል። በጋራ በሚሠሩበት ጊዜ ተማሪዎች መረዳዳትን፣ መደጋገፍን፣ ሥራ የመሥራት ክህሎትን እና ባህልን እንደሚያያዳብሩ ያስገንዝቧቸው። በተጨማሪም በጋራ በሚሰሩበት ወቅት በአካባቢያቸው ጉዳት ሊያደርሱባቸው ከሚችሉ ጎጅ ነገሮች ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው ማሳወቅ ይኖርብዎታል።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለአንደኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሆኑ በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ሊተገበሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ በጋራ የሚሠሩ የሥራ ዓይነቶችን ማዘጋጀት ይኖርብዎታል።በተጨማሪም በቅድሚያ ልጆች በጋራ የሚሠሯቸውን ሥራዎች የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ድራማዎች፣ የሚና ጨዋታዎች እና ሥዕሎችን ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች በአካቢያቸው ምን ምን ሥራዎችን በጋራ እንደሚሠሩ ከጠየቁ በኋላ መልሶቻቸውን መሠረት በማድረግ በተግባር ሦስት የተሰጠውን በቡደን በቡደን በመሆን በሚና ጨዋታና በድራማ መልክ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲገልጹ ያድርጓቸው። በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኘውን ሥዕል 4.13 ተማሪዎች በጋራ ሲጫወቱ፤ በጋራ ሲሠሩ እና ያዘጋጇቸውን

ተንቀሳቃሽ ምስሎች በመጠቀም ያቅርቡላቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ከዚህ ዝግጅት የተረዱትን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም በጋራ ሲጫወቱ ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች በማስገንዘብ ትምህርቱን ያጠቃልሉ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- በጋራ የሚሠሩ ሥራዎችን የሚያሳዩ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- ተማሪዎች በጋራ ትምህርት ቤታቸውን ሲንከባከቡ የሚያሳይ ፎቶዎች

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- የቃል ጥያቄ
- የሚና ጨዋታ (ተማሪዎች በጋራ ትምህርት ቤታቸውን የሚንከባከቡበትን መንገድ በተመለከተ)
- ገለጻ
- በጥያቄና መልስ

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ በቤታቸው አካባቢ ምን ምን ዓይነት የጋራ ሥራዎችን እንደሚሠሩ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው እና በትምህርት ቤታቸው በጋራ የሚሠሯቸውን ሥራዎች እንዲለዩ ያድርጓቸው::
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ ያዩአቸውን በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች እንዲዘረዝሩ ይጋብዟቸው፡፡
- ✓ በትምህርት ቤት የሚሠሯቸውን የጋራ ሥራዎች በድራማ እና በሚና ጨዋታ መልክ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የመልመጃ 4.5 መልሶች

<u>የግለጹ መልሶች</u>

1. መምህር! ከተማሪዎች ዝርዝር መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡
2. መምህር! ተማሪዎች በጠቀሷቸው ክበባት ውስጥ እንደሚሳተፉባቸው በማረጋገጥ መልሶቻቸውን ይቀበሏቸው፡፡

4.6 የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን መለየት

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-9

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ ቦታዎችን የሚያመለክቱ ሥዕሎችን በመስራት ደኅንነታቸውን የሚጠብቁበትን መንገድ ያሳያሉ።።**

የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦች

የይዘቱ ጭብጥ

ትምህርት ቤቶች የየራሳቸውን ሕግና ደንቦች በማዘጋጀት ይተዳደራሉ።። ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ ሆነው እንዲያድጉ ሕግና ደንቦችን ማስተማር ያስፈልጋል።። ሕግና ደንቦችንም እንዲረዱ ማድረግ እና በአግባቡ መተግበራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።።

የሚከተሉትን የትምህርት ቤትና አካባቢው ሕግና ደንብ አለማክበር ለአደጋ ሊያጋልጡን ይችላሉ።።

- **በአጥር ላይ ለመዝለል መሞከር (መዝለል)**
- **የቤተ-ሙከራ ቁሳቁሶችን ያለአግባብ መንካት**
- **መፀዳጃ ቤትን በአግባቡ አለመጠቀም**
- **የመንገድ መብራት ሕጎችን መተላለፍ**
- **የኤሌክትሪክ ሽቦዎችን መነካካት**
- **ድንጋይ መወራወር እና የመሳሰሉት ናቸው።።**

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን ሕግና ደንቦች በዝርዝር የማወቅ እድላቸው ዝቅተኛ ስለሆነ እርሶ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ዋና ዋና ሕግና ደንቦቹን በመጠየቅ በቻርት ላይ አዘጋጅተው ወደ ክፍል ሲገቡ ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ ላይ ያስቀምጡት።።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች ስለ ክፍላቸው እና ትምህርት ቤታቸው ሕግና ደንቦች በተግባር አራት ላይ እንዲወያዩ ያድርጓቸው።። በመቀጠልም ተማሪዎች ስለተወያዩባቸው ሐሳብ አጠር ያለ ዕብረቃ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው።። ከተማሪዎች ዕብረቃ በመነሣት የክፍላቸውን እና ትምህርት ቤታቸውን ሕግና ደንቦች ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው በማረጋገጥ ወደ ቀጣዩ የጋራ ሥራ ይሸጋገሩ።። በጋራ በሚሰሩበት ወቅት ደኅንነታቸውን ከአደጋ የሚጠብቁበትን መንገድ በሥዕል አዘጋጅተው እንዲያመጡ ይዘሏቸው።። በተጨማሪም ደኅንነታቸውን ከአደጋ የሚጠብቁበትን መንገድ

በድራማ ወይንም በጭውውት መልክ እንዲያሳዩ ይጋብዟቸው፡፡ የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦች በትምህርት ቤት ቆይታቸው ሊተገብሯቸው እንደሚገባም ይንገሯቸው፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- በጋራ የሚሠሩ ሥራዎችን የሚያሳዩ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- በተምህርት ቤታቸው ተማሪዎች የሰልፍ ሥነ-ሥርዓትን የሚያሳዩ ፎቶዎች

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- የቃል ጥያቄ
- የሚና ጨዋታ (ተማሪዎች የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን ማክበር በተመለከተ)
- የተግባር ሥራ (የትምህርት ቤት ሕግና ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ)
- በገለጻ
- ጥያቄና መልስ

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ በቤታቸው አካባቢ ምን ዓይነት የጋራ ሥራዎችን እንደሚሠሩ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ በአካባቢያቸው እና በትምህርት ቤታቸው በጋራ የሚሠሯቸውን ሥራዎች እንዲለዩ ያድርጓቸው::
- ✓ በሥዕላዊ መግለጫው ላይ የተመለከቷቸውን በጋራ የሚሠሩ ሥራዎች እንዲዘረዝሩ ይጋብዟቸው፡፡
- ✓ በትምህርት ቤት የሚሠሯቸውን የጋራ ሥራዎች በድራማ እና በሚና ጨዋታ መልክ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

የመልመጃ 4.6 መልሶች

<u>እውነት/ሐሰት መልሶች</u>

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ. እውነት/ሐሰት መልሶች

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት

ለ. የምርጫ መልሶች

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ
4. ሐ
5. ሀ

ምዕራፍ አምስት

ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-34

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ የትራፊክ ደንቦችን ይተገብራሉ፡፡
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገነዘባሉ፡፡
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ሐዘኔታ እና ፍቅር ያሳያሉ፡፡

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

5.1 ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዴት እንጠቀማለን?

5.2 ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ምንድን ነው?

5.1 ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዴት እንጠቀማለን?

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-17

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ **የትራፊክ ደንቦችን ይገልጻሉ፡፡ ----------**
- ✓ **የትራፊክ ደንቦችን ይተገብራሉ፡፡**

የተሽከርካሪና የእግረኛ መንገድ

የይዘቱ ጭብጥ

ተሽከርካሪ የምንለው በእንስሳት፣ በነዳጅ ወይንም በኤሌክትሪክ ኃይል ሊንቀሳቀስ የሚችል በአብዛኛው ለሰዎች እና እቃ ማጓጓዣነት የሚያገለግል ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ነው፡፡ የእግረኛ እና የተሽከርካሪ መንገድ የተለያየ ነው፡፡ ለተሽከርካሪ መንቀሳቀሻ ብቻ የተፈቀደ መንገድ የተሽከርካሪ መንገድ ይባላል:: ለእግረኛ መንቀሳቀሻ ብቻ የተፈቀደ መንገድ የእግረኛ መንገድ ይባላል፡፡ እግረኞች ከተሽከርካሪዎች በተቃራኒ መንገድ የሚጓዙት አንደኛው የሌላኛውን እንቅስቃሴ በግልፅ ለማየት እንዲችል እና ራሳችንን ከአደጋ ለመጠበቅ ነው፡፡

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለተማሪዎች አስተማሪ በሆኑ ሰዎች የተሽከርካሪ መንገድ አጠቃቀምን የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ትናንሽ ሞዴል መኪናዎች፣ ፖስተር እና ሥዕል ማዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

የዚህን ንዑስ ርዕስ ፅንሰ ሐሳብ ለተማሪዎች ለማስጨበጥ የሚከተሉትን መወያያ ጥያቄዎች በማቅረብ ትምህርቱን መጀመር፡፡

- **የተሽከርካሪ እና የእግረኛ መንገድ ልዩነታቸው ምንድን ነው?**
- **ሰዎችና ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ አቅጣጫ የማይጓዙት ለምንድን ነው?**

የተማሪዎችን መልሶች ከተቀበሉ በኋላ እርስዎ በቂ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎችን በአምስት ቡድን በማደራጀት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ በተሰጠው የቡድን ውይይት አንድ ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው መልሶቻቸውን በቡድን ተወካዮቻቸው እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው፡፡ መልሶቻቸውን መነሻ በማድረግ የተሽከርካሪ እና የእግረኛ መንግድ ምንነትን ይግለጹላቸው፡፡ ገለጻውን ካጠናቀቁ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 5.1 ተገቢ የሆነ እና ሥዕል 5.2 ተገቢ ያልሆነ የእግረኞች መንገድ አጠቃቀም ተማሪዎች እንዲመለከቱ እና ከሥዕሉ ሥር የተሰጡትን ጥያቄዎች አንብበው እንዲመለሱ ያበረታቷቸው፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ተማሪዎችን ስለትራፊክ መንገድ

አጠቃቀም (አሽከርክር ረጋ ብለህ ...የሚለውን) መዝሙር ያዘምሯቸው፡፡

በመጨረሻም ስለ ተሽከርካሪ እና እግረኛ መንገድ ምንነት እና የአጠቃቀም ልዩነት በመከለስ ትምህርቱን ማጠቃለል ይችላሉ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- **የእግረኞችን መንገድ አጠቃቀም የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስሎች**
- **የተሽከርካሪ እና እግረኛ መንገድ ሥዕሎች እና ፖስተሮች**

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- **የቡድን ውይይት (የእግረኛ እና የተሽከርካሪ መንገድ አጠቃቀም ጥንቃቄን መተግበር)**
- **የቃል ጥያቄ**
- **ገለጻ**
- **ጥያቄና መልስ**
- **መዝሙር መጠቀም (የትራፊክ መንገድ አጠቃቀምን)**

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ **የተሽከርካሪ እና የእግረኛን መንገድ ለይተው እንዴት እንደሚጠቀሙ እንዲያስረዱ ማድረግ፡፡**
- ✓ **የተሽከርካሪን መንገድ በየትና መቼ መጠቀም እንዳለባቸው ይጠይቋቸው፡፡**
- ✓ **በእግረኛ መንገድ ላይ ሲጓዙ የትኛውን አቅጣጫቸውን ይዘው መጓዝ እንዳለባቸው ተወያይተው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡**
- ✓ **ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡**

<u>የትራፊክ መብራት</u>

<u>የትምህርቱ ጭብጥ</u>

በመገናኛ መንገዶች ላይ ተሽከርካሪዎችና እግረኞች ተራቸውን ጠብቀው እንዲተላለፉ የሚያስችል መብራት የትራፊክ መብራት ይባላል፡፡ የትራፊክ መብራት ቀለም ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም፡- ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ናቸው፡፡ የመብራቱ ቀለማት የሚያስተላልፉት መልእክት አላቸው፡፡ ቀይ መብራት ቁም ለማለት ሲሆን ቢጫ መብራት ተዘጋጅ እንዲሁም አረንጓዴ መብራት ሂድ ለማለት ያገለግላሉ፡፡

<u>ቅድመ ዝግጅት</u>

መምህር! ለተማሪዎች የትራፊክ መብራት አጠቃቀምን የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም ትናንሽ ሞዴል የትራፊክ መብራቶች፣ ፖስተሮች እና ሥዕል ማዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

ያለፈውን ክፍል ጊዜ ስለ ተሽከርካሪ እና እግረኛ መንገድ አጠቃቀም በማስታወስ ወደ ዕለቱ ትምህርት ይግቡ፡፡ በዕለቱ ትምህርት ስለ ትራፊክ መብራት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ሥዕል 5.3 የትራፊክ መብራቶች ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ይርዷቸው፡፡ መልሶቻቸውን ከተቀበሉ በኋላ ያዘጋጁትን የትራፊክ መብራት ሞዴል በመጠቀም አጠር ያለ ማብራሪያ በሚከተለው መንገድ መስጠት ይችላሉ፡፡

የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት በተመለከተ፡-

- ቀይ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት የሚበራው አሽከርካሪዎች ለእግረኛ ማስተላለፊያ የተሰመረውን መስመር ሳያልፉ እንዲቆሙ ለማድረግ ነው፡፡
- ቢጫ የተሽከርካሪ መብራት የሚበራው ወደ መገናኛ መንገድ በመድረስ ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች ከእግረኛ መተላለፊያ መስመር ሳያልፉ በመቆም እንዲዘጋጁ ነው፡፡
- አረንጓዴ የተሽከርካሪ መብራት የሚበራው አሽከርካሪዎች ቀድመው ወደ መረጡት አቅጣጫ እንዲሄዱ ነው፡፡

  የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት በተመለከተ፡-
- ቀይ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት የሚበራው እግረኞች እንዳያቋርጡ ለማድረግ ነው፡፡
- አረንጓዴ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት የሚበራው እግረኞች ለመተላለፊያ በተሰመረ መስመር ውስጥ ብቻ አንዲያቋርጡ ለማድረግ ነው፡፡

በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ስለ ተሽከርካሪ መብራት አጠቃቀም የሚያሳየውን ሥዕል 5.4 የትራፊክ መብራት አጠቃቀም እንዲመለከቱ እና ከሥዕሉ የተረዱትን እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው:: ከመልሶቻቸው በመነሣት አጠር ያለ ክለሳ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናቅቁ፡፡

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኙ ሥዕሎች
- ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- የተሽከርካሪ እና እግረኛ መብራት ሞዴሎች
- የተሽከርካሪ እና እግረኛ መብራት ፖስተሮች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት (የተሽከርካሪ እና የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት አገልግሎትን በተመለከተ)
- እያሳዩ ማስተማር
- የቃል ጥያቄ
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የተሽከርካሪ እና የእግረኛን መብራት ለይተው እንዴት እንደሚጠቀሙ እንዲያስረዱ ያድርጉ።
- ✓ የተሽከርካሪ መብራት ቀለማትን ለይተው እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።
- ✓ የተሽከርካሪ መብራት ጠቀሜታን እንዲናገሩ ያድርጉ።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የትራፊክ ደንቦች

የትምህርቱ ጭብጥ

እግረኞች እና አሽከርካሪዎች በትራፊክ መንገድ ላይ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ደንቦች የትራፊክ ደንቦች ይባላሉ።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለተማሪዎች ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የትራፊክ ፖሊስ ባለሙያዎችን በትምህርት ቤት በመጋበዝ ሙያዊ ማብራሪያ እንዲያደርጉ ቀድመው ያመቻቹላቸው። በተጨማሪም ስለ የትራፊክ ደንቦች የሚገልጹ ፖስተሮች፣ ሥዕል እና መዝሙሮች (ተንቀሳቃሽ ምስሎችን) ይህን ድህረ ገፅ (www.youtube.com/watch?v=h91jPtjjMs4) በመጠቀም ማዘጋጀት ይኖርብዎታል።

የትምህርቱ አቀራረብ

ያለፈውን ክፍል ጊዜ ስለ ተሽከርካሪ እና እግረኛ መስተላለፊያ መብራት አጠቃቀም በማስታወስ ወደ ዕለቱ ትምህርት ይግቡ። በዕለቱ ትምህርት ስለ ትራፊክ ደንቦች በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ጥያቄዎች (የትራፊክ ደንቦች ምንድን ናቸው? የሚተገብሩትስ እነማን ናቸው?) አንብበው እንዲመልሱ ያድርጓቸው። ከመልሶቻቸው በመነሣት በሚከተለው መልኩ ስለ ትራፊክ ድንቦች ገለጻ ያድርጉ።

- እግረኞች በመንገድ ላይ ሲጓዙ ግራ አቅጣጫቸውን ይዘው መጓዝ አለባቸው
- የትራፊክ መብራት ሕጎችን ማክበር
- መንገድ ከማቋረጥ በፊት ግራና ቀኝን መመልከት
- የእግረኛ መንገድ ማቋረጫ መስመርን በመጠቀም ማቋረጥ እና የመሳሰሉት ናቸው።

በመቀጠል በተግባር አንድ ላይ የተሰጠውን የተግባር ሥራ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የእግረኛ እና የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሠርተው እንዲያመጡ በማድረግ መቼና ለምን እንደሚያገለግሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው ገለጻ እንዲያደርጉ ዕድል ይስጧቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች ስለትራፊክ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳድጉ ለማድረግ ‹‹አሽከርክር ረጋ ብለህ...›› የሚለውን መዝሙር ያዘምሯቸው። በተግባር አንድ ላይ የተሰጠውን የትራፊክ መብራት ሞዴል አሠራር ቅደም ተከተል በገለጻ ለተማሪዎች ካስረዱ በኋላ እንዲሰሩ ይዘሏቸው። ተማሪዎች ይህን የትራፊክ መብራት ሞዴል ከሠሩ በኋላ መቼ እና ለምን እንደሚጠቅሙ ይግለጹ።

በመጨረሻም የትራፊክ ደንቦችን ለመከለስ ያመች ዘንድ የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን በሚከተለው መንገድ በመጠየቅ ትምህርቱን ይደምድሙ፡፡

የትራፊክ ሕጎችን ማክበር ለምን ይጠቅማል?

የትራፊክ ደንቦችን ዘርዝሩ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ስለ ትራፊክ ደንቦች የሚገልጹ ተንቀሳቃሽ ምስሎች
- የተሽከርካሪ እና እግረኛ መንገድ አጠቃቀም የሚያሳዩ ፖስተሮች

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- የቃል ጥያቄ
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- ስለትራፊክ ደንቦች የሚገልጽ መዝሙር መጠቀም

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ የትራፊክ ደንቦችን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው፡፡
- ✓ በእግረኛ መንገድ ላይ ሲጓዙ የትራፊክ ደንቦችን እንዴት ተግባራዊ እንደሚደርጉ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡

<u>የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች</u>

<u>የይዘቱ ጭብጥ</u>

የተሽከርካሪ አደጋዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የአሽከርካሪው ችልተኝነት እና የእግረኞች መዘናጋት ዋነኛ መንሥኤዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ራሳቸውን ከተሽከርካሪ አደጋ ለመከላከል የተለያዩ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ግራ አቅጣጫን ይዞ መጓዝ፣ የትራፊክ መብራት ሕጎችን ማክበር እና የተሽከርካሪ መንገድ ከማቋረጥ በፊት ቀኝና ግራን መመልከት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለአንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሚመጥን ሁኔታ በትምህርት ቤት ውስጥ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብራት መዘጋጀት አለባቸው፡፡

<u>ቅድመ ዝግጅት</u>

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤን ሊያመለክቱ የሚችሉ ልዩ ልዩ ጋዜጣዎችን፣ ሥዕሎችን፣ መጽሔቶችን እና ፖስተሮችን ያዘጋጁ፡፡

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤ ምን ሊሆን እንደሚችል በመጠየቅ ተማሪዎችን ያሳትፉ:: በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የተቀመውን ሥዕል 5.5 የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎችን አስተውለው ከተመለከቱ በኋላ የተገነዘቡትን ተራ በተራ የተመለከቱትን ነገር እንዲገልጹ ያድርጓቸው:: በመማሪያ መጽሐፉ የተሰጠውን የቡድን ውይይት ሁለት ተማሪዎች በቡድን እንዲደራጁ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲወያዩበት ይስጧቸውቸው::

1. የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች ምን ምን ናቸው?
2. የተሽከርካሪ አደጋ ምን ጉዳት ያስከትላል?

በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ስለትራፊክ አደጋ መንሥኤዎች የሚያሳየውን ሥዕል 5.5 የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች እንዲመለከቱ በማደረግ የተገነዘቡትን ይጠይቋቸው:: ተማሪዎች ከላይ የተወያዩባቸውን ጥያቄዎች እና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተቀመጠውን ሥዕል በማዋሐድ እንዲሁም መልሶቻቸውን በመቀበል በሚከተለው መንገድ ገለጻ ያድርጉላቸው::

ተማሪዎች በተሽከርካሪ መንገድ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የትራፊክ ሕግና ደንብን በመገንዘብ ለትራፊክ አደጋ እንዳይጋለጡ ደኅንነታቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል:: የትራፊክ አደጋ መንሥኤዎች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- ሕፃናት በተሽከርካሪ መንገድ አካባቢ በሚጓዙበት ጊዜ በትኩረት እና በንቃት አካባቢያቸውን ያለመቃኘት ችግር (የትኩረት ማነስ)
- ሲደናገጡ ሮጠው ለማምለጥ ብለው ጉድጓድ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ::
- የትራፊክ ሕግና ደንብን ጥሰው በዘፈቀደ የተሽከርካሪን መንገድ ለማቋረጥ መሞከር
- በተሽከርካሪ መንገዶች አካባቢ ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ ውስጥ ሆነው የተለያዩ ጨዋታዎችን መጫወት
- የተደናበሩ እንስሳትን ለመሸሽ ሲሉ በድንጋጤ ዘለው የተሽከርካሪ መንገድ ውስጥ መግባት
- እያወሩ ሲጓዙ በመዘናጋት የተሽከርካሪ መንገድ ውስጥ መግባት

በአጠቃላይ የተሽከርካሪ አደጋን ለመቀነስ የትራፊክ ደንቦችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገለጻ በማድረግ እንዲሁም ስለተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች እና ጉዳቶቻቸው የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ያጠቃልሉላቸው::

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ስለተሽከርካሪ አደጋ የሚያብራሩ በራሪ ወረቀቶች
- በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኙ ሥዕሎች
- የተሽከርካሪ አደጋዎችን የሚያሳዩ ፖስተሮች
- የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎችን የሚያሳዩ ፖስተሮች
- ስለተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች እና ጉዳቶቻቸው የሚገልጹ መዝሙር

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት (ስለተሸከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች እና ጉዳቶቻቸው)
- የቃል ጥያቄ
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- ስለተሸከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች እና ጉዳቶቻቸው የሚገልጽ መዝሙር መጠቀም

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የተሸከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች ምን ምን እንደሆኑ ይጠይቋቸው።
- ✓ የተሸከርካሪ አደጋን ለመቀነስ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለክፍል ለጓደኞቻቸው ፅብረቃ እንዲያቀርቡ ይዘሏቸው።
- ✓ ስለተሸከርካሪ አደጋ ጉዳት ከአካባቢያቸው የተመለከቱትን ወይንም የሰሙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ይጋብዟቸው።
- ✓ መልመጃዎችን መስጠት
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የተግባር አንድ መልሶች

1. ግራና ቀኝ ዞሮ በመመልከት መኪና ካለፈ በኋላ በመንገደኛ መተላለፊያ ያቋርጣሉ።
2. ግራና ቀኝ

የመልመጃ 5.1 መልሶች

ሀ. የአዛምድ መልሶች

1. ሐ
2. ሀ
3. ለ

ለ. የምርጫ መልሶች

1. ለ
2. ሐ

የተግባር ሁለት መልስ

1. የትራፊክ መብራት ሞዴል ሠርተው ካመጡ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው ማብራሪያ ሲያቀርቡ ይከታተሉ።

የውይይት ሁለት መልሶች

1. መንገድ ሲያቋርጡ ቀኝና ግራን አለማየት
    - የተሽከርካሪ መንገድ ላይ የተለያዩ ጨዋታዎችን መጫወት
    - የእግረኛ መንገድ ማቋረጫ መስመር ሳይጠቀሙ ማቋረጥ የተሽከርካሪ አደጋ መንሥኤዎች ናቸው።
2. የተሽከርካሪ አደጋ በሰው ሕይወት እና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል።

5.2 ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?

የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት፡-17

የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- ✓ ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገነዘባሉ።
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ሐዘኔታ እና ፍቅር ያሳያሉ።

ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?

የይዘቱ ጭብጥ

ኤች.አይ.ቪ የሰውነትን ሕመም የመከላከል አቅም በማዳከም ሰውነታችን ለተለያዩ ሕመሞች በማጋለጥ በሕይወት የመኖር ዕድልን የሚቀንስ አደገኛ ቫይረስ ነው። ይህ ቫይረስ ሰውነታችንን ለብዙ ሕመሞች ካጋለጠ በኋላ ኤድስ የሚል ስያሜ ይሰጠዋል። ስለዚህ ኤች.አይ.ቪ የሕመሙ አምጪ ቫይረስ ሲሆን ኤድስ ደግሞ የሕመሙ መጠሪያ ስም ነው።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ለአንደኛ ክፍል በሚመጥን ደረጃ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት የሚገልጹ ሥዕሎችን፣ ፖስተሮችን፣ በራሪ ወረቀቶችን እና የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ማዘጋጀት ይኖርብዎታል።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ተማሪዎች አምስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሠርቱ በማድረግ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት ኤች.አይ.ቪ ምንድን ነው? ኤድስስ ምንድን ነው? በማለት እንዲወያዩ ይጠይቋቸው። ያላቸውን ግንዛቤ ከተወያዩ በኋላ የተገነዘቡትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። የውይይታቸውን ግብረመልስ በመቀበል በሚከተለው መንገድ ገለጻ ያድርጉላቸው።

ኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ ሲተነተኑ፡-

- **ኤች** (Human) - **የሰው ዘር በሙሉ**
- **አይ** (Immunodeficiency) - **ሕመም የመከላከል አቅም የሚያዳክም**
- **ቪ** (virus) - **ቫይረስ**

ስለዚህ ኤች.አይ.ቪ ማለት የሰው ልጆችን በተፈጥሮ ሕመምን የመከላከል አቅም የሚያዳክም ቫይረስ ነው፡፡

- **ኤ** (Acquired) - **በዘር የማይተላለፍ ሕመም (አብሮ ያልተወለደ ነገር ግን በወሊድ ጊዜ ወይንም ከተወለድን በኋላ የሚከሰት ሕመም)**
- **ዲ** (Immunodeficiency) - **የሰውነት ሕመም መከላከል አቅም ዕጥረት**
- **ስ** (syndrome) - **የተለያዩ የሕመም ምልክቶች ስብስብ**

ኤድስ ማለት የተለያዩ ሕመሞች ምልክት ጥርቅም ነው፡፡

በመጨረሻም ስለ ኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ ምንነት ክለሳ በማድረግ ያጠቃልሉ፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- **ስለኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ የሚያሳዩ ሥዕሎች**
- **ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚገልጹ ፖስተሮች**
- **ስለኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ ምንነት የሚገልጹ በራሪ ወረቀቶች**
- **ስለኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ ምንነት የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች**

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- **የቃል ጥያቄ**
- **የቡድን ውይይት (በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት ላይ)**
- **ገለጻ**
- **ጥያቄና መልስ**

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ **የኤች.አይ.ቪን እና የኤድስን ምንነት ይጠይቋቸው፡፡**
- ✓ **በኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ ምንነት ዙሪያ የቡደን ሥራ ይስጧቸው፡፡**
- ✓ **የኤች.አይ.ቪን እና የኤድስን ልዩነት ይጠይቋቸው፡፡**

- ✓ በኤች.አይ.ቪ እና ኤድስ መካከል ያለውን ትስሥር ይጠይቋቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

የኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች

የይዘቱ ጭብጥ

ኤች.አይ.ቪ የሰውነትን ሕመም የመከላከል አቅም የሚያዳክም ቫይረስ ሲሆን በተለያዩ መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል። በዚህ ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች የኤች.አይ.ቪን መተላለፊያ መንገዶች ለተማሪዎች ማስገንዘብ በጣም ትልቅ ጥረትን ይጠይቃል።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ለአንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሚመጥን ሁኔታ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት አለበዎት። ለምሳሌ፡- ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች የሚገልጹ ሥዕሎችን፣ ቻርቶችን እና መዝሙሮች (ተንቀሳቃሽ ምስሎችን) ይህን ድህረ ገፅ (www.youtube.com/watch?v=2e70mkdmwJw ወይንም www.youtube.com/watch?v=sDSyUPerg0c) በመጠቀም ማዘጋጀት ይኖርብዎታል።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ይህን ንዑስ ርዕስ ቀለል ባለ መልኩ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ጥረት ማድረግ ይኖርብዎታል:: ተማሪዎች ጉዳዩን በቀላሉ እንዲረዱት ለማድረግ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኘውን ሥዕል 5.6 የኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ የሆኑ እና ያልሆኑ መንገዶች እንዲመለከቱ ማድረግ እና የማነቃቂያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መንደርደር ይችላሉ። ለምሳሌ፡- ኤች.አይ.ቪ ከሕመምተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው እንዴት እንደሚተላለፍ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ እና ሐሳባቸውን በመቀበል ይበልጥ ተሳትፎአቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ እንዲሁም በቡድን በቡድን በመከፋፈል ኤች.አይ.ቪ እንዴት ሊተላለፍ እንደሚችል የቡድን ውይይት ሶስት መሰረት በማድረግ እንዲወያዩበት መርዳት ተገቢ ነው፡ ፡ የኤች.አይ.ቪ መከላከያ መንገዶችን የሚገልጹ የተለያዩ መዝሙሮችንም ያዘምሯቸው። ከዚያም የውይይታቸውን ፍሬ ሐሳብ በተወካዮቻቸው በኩል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በመጨረሻም የኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶችን ጠቅለል አድርገው በበቂ ሁኔታ ማብራሪያ በመስጠት እና ተማሪዎችን ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መዝሙር (‹‹ማለባበስ ይቅር...›› እና ‹‹መላ መላ መላ...››) የሚለውን እንዲያዜሙ እና መልዕክቱን እንዲገነዘቡ በማድረግ ያጠቃልሉ።

አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ➢ ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገድ የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ➢ ኤች.አይ.ቪን ሊያስተላልፉ የሚችሉ ቁሳቁሶች
- ➢ ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገድ የሚያብራሩ በራሪ ወረቀቶች
- ➢ ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች የሚገልጹ መዝሙሮች

የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች

- ገለጻ
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ውይይት (ስለ ኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች)
- ጥያቄና መልስ
- መዝሙር (ስለ ኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች)

የምዘናና ክትትል ስልቶች

- ✓ የኤች.አይ.ቪ መከላከያ መንገዶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ።
- ✓ በተወያዩበት መሠረት የኤች.አይ.ቪን መተላለፊያ መንገዶች መግለጻቸውን መገምገም።
- ✓ በቡድን በቡድን በመሆን ስለኤች.አይ.ቪ መተላለፊያ መንገዶች እንዲወያዩ ጋብዘው መከታተል።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዘግቡ።

ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት

የይዘቱ ጭብጥ

በኤች.አይ.ቪ የተጠቃ ሰው የተለያዩ ሕመሞችን ምልክት ሊያሳይ ስለሚችል ተመሳሳይ የሆኑ የሕመም ምልክቶችን ለይቶ ለመግለፅ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። አንድ ግለሰብ በኤድስ ሕመም ሲታመም ቤተሰብ ላይ ብዙ ጫና ሊያመጣ ይችላል። ለምሳሌ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ግለሰብ (እናት ወይንም አባት) ሲታመሙ የቀሪው ቤተሰብ መኖር ህልውና ጥያቄ ውስጥ ይገባል። ምክንያቱም ሠርቶ ቤተሰብን የሚያስተዳድር ግለሰብ ጤናው በዚህ ሕመም ሲዛባ ቤተሰብ በሙሉ ኑሮው ይቃወሳል። በተጨማሪም ልጆችን ያለ ወላጆች፤ ወላጆችን ያለ ልጆች ያስቀራል።

ቅድመ ዝግጅት

መምህር! ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለተማሪዎች ለማስገንዘብ ይረዳዎት ዘንድ ለመርጃ መሣሪያነት የሚጠቀሟቸውን ቁሳቁሶች በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል። ስለዚህ በኤች.አይ.ቪ የተጎዳ ሰውነት ያላቸውን ሰዎች ሥዕል/ፎቶዎች ባይጠቀሙ ይመረጣል። ወደ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ኤች.አይ.ቪ የሚያደርሰውን ጉዳት በጽሑፍ የሚገልጽ አጭር ታሪክ፣ በራሪ ወረቀቶች እና ቻርት ያዘጋጁ።

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ወደ ዕለቱ የትምህርት ይዘት ከመግባትዎ በፊት ቀደም ሲል ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት ተጠቅመው እንዲሳተፉ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ያነቃቋቸው። ለምሳሌ፦ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቤተሰብ ላይ ምን ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል መጠየቅ። ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡ ጥንድ ጥንድ በመሆን ቀጥሎ በተሰጠው የቡድን ውይይት ሁለት ጥያቄዎች ላይ

ተወያይተው መልሶቻችውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት የሚገልጹ መዝሙሮችን አዘጋጅተው ያዘምሯቸው፡፡

በአቅራቢያዎ ከሚገኙ የጤና ተቋማት ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት የጤና ባለሙያ በመጋበዘ ለተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርብዎታል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤታቸው በሚገኘው የፀረ-ኤድስ ክበብ መርሐግብር ላይ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መዝሙሮች በሚኒሚዲያ በማስተላለፍ ግንዛቤያቸው እንዲጨምር ያመቻቹላቸው፡፡ እንዲሁም ከመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ባሉት የመወያያ ነጥቦች እንዲወያዩ በማድረግ የውይይታቸውን ፍሬ ሐሳብ በቡድን ተወካዮቻቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው ፅብረቃ እንዲያቀርቡ ይርዷቸው፡፡ በመጨረሻም ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት በሚከተለው መልክ ያጠቃልሉ፡፡

በኤች.አይ.ቪ የተጠቃ ግለሰብ ለተለያዩ ጉዳቶች ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

- የሰውነት ክብደት መቀነስ
- የጉሮሮ ቁስለት
- ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ተቅማጥ
- ለረዥም ወራት የሚቆይ የሰውነት ተኩሳት መኖር
- ከፍተኛ የድካም ስሜት መኖር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ይህ ሕመም ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን ያስከትላል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

1. በጤናው ዘርፍ
2. በግብርናው ዘርፍ
3. በትምህርትው ዘርፍ
4. በኢኮኖሚው ዘርፍ የሚደርሰው ጉዳት በዋናነት ሊገለጽ ይችላል፡፡

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት የሚገልጽ በራሪ ወረቀት
- ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት የያዘ ቻርት
- ስለኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ሰለሚያደርሰው ጉዳት የሚገልጹ መዝሙሮች

<u>የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- ገለጻ
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሰውንት ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ዙሪያ ገለጻ እንዲያደርጉ የጤና ባለሙያዎችን በመጋበዝ
- የቃል ጥያቄዎች

- የቡድን ውይይት (ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት)
- በጥያቄና መልስ

<u>የምዘናና ክትትል ስልቶች</u>

- ✓ በቡድን ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት እንዲወያዩ ይዘሏቸው።
- ✓ በውይይታቸው መሠረት የኤች.አይ.ቪን የጉዳት መጠን እንዲገልጹ ያድርጓቸው።
- ✓ ኤች.አይ.ቪ በሰውነት ላይ ስለሚያደርሰው ጉዳት እንዲዘረዝሩ ዕድል ይስጧቸው።
- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ።

በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሕፃናት ሐዘኔታ እና ፍቅር ማሳየት

<u>የይዘቱ ጭብጥ</u>

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ አብሮ በመብላት፣ አብሮ በመተኛት፣ አብሮ በመጫወት እና በትንፋሽ ስለማይተላለፍ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሕመማንን መንከባከብ ያስፈልጋል። በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተጠቁ ሰዎች (ግለሰቦች) ከቤተሰብ (ከማኅበረሰብ) ልዩ ድጋፍ እና እንክብካቤ ከተደረገላቸው እንደማንኛውም ጤናማ ሰው የዕለት ተዕለት ኑሮአቸውን ማከናወን ይችላሉ። ስለሆነም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሕመማን በሥነ-ልቦና እንዳይጎዱ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች አቅም በፈቀደ መጠን መርዳት ያስፈልጋል። በተለይም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ በመሆናቸው በሥነ-ልቡና እንዳይጎዱ ድጋፍ፣ ትብብር፣ ሐዘኔታ፣ ፍቅር፣ ማቅረብና ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ ይኖርብናል።

<u>ቅድመ ዝግጅት</u>

መምህር! ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ላለባቸው ሰዎች (የማኅበረሰብ ክፍሎች) ርኅራኄን፣ ሐዘኔታን እና ፍቅርን ሊያስገነዝቡ የሚችሉ የመርጃ መሣሪያዎች ክፍል ከመግባትዎ በፊት ያዘጋጁ።
ለምሳሌ፦ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ቻርቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ መዝሙሮች እና ከጤና ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

<u>የትምህርቱ አቀራረብ</u>

መምህር! ወደ ዕለቱ ንዑስ ርዕስ ከመግባትዎ በፊት ከቀድሞ ዕውቀታቸው በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ስላለባቸው ሕፃናት እና ቤተሰቦቻቸው ምን ዓይነት ድጋፍ እና እንክብካቤ ቤተሰባቸው (ማኅበረሰቡ) እንደሚያደርግላቸው የሚያውቁትን እንዲናገሩ ዕድል ይስጧቸው። በመቀጠልም አንድ ተማሪ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን የማሚት ቤተሰብ ታሪክ እንዲያነብ በማድረግ አምስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሠርቱ እና የቡድን ውይይት አራት መወያያ ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው መልሶቻቸውን ከቡድኑ አንድ አባል በመወከል ዕብረቃ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። በመጨረሻም የተማሪዎች ትክክለኛ የሆኑ ግንዛቤዎችን በመያዝ እንደሚከተለው ያጠቃልሉ። ተማሪዎች የማሚት ቤተሰብ ፍቅርን እና ሀዘኔታን ከማሳየት ባሻገር አስቴር ወደ አቅራቢያዋ ጤና ተቋም በመሔድ የዕድሜ ማራዘሚያ መድሐኒት በማግኘት ወደ ቀድሞ ጤናዋ በመመለስ የተለመደውን የዕለት ተዕለት ኑሮዋን ማስቀጠል እንደምትችል መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት፡-

- ✓ **ፍቅር መስጠት**
- ✓ **አብሮ መጫወት**
- ✓ **አብሮ መብላት**
- ✓ **እንዲያጠኑ መርዳት እና በሥነ-ልቦና እንዳይጎዱ ድጋፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡**

<u>አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች</u>

- ➢ **ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ስላለባቸው ግለሰቦች የሚገልጽ በራሪ ወረቀት**
- ➢ **ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ስላለባቸው ግለሰቦች የሚገልጽ ቻርት**
- ➢ **ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ስላለባቸው ግለሰቦች የሚገልጹ መዝሙሮች**

<u>የማስተማርያ ሥነ-ዘዴዎች</u>

- **ገለጻ**
- **የጤና ባለሙያ በመጋበዝ (በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሕፃናት ሐዘኔታ እና ፍቅር ማሳየት)**
- **የቃል ጥያቄዎች**
- **የቡድን ውይይት (በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሕፃናትና ቤተሰቦቻቸው ሐዘኔታ እና ፍቅር ማሳየት)**
- **በጥያቄና መልስ**

<u>የምዘናና የክትትል ስልቶች</u>

- ✓ **በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ስላለባቸው ቤተሰቦች እና ልጆቻቸው መደረግ ስላለበት ሐዘኔታ እና ፍቅር እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡**
- ✓ **በቡደን ሆነው በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ስላለባቸው ሕፃናት ሊደረጉ ስለሚገቡ ድጋፎች እንዲወያዩ ይዘዟቸው፡፡**
- ✓ **በተወያዩት መሠረት በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ላለባቸው ሕፃናት መደረግ ስላለበት ሐዘኔታ እና ፍቅር በጭውውት መልክ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቅርቡ ያድርጉ፡፡**
- ✓ **ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን ይመዝግቡ፡፡**

1.

የውይይት ሦስት መልሶች

1. በጋራ ስለታማ ነገሮችን በመጠቀም

   የጥርስ ብሩሽን በጋራ በመጠቀም

   በደም ንክኪ

2. የሰውነትን ሕመም የመከላከል የተፈጥሮ አቅም በማዳከም ለብዙ ሕመሞች እንድንጋለጥ ያደርጋል።

የውይይት አራት መልሶች

1. የትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል።

   ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ ይችላሉ።

   ለቤተሰባቸው የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የተለያዩ ሥራዎችን (የቀን ሥራ፣ ልብስ ማጠብ ወ.ዘ.ተ...) በመሥራት ለጉልበት ብዝበዛ ሊጋለጡ ይችላሉ።

2. እንክብካቤ ማድረግ ፣ ፍቅር መስጠት ፣ የኢኮኖሚ ድጋፍ ማድረግ

3. የሕክምና ክትትል በአግባቡ ማድረግ አለባት ፣ ተስፋ አለመቁረጥ ፣ ሁኔታዎች እያደር እየተሻሉ እንደሚሆኑ ተስፋ ማድረግ ፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ካለባቸው ሰዎች ጋር መመካከር/ውይይት ማድረ

የመልመጃ 5.2 መልሶች

<u>እውነት/ሐሰት መልሶች</u>

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
2. እውነት

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልሶች

ሀ. የምርጫ መልሶች

1. ለ
2. ለ
3. ለ
4. ሀ
5. ሐ

ለ. የግለፅ መልሶች

1. ኤድስ

   - ኤድስ በኤች አይ ቪ ቫይረስ ስንጎዳ የሚመጣ ህመም መጠሪያ ነው

2. የተሸከርካሪ መንገድ ደንቦች የሚባሉት

   - የተሸከርካሪ መንገድ ሲያቋርጡ ቀኝና ግራ መመልከት
   - የተሸከርካሪ መንገድ ሲያቋርጡ ለእግረኛ የሚፈቅድ አረንጓዴ መብራቱን ማስተዋል
   - ከተለያዩ ልብን ከሚሰርቁ ሐሳቦች ውጪ በመሆን በጥንቃቄ የተሸከርካሪ መንገድ ማቋረጥ

3. የትራፊክ መብራት ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ለምሳሌ፡-

   - የተሸከርካሪ መንገድ ፍሰቱን ለመቆጣጠር
   - በሕይወት እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ይረዳል
   - የተሸከርካሪ መንገድ ለሰው እና ለተሸከርካሪ የሚፈቀድበትን ጊዜ ለመወሰን

4. ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ መንገዶች

   - ስለታማ ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም
   - የኤች.አይ.ቪ ሕመምተኛ ደም አለመንካት
   - የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በጋራ አለመጠቀም

5. ኤች.አይ.ቪ የሕመሙ አምጪ ቫይረስ ሲሆን ኤድስ ደግሞ የሕመም ስም ነው፡፡

6. ኤች.አይ.ቪ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት፡-

   - ✓ ፍቅር መስጠት
   - ✓ አብሮ መጫወትና መብላት
   - ✓ እንዲያጠኑ መርዳት እና በሥነ-ልቡና እንዳይጎዱ ድጋፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

- አካባቢ ሳይንስ የተማሪ መጽሐፍ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍል የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2006 ዓ.ም
- አካባቢ ሳይንስ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍል የመምህር መምሪያ የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2006 ዓ.ም
- የኅብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 1997 ዓ.ም
- የኅብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል በክልል 14 ትምህርት ቢሮ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር መምሪያ ተዘጋጀ አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም
- ቶፕ መሠረታዊ የአካባቢ ሳይንስ አጋዥ መጽሐፍ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል 2008 ዓ.ም በድጋሚ 5ኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ
- መሪ የአሸከርካሪዎች የስልጠና መጽሐፍ በአዲሱ የ2010 ዓ.ም የአሸከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ አዋጅ መሰረት የተዘጋጀ
  - https://am.wikipedia.org/wiki /የኢትዮጵያ እጽዋት
  - www.youtube.com/watch?v=h91jPtjjMs4 (Music video)
  - www.youtube.com/watch?v=2e70mkdmwJw (Music video)
  - www.youtube.com/watch?v=sDSyUPerg0c (Music video)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የይዘት ፍሰት

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.

ምዕራፍ	የመማር ይዘት መስኮች	አንደኛ ክፍል	ሁለተኛ ክፍል	ሦስተኛ ክፍል	ዐራተኛ ክፍል	አምስተኛ ክፍል	ስድስተኛ ክፍል
አንድ	መገኛ	• የመገኛ ምንነት	• የወረዳችን መገኛ	• የክፍለ ከተማችን መገኛ	• የከተማችን መገኛ	• የኢትዮጵያ አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ	• የምሥራቅ አፍሪካ አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ
ሁለት	ሳይንስን መገንዘብ	• የሰውነታችን ክፍሎች • ምግብና ጥቅሙ • የብርሃን ምንነት	• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንና • የስሜት አካላቶቻችን • የቁሶች አካላዊ ባሕርያት • የብርሃን ምንጮች	• ምግብና ጤና • የምግብ ጥቅም • ዐራቱ የምግብ ምድቦች (ጥራ ጥሬዎች፣ ሥጋ፣ ወተት፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች) • የምግብ ብክለት • የቁስ አካል ሁኔታዊ ለውጥ (ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች) • የብርሃን ጥቅም	• ምግብና ጤናማ አኗኗር • ውስጣዊ የሰውነት አባል አካላት • አስፈላጊ የምግብ ንጥረ ነገሮች • የተመጣጠነ አመጋገብ • የቁስ አካል አካላዊና ኬሚካዊ ባሕርያት • የብርሃን ባሕርያትና ጥላ	• የሥርዓተ ልመት ዋና ዋና ክፍሎች • የውሃ ጥቅም • የጉልበት ምንጮች	• የደም ዝውውር • ጉርምስና • የአየር ምንዝሮች • ሥርዓተ ትንፈሳ • ጉልበትና ጥቅሙ
ሦስት	ተፈጥሮአዊ አካባቢ	• የአየር ሁኔታ • ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች •ለማዳና የዱር እንስሳት • የመኖሪያ አካባቢያችንን መንከባከብ	• የአየር ሁኔታእና የአየር ንብረት • በወረዳችን የሚገኙ እንስሳ ትና ዕፅዋት • በወረዳችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶች • የወረዳችንን አካባቢ መንከባከብ	• የክፍለ ከተማችን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የክፍለ ከተማችንን አካባቢ መንከባከብ	• የከተማችን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የከተማችንን አካባቢ መንከባከብ	• የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የኢትዮጵያን አካባቢ መንከባከብ	• የምሥራቅ አፍሪካ ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢ መንከባከብ

ምዕራፍ	የመማር ይዘት መስኮች	አንደኛ ክፍል	ሁለተኛ ክፍል	ሦስተኛ ክፍል	ዐራተኛ ክፍል	አምስተኛ ክፍል	ስድስተኛ ክፍል
ዐራት	ማኅበራዊ አካባቢ	• ቤተሰብና ማኅበረሰብ • አካባቢያችን	• ቤተሰብና ማኅበረሰብ በወረዳችን • አካባቢያችን	• የክፍለ ከተማችን ሕዝቦችና ባህሎች • የክፍለ ከተማችን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች	• የከተማችን ሕዝቦችና ባህሎች • የከተማችን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች	• የባህል ብዝኃነት በኢትዮጵያ • ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ	• የሕዝብ ብዙኃነት በምሥራቅ አፍሪካ • ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በምሥራቅ አፍሪካ
አምስት	ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ /ኤድስ	• የኬሚካል አጠቃቀም ደኅንነት • ኤች አይ ቪ እና ሌሎች ተላላፊ ሕመሞች • ድርቅና ረሃብ በከተማችን	• የኬሚካል አጠቃቀም ደኅንነትና አደንዛዥ ዕፅ • ድርቅና ረሃብ በኢትዮጵያ • ኀጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወረዳችንና በክፍለ ከተማችን	• አደንዛዥ ዕፅና ሱሰኝነት • ድርቅና ረሃብ በምሥራቅ አፍሪካ • ኀጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በከተማችንና በሀገራችን

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

የአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ምዕራፍ አንድ መገኛ	ምዕራፍ ሁለት ሳይንስን መገንዘብ	ምዕራፍ ሦስት ተፈጥሮአዊ አካባቢ	ምዕራፍ ዐራት ማኅበራዊ አካባቢ	ምዕራፍ አምስት ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች
• የመገኛን ፅንሰ ሐሳብ መግለጽ • ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ አቅጣጫዎችን መለየት • የአንድ ቦታ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር እንዴት እንደሚወሰን ማብራራት • በዙሪያችን የሚገኙ ነገሮችን አቅጣጫ ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ በማለት መለየት • በትምህርት ቤት የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ገጽታና መገኛ መለየት • የትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤትንና የጎረቤት መገኛን መለየት • የአካባቢን ንድፍ ካርታ መሥራትና የትምህርት ቤት አቅጣጫን ማሳየት	• ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን መጥራት • የስሜት አካላትን መለየትና ጥቅማቸውን መናገር • የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና መለየት • የጨለማን ምንነት መገንዘብ	• የወቅቶችን፣ የቀንና የማታን ምንነት መግለጽ • ቀስተ ደመናና ጎርፍ ተፈጥሮዊ ክስተቶች መሆናቸውን በማጥናት መገንዘብ • ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕርያት መግለጽ • ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች መለየት • የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት መለየት • እንስሳትን በአካል ሽፋናቸው፣ በእንቅስቃሴያቸውና በእግራቸው ብዛት መመደብ • የቤት ውስጥ የንጽሕና ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመጸዳጃ ቤት ንጽሕና መጠበቅ መቻል	• የቤተሰብ አባላትን መዘርዘር • የቤተሰብን መሠረታዊ ፍላጎት መግለጽ • የትምህርት ቤት ግቢን መለየት • በትምህርት ቤት ከአቻዎቻቸው ጋር የርስ በርስ ግንኙነት በማዳበር ተግባራትን ማከናወን • የቤተሰብ አባላት መብትና ኃላፊነትን መግለጽ • በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ ቦታዎችን የሚያመለክቱ ሥዕሎችን በመሥራት ደኅንነታቸውን የሚጠብቁበትን መንገድ ማሳየት	• የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መተግበር • ኤች. አይ. ቪ.. በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መገንዘብ • ኤች.አይ.ቪ.. በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ኀዘኔታንና ፍቅርን ማሳየት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የአንደኛ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርቶች

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ አንድ ፡- የአካባቢያችን መገኛ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 42

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ ፡- • የመገኛን ምንነት ዕንሰ ሐሳብ ይገልጻሉ፡፡ • ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ አቅጣጫዎችን ይለያሉ፡፡ • የአንድ ቦታ መገኛ ከሌሎች ቦታዎች አንጻር እንዴት እንደሚወሰን ያብራራሉ፡፡ • በዙሪያችን የሚገኙ ነገሮችን አቅጣጫ ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ በማለት ይለያሉ፡፡ • በትምህርት ቤት የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ገጽታና መገኛ ይለያሉ፡፡ • የትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤትንና የጎረቤት መገኛን ይለያሉ፡፡ • የአካባቢን ንድፍ ካርታ መሥራትና የትምህርት ቤት አቅጣጫን ያሳያሉ፡፡	የአካባቢያችን መገኛ • የመገኛ ምንነት • ዐራት አቅጣጫዎች (ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ) • ከትምህርት ቤታችንና ከወረዳችን አንጻንር የቤታችን መገኛ • በዙሪያችን የሚገኙ ጎረቤቶቻችን መገኛና ስም	• ለተማሪዎች ስለ መገናኛ ምንነት እንዲገልጹ መጠየቅ • ተማሪዎች በንድፍ ካርታና ሥዕሎች የቤታቸውንና የትምህርት ቤታቸውን መገኛ እንዲያመለክቱ ማሠራት • ተማሪዎች በጥንድ ወይንም በቡድን ሆነው የተለያዩ ቦታዎች ስምን የያዘ ንድፍ ካርታ በመጠቀም የሚገኙበትን ቦታ እንዲገምቱ ማድረግ • ተማሪዎች በንድፍ ካርታ ላይ የተመለከቱ አካባቢዎችን፣ ዕፅዋትንና ሰው ሠራሽ ነገሮችንና ሌሎች ነገሮችን በመመልከት መገኛቸውን እንዲገልጹ ማድረግ • ተማሪዎች የንድፍ ካርታ ተገጣጣሚ ሥዕሎችን በመጠቀም አካባቢያቸውን እንዲያመለክቱ ማድረግ • ተማሪዎች ቀላል ንድፍ ካርታ በመሣል የቤታቸውንና የትምህርት ቤታቸውን አንጻራዊ መገኛ እንዲያመለክቱ ማድረግ • ተማሪዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም አቅጣጫ ስለሚለይባቸው ዘዴዎች እንዲወያዩ ማድረግ	• ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራት ሲያከናውኑ በመመልከት እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ •ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን ለማመልከት የሚያደርጉት ጥረት መሻሻሉን መከታተል •ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲያሻሽሉ ግልጽ ግብረ መልስ መስጠት •ተከታታይ ተግባራት መስጠት ለምሳሌ የትምህርት ቤታቸውንና የወረዳቸውን መገኛ የሚያሳይ ንድፍ ካርታ እንዲሠሩ ማድረግ •የክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘና ማድረግ

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ ሁለት፡- ሳይንስን መገንዘብ **ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 54**

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ፡- • ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት አካላትን ይጠራሉ • የስሜት አካላትን በመለየት ጥቅማቸውን ይናገራሉ • የስሜት አካላት ያላቸውን ዝምድና ይለያሉ፡፡ • የግል ንጽሕና በመረዳት ይተገብራሉ • የጨለማን ምንነት ይገነዘባሉ	2.1 የሰውነታችን ክፍሎች • ምንነትን መግለጽ • ራስ፣ ፊት፣ ጸጉር፣ ጆሮ፣ አንገት፣ ግንባር፣ ዐይን፣ አፍንጫ፣ አፍ... • ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን መንከባከብ 2.2 የግል ንጽሕናን መጠበቅ • ስለሌሎች ሰዎች ጤንነት ኃላፊነት መውሰድ 2.3 የብርሃን ምንነት	• ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፋቸውን እንዲያነቡ፣ እንዲወያዩ ከማድረግ በተጨማሪ በገለጻና በሠርቶ ማሳያ መንገድ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ • ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡- • የሰውነታችን ውጫዊ አካላት እነማን ናቸው? • ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ጥንቃቄ የምናደርግባቸውን መንገዶች ዘርዝሩ፡፡ • ተማሪዎች ከተወያዩ በኋላ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን በመዘርዘር ተግባሮቻቸውን እንዲናገሩ ማበረታታት • የሰውን ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን የሚያመላክቱ ሥዕሎችን፣ወላይ ቅርጾችን የመሳሰሉትን ማሳየት • በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? • የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎችን በመጠቀም ማስተማር	• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ውጫዊ የሰውነት ክፍልን ከሚያመላክተው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጋር ሲያወዳደሩ መመልከት • ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን እንዲያመላክቱ በመጠየቅ የተሳትፏቸውን መረጃ መያዝ • በውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራት ላይ ሲወያዩ መከታተል • በብርሃንና ጨለማ ልዩነት ላይ ሲወያዩ ያላቸውን መረዳት መገምገም • ለጥያቄዎች ከሚሰጡት መልስ በመነሳት ተገቢውን ግብረመልስ መስጠት መማራቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ ማመላከት

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ ሦስት ፡- ተፈጥሮአዊ አካባቢ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 54

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ፡- • የወቅቶችን፣ የቀንና የማታን ምንነት ይገልጻሉ • ቀስተ ደመናና ጎርፍ ተፈጥሮዊ ክስተቶች መሆናቸውን በማጥናት ይገነዘባሉ • ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ባሕርያት ይገልጻሉ • ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ይለያሉ • የለማዳ እንስሳትን አገልግሎት ይለያሉ • እንስሳትን በአካል ሽፋናቸው፣ በእንቅስቃሴያቸውና በእግራቸው ብዛት ይመድባሉ • የቤት ውስጥ የንጽሕና ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመጸዳጃ ቤት ንጽሕና ይጠብቃሉ	3.1 የአካባቢያችን የአየር ንብረት • የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት • የአየር ንብረት ይዘቶች • የአየር ንብረት ክልሎች • የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች 3.2 ሕይወት ያላቸው ነገሮች • ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባሕርያት (መንቀሳቀስ፣ አየር ያስፈልጋቸዋል፣ ስሜት አላቸው፣ ያድጋሉ፣ ይራባሉ፣ ይጸዳዳሉ፣ ምግብ / ጉልበት ያስፈልጋቸዋል • የእንስሳት ምድብ • በአካባቢያችን የሚገኙ እንስሳትና የሚራቡበት ወቅት 3.3 ንጽሕናና የግል ንጽሕና • ቆሻሻን ማስወገድና መልሶ መጠቀም	• ስለአየር ሁኔታና ስለ አየር ንብረት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲናገሩ መጠየቅ • ስለኢትዮጵያ አየር ንብረት ገለጻ እንዲያደርጉ መጠየቅ • የዝናብ ሥርጭት ካርታን በመጠቀም የኢትዮጵያን እርጥበታማና ደረቃማ ክልሎችን እንዲያሳዩ ማድረግ • የሙቀት መጠን ካርታን በመጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሙቀት መጠን ልዩነት እንዲያሳዩ ማድረግ • ዋና ዋና የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎችን እንዲገልጹ ማድረግ • የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ካርታ በመጠቀም የአየር ንብረት ክልሎች እንዲለዩ ማድረግ • በጥንድ ወይም በቡድን በማድረግ የኢትዮጵያን የአየር ንብረት ክልሎች እንዲያወዳድሩና እንዲያነጻጽሩ ማድረግ • የተወያዩበትን ርዕሰ ጉዳይ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት • በቤታቸው ወስደው የሚሠሩትን ተግባር በመስጠት ስለ ኢትዮጵያ አየር ንብረት ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ማድረግ • ሥዕል በማየት፣ በሚና ጨዋታና በአነስተኛ ቡድን በሚሰጥ ተግባር ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች ልዩነቶች እንዲገልጹ ማድረግ • የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅመው ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ያለውን መመሳሰልና ልዩነት እንዲያስተውሉና እንዲለዩ ማድረግ • የእንስሳትና የዕጽዋትን ዋና ዋና ባሕርያት እንዲለዩ ማድረግ • እንስሳትን በአረባባቸው ፣በአካል ገጽታቸው ወይም በሚኖሩበት ቦታ እንዲለዩ/ እንዲመድቡ ማድረግ	• ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ መመልከት • የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ልዩነትን ሲያብራሩ መከታተል • ተግባሮችን ሰጥቶ መከታተል ለምሳሌ ፡ - ከሙቀትና የዝናብ መጠን ሥርጭትን ከሚያሳይ ካርታ ላይ መረጃን የመመዝገብና የማንበብ ክህሎት እንዲያዳብሩ ማድረግ • የአየር ንብረት ይዘት መለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሙቀትና የዝናብ መጠንን መዝግበው እንዲያሳዩ ማድረግ • መረጃ በመያዝ ገንቢ ግብረ መልሶችን መስጠት • የተማሪዎችን ሥራ በማየት ገንቢ ግብረ መልሶችን መስጠት • ተከታታይ ምዘና መስጠት • የተማሪዎችን ተሳትፎ መከታተል • የተመለከቱትን የእንሳሳትንና የዕጽዋትን ዝርያዎች ሲዘረዝሩ መመልከት • በዕጽዋትና በእንስሳት ዝርያዎች መካከል ያለውን መመሳሰልና ልዩነት ሲወያዩ መመልከት • የዕጽዋትንና የእንስሳትን ዝርያዎች በውይይት ሲለዩ መመልከት • ስለ ተማሪዎች ንጽሕና ሁኔታ መረጃ መያዝ (ጥርሳቸውን በምን ያህል ጊዜ እንደሚቦርሹ፣ ገላቸውን በምን ያህል ጊዜ እንደሚታጠቡና የልብሳቸውን ንጽሕና)

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ ዐራት :- ማኅበራዊ አካባቢ ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 54 / 36

አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ሲያጠናቅቁ • የቤተሰብ አባላትን ይዘረዝራሉ • የቤተሰብ አባላት መብትና ኃላፊነትን ይገልጻሉ • የቤተሰብን መሠረታዊ ፍላጎት ይገልጻሉ • የትምህርት ቤት ግቢን ይለያሉ • በትምህርት ቤት ከአቻዎቻቸው ጋር የርስ በርስ ግንኙነት በማዳበር ተግባራትን ያከናውናሉ • በትምህርት ቤትና በአካባቢው የሚገኙ ቦታዎችን የሚያመለክቱ ሥዕሎችን በመሥራት ደኅንነታቸው የሚጠበቁበትን መንገድ ያሳያሉ	4.1 የቤተሰብ አባላትና ሚናቸው 4.2 ለመኖር ምን ያስፈልገናል? 4.3 በአካባቢያችን የሚገኙ ተፈላጊ ዕጽዋቶች 4.4 በትምህርት ቤታችን ምን ምን ነገሮችን እናገኛለን? 4.5 በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንሥራ 4.6 የትምህርት ቤትን ሕግና ደንቦችን መለየት	• ተማሪዎች ዕጽዋትን በአስተዳደጋቸው፤ በውጫዊ ገጽታቸው እና/ ወይም በሚኖሩበት/ በሚገኙበት ስፍራ እንዲመድቡ ማድረግ • በሥዕል የሚነበቡ ነገሮችን መጠቀም፤ በሚና ጨዋታና አነስተኛ ቁጥር ባላቸው በቡድን የሚሠሩ ተግባራት መስጠት • ቤተሰብ አስፈላጊ ተቋም መሆኑን ማሳየት፤ የቤተሰብ አባላትን እንዲለዩ ማድረግና በእነሱም አስተዳደግ ላይ ያላቸውን ወሳኝ ሚና ማመላከት • እነርሱና ቡድናቸው የሚገኙበትን እንዲለዩና እንዲያብራሩ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ቤተሰብ፤ በትምህርት ቤት የሚገኙበት ክፍል) • አንዳንድ ግለሰባዊ ኃላፊነትን እንዲለዩ ማድረግ • ከማን ጋር መጫወት እንደሚፈልጉና ለምን እንደሆነ ምክንያቱን እንዲናገሩ ማድረግ	• በቤተሰብ አባላት መካከል ያለባቸውን ኃላፊነት እንዲገልጹ በማድረግና፤ የቤተሰብ አባላት በቤተሰብ፤ በማኅበረሰብና በሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው ማኅበራዊ ግንኙነትና ኃላፊነት ሲገልጹ መመልከትና ልኬት ማስቀመጥ/ መመዝገብ • በቤተሰብ ኃላፊነት ጉዳይ ሲወያዩና ሲያብራሩ መመልከትና ልኬት ማስቀመጥ • መሠረታዊ ፍላጎቶች (ምግብ፤ ልብስና መጠለያ) ለሰው ልጆች መኖር አስፈላጊ መሆናቸውን ሲያብራሩ መመልከት፤ መከታተልና ልኬት / ውጤት ማስቀመጥና መመዝገብ • የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶችን ሲዘረዝሩና ሲያብራሩ መመልከትና የልኬት ደረጃ ማስቀመጥ • የሚና ተጫዋቾችን ክህሎቶች፤ ተሰጥኦና ፍላጎቶች መመልከትና የልኬት ደረጃ ማስቀመጥ

የአንደኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ አምስት :- ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች — ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 34

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ :- • የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መተግበር • ኤች. አይ. ቪ. በሰውነት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መገንዘብ • ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሕፃናት ንዘኔታና ፍቅር ማሳየት	1. ተሸከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዴት እንጠቀማለን? 2. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምንድን ነው?	• ተማሪዎችን በመንገድ ላይ በተሸከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን መንሥኤ መጠየቅ • ተማሪዎች የመንገዱን ግራ አቅጣጫ ይዘው መጓዝ እንዳለባቸው፣ በእግረኛ መንገድ ማቋረጫ መስመር (zebra lines) ላይ ብቻ መንገድ ማቋረጥ እንደሚገባ እንዲናገሩ ማድረግ • ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ስላለባቸው ቤተሰቦችና ስለ ልጆቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ	• መሠረታዊ የመንገድ ላይ ደንቦችን እንዲናገሩ መጠየቅ •የተማሪዎችን ጽብረቃ መመልከት